
በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

የቆጠራ ካርታ ሥራ መመሪያ



አዲስ አበባ
የካቲት 1995

26

የቆጠራ ካርታ ሥራ መመሪያ

አዲስ አበባ
የካቲት 1995

ማ ው ጫ

አርዕስት ገፅ

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ ---------- 1
1.1 የቆጠራ ካርታ ትርጉም እና የሦስተኛው ዙር ካርታ ሥራ አስፈላጊነት ------- 1
1.2 የቆጠራ ካርታ ሥራ ዋና ዋና ዓላማዎች ---------- 3

ምዕራፍ ሁለት

2. ጽንሰ ሀሳቦች፣ ፍቺዎችና መሠረታዊ የቆጠራ ካርታሥራ ቅደም ተከተሎች ----- 4
2.1 ጽንሰ ሀሳቦችና ፍቺዎች ---------- 4
2.1.1 ቀበሌ ---------- 4
2.1.2 መንደር ---------- 4
2.1.3 ከተማ ---------- 4
2.1.4 ወረዳ ---------- 5
2. 1.5 ዞን ---------- 5
2.1.6 የቆጠራ ቦታ ---------- 5
2.1.7 የመቆጣጠሪያ ቦታ ---------- 6
2.1.8 ቤተሰብ ---------- 6
2.1.9 መደበኛ የቤተሰብ አባል ---------- 7
2.1.10 የቤተሰብ ኃላፊ ---------- 8
2.1.11 ቤት ---------- 8
2.1.12 የጋርዮሽ መኖሪያ ---------- 9
2.2 መሠረታዊ የቆጠራ ካርታ አዘገጃጀት ቅደም ተከተሎች ---------- 9
2.2.1 የካርታ ዓይነቶችና አንዳንድ የካርታ ሥራ ጭብጠች ---------- 9
I. ኮንቱሮች ---------- 13
II. የኮንቱሮች ባህሪያት ---------- 14
2. 2.2 የካርታ አነባበብ ቅደም ተከተሎች ---------- 23

ምዕራፍ ሦስት

3. የጂ.ፒ.ኤስ (GPS) አጠቃቀም ---------- 25
3.1 መግቢያ ---------- 25
3.2 ጂ.ፒ.ኤስ (GPS) ምንድ ነው? ---------- 25
3.3 የጂ.ፒ.ኤስ መቀበያ መሣሪያ ደካማ ጐኖች ---------- 27
3.4 የጂ.ፒ.ኤስ መቀበያ መሣሪያ መሠረታዊ ባህሪያትና አጠቃቀም ---------- 27
3.4.1 የመቀበያ መሣሪያውን ኃይል እንዲያገኝ ማድረግ
(Powering the receiver)---------- 28
3.4.2 የመቀበያ መሣሪያውን ፕሮግራም ማድረግ እና ለሥራ ማዘጋጀት
(Programming and Initializing the receiver) ---------- 29
3.4.3 የሳተላይት ገጽ (satellite page) ---------- 32
3.4.4 የነጥብ ቦታ ገጽ (Position page)---------- 34
3.4.5 የዩ.ቲ.ኤም /UTM/ ኮኦርዲኔቶችን ማስፈር
(Plotting UTM Cordinates) ---------- 35

ምዕራፍ አራት

4. የቆጠራ ካርታ ሥራ በገጠር አካባቢዎች ---------- 40
4.1 በገጠር አካባቢዎች የቆጠራ ቦታ መመስረቻ መመዘኛ ነጥቦች ---------- 40
4.1.1 የቤተሰብ ብዛት በቆጠራ ቦታ ውስጥ ---------- 40
4.1.2 የቆጠራ ቦታ ስፋት ---------- 40
4.1.3 የቆጠራ ቦታ ወሰን ከአስተዳደር መዋቅር አንፃር ---------- 40
4.2 በገጠር አካባቢዎች የቆጠራ ቦታ መመስረቻ ተከታታይ ቅደም ተከተሎች - 41
4.3 በቆጠራ ቦታ ምሠረታ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች ---------- 48
4.4 የገጠር አካባቢ ካርታዎች ዲዛይንና ይዘት ---------- 52
4.4.1 የቆጠራ ቦታ ካርታ ---------- 52
4.4.2 የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ ---------- 55
4.4.3 የወረዳ ካርታ---------- 57
4.5 በገጠር አካባቢዎች የካርታ ሥራ ቅፆች ዓይነትና ይዘት ---------- 59
4.5.1 ቅጽ ገ-1፡- በወረዳ ውስጥ የሚገኙትን የገጠር ቀበሌዎች መመዝገቢያ
ቅጽ ---------- 59
4.5.2 ቅጽ ገ-2፡- የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጽ---------- 62
4.5.3 ቅጽ ገ-3፡- የጋርዮሽ መኖሪያዎች መመዝገቢያ ቅጽ ---------- 66

4.5.4 ቅጽ ገ-4፡- የልዩ ቆጠራ ቦታ መመዝገቢያ ቅጽ ---------- 69
4.5.5 ቅጽ ገ-5፡- የገጠር ቆጠራ ድንበር መግለጫ ቅጽ ---------- 72
4.5.5 ቅጽ ገ-6፡- በገጠር የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባብ መመዝገቢያ ቅጽ ---------- 74

ምዕራፍ አምስት

5. የቆጠራ ካርታ ሥራ በከተማ አካባቢዎች ---------- 80
5.1 በከተማ አካባቢዎች የቆጠራ ቦታ መመሥረቻ መመዘኛ ነጥቦች ---------- 80
5.2 የከተማ ቆጠራ ቦታዎች መመሥረቻ ተከታታይ ቅድም ተከተሎች-------- 81
5.3 ልዩ የቆጠራ ቦታዎች በተከማ አካባቢዎች---------- 84
5.4 የከተማ አካባቢ ካርታዎች ዲዛይንና ይዘት ---------- 85
5.4.1 የቆጠራ ቦታ ካርታ---------- 85
5.4.2 የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ ---------- 88
5.4.3 የጂ.ፒ.ኤስ ንድፍ ካርታ /ማስተር ፕላን ለሌላቸው ከተሞች/ -------- 90
5.5 የጂ.ፒ.ኤስ ንድፍ (GPS SKETCH) አሠራር ---------- 92
5.6 ለከተማ አካባቢዎች የካርታ ሥራ ቅፆች ዓይነትና ይዘት ---------- 99
5.6.1 ቅጽ ከ-1፡- የከተሞች፣ ወረዳዎች/ክፍተኞችና ቀበሌዎች መመዝገቢያ ቅጽ---------- 99
5.6.2 ቅጽ ከ-2፡ የቤቶችና የቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ ----------102
5.6.3 ቅጽ ከ-3፡- በከተማ የጋርዮሽ መኖሪያዎች መመዝገቢያ ቅጽ ------109
5.6.4 ቅጽ ከ-4፡ የልዩ የቆጠራ ቦታ መመዝገቢያ ቅጽ/100 እና ከዚያ በላይ ነዋሪዎች ያሉባቸው የጋሪዮሽ መኖሪያዎች/ ----------112
5.6.5 ቅጽ ከ-5፡ የከተማ ቆጠራ ቦታ መግለጫ ቅጽ----------115
5.6.6 ቅጽ ከ-6፡ የከተማ የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባብ ----------117
5.6.7 ቅጽ ከ-7፡- የከተማ ቆጠራ ቦታ መለያዎች ዝርዝር ማስፈሪያ ቅጽ --123

6. ዕዝል I፡- የጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያ ዋና ዋና ገጾች----------127
7. ዕዝል II፡- በጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያ ውስጥ የባትሪ ድንጋይ ትክክለኛ አቀማመጥ ማብራሪያ ----------128
8. ዕዝል III የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች መመዝገቢያ ቅጽ/ቅጽከ-6/ እና የተጂ ከተማ ንድፍ----------130
9. ዕዝል IV፡- የካርታ ምልክቶችና መግለጫዎች----------133
10. ዕዝል V፡- የእንቅስቃሴ መከታተያ ዝርዝር ----------135
11. ዕዝል VI፡- የካርታና ቅፆች መረካከቢያ ቅፅ (ቅፅ ካቅመ-ገ እና ቅፅ ካቅመ -ከ)----------145

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ

የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ በተወሰነ ወቅትና የአስተዳደር ክልል ስለህዝብ ባህሪያት፤ ስለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እንዲሁም ስለቤቶች ሁኔታ የሚገልፁ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ፤ የማጠናቀርንና የመተንተንን ከዚያም አስተማማኝነቱን እና ትክክለኛነቱን በመገምገም የተገኘውን ውጤት የማሰራጨት ተግባራትን ያጠቃልላል። ቆጠራው የሚካሄድበት ክልል በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ የአንድን ሀገር የአስተዳደር ክፍሎች ሊያጠቃልል ስለሚችልም በቆጠራው በተሸፈኑት ከዝቅተኛው የአስተዳደር ክፍል ጀምሮ የኢኮኖሚና የማህበራዊ መረጃዎች ለማቅረብ ያስችላል።

የአንድን ሀገር ሕዝብ ብዛት፤ የሕዝቡን የማህበራዊና የኢኮኖሚ ሁኔታ በትክክል የሚያመለክት መረጃ ከሌለ አስተማማኝ ዕቅድ ለማዘጋጀትና ፖሊሲ ለማውጣት አዳጋች ይሆናል። ስለዚህም የሕዝብና ቤት ቆጠራ ቢያንስ በየአሥር ዓመቱ አንድ ጊዜ ይካሄዳል።

ሦስተኛው የኢትዮጵያ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ በየካቲት ወር 1999 ይካሄዳል። በግንቦት 1976 እና በጥቅምት 1987ቱ በመጀመሪያውና በሁለተኛው ዙር ቆጠራዎች እንደተደረገው ሁሉ ሦስተኛውም የሚከናወነው በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን የበላይ ኃላፊነት፤ በህዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት አስፈፃሚነት እንዲሁም ከሌሎች የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ነው።

የቆጠራ ክንውን የሚከተሉትን አጠቃላይ ተግባራት ያጠቃልላል።

ሀ. የቅድመ ዝግጅት ሥራ
ለ/ ቆጠራ
ሐ/ መረጃ ማቀነባበር
መ/ የመረጃ ትንተናና የውጤቱ ግምገማ
ሠ/ የተሟላ የቆጠራ ልምድ ሪከርድ ዝግጅት
ረ/ ውጤቶችን ለተጠቃሚዎች ማሰራጨት።

1.1 የቆጠራ ካርታ ትርጉም እና የ3ኛው ቆጠራ ካርታ ሥራ አስፈላጊነት

የቆጠራ ካርታ ማለት ማንም ሰው ወይም ቤት ሳይቆጠር እንዳይቀር እንደዚሁም ከአንድ ጊዜ በላይ እንዳይቆጠር ለማድረግ ቆጠራው ከመከናወኑ በፊት የቆጠራ ቦታና የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎችን ማዘጋጀት ነው። በቅድመ ዝግጅት ሥራ ወቅት ከሚከናወኑት ተግባራት ዋነኛው የቆጠራ ካርታ ሥራ ማዘጋጀት ይሆናል። የዚህም ሥራ ግብ አገሪቱን በአነስተኛ ክልሎች ማለትም በቆጠራ ቦታና በመቆጣጠሪያ ቦታዎች ሸንሽኖ ካርታዎችን በማዘጋጀት ለቆጠራ ተግባር ማዋል ነው።

የቆጠራ ካርታ ሥራው በመነሻነት የሀገሪቱን አስተዳደራዊ ክፍፍል ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን ይኖርበታል። ኢትዮጵያ በዘጠኝ ክልሎች ማለትም ትግራይ፤ አማራ፤ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፤ ጋምቤላ፤ አሮሚያ፤ የደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፤ አፋር፤ ሐረሪና ሶማሌ እንዲሁም ሁለት የከተማ አስተዳደሮች ማለትም አዲስ አበባና ድሬዳዋ የተከፈለች ናት። እነዚህ ክልሎችና የከተማ አስተዳደሮች ደግሞ በዞኖችና በወረዳዎች የተከፋፈሉ ናቸው።

በገጠሩ አካባቢ ወረዳዎች በገጠር ቀበሌዎች በከተማ አካባቢዎች ደግሞ ከተሞች በከተማ ቀበሌዎች የተከፋፈሉ ናቸው። የካርታ ሥራው የሚጀምረው ከወረዳዎች ይሆናል። የቆጠራ ካርታ ሥራው የሚጠናቀቀው የገጠሩና የከተማው የአገሪቱ ክፍሎች በሙሉ የአስተዳደር ክልሎችን በመከተል በቆጠራ ቦታዎች ተሸንሽነው (ተከፋፍለው) ሲጠናቀቁ ይሆናል።

ሁለተኛው ዙር የቆጠራ ካርታ ከተዘጋጀ ከዘጠኝ ዓመት በላይ ሆኖታል። በዚህ ጊዜ ውስጥ በአገሪቱ ውስጥ የተለያየ ተፈጥሯዊና ሰው ሠራሽ /የአሰፋፈር፤ የግንባታ፤ ...ወዘተ/ ለውጦች ተከስተዋል። የሕዝብ ብዛት፤ ሥርጭቱና የመሳሰሉትም ሌሎች የተከሰቱ ለውጦች ናቸው። በገጠር ቀበሌዎች የተለያዩ ለውጦች ማለትም የመቀላቀል፤ በሁለት የመከፈልና የሽግሽግ ሂደቶች ታይቶባቸዋል። በዚህ የተነሳ ቀድሞ የተሰራው የቆጠራ ካርታ እንዳለ ለአሁኑ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ሥራ አገልግሎት ሊውል አይችልም።

ስለዚህ ከላይ በተጠቀሱት የተለያዩ ለውጦች ምክንያት የ1987 ዓ.ም. የቆጠራ ካርታዎችን ለቆጠራ ተግባር ጥቅም ላይ ማዋል ስለማይቻል አዲስ የቆጠራ ካርታዎችን የመከለልና አዲስ የቆጠራ ካርታዎችን የማዘጋጀት ተግባር ለሦስተኛው ዙር ቆጠራ መሣካት ከፍተኛ አስፈላጊነትና ጠቀሜታ ይኖረዋል። ሦስተኛው ዙር የቆጠራ ካርታ ሥራ የሚከተሉትን የአሰራር ዘዴዎች ተከትሎ ይከናወናል። እነዚህም፦

ሀ. በኢትዮጵያ ካርታ ሥራ ባለሥልጣን የሚታተሙትን የቶፖግራፊ ካርታዎችና የከተማ ካርታዎች ወቅታዊ በማድረግ አዲስ የቆጠራና የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎችን ማዘጋጀት፤

ለ. በከፍተኛ መሥፈርት መነሻ ካርታዎች ባልተሸፈኑ የከተማ አካባቢዎች ደግሞ የካርታ ኮኦርዲኔቶችን ያካተቱ የጂ.ፒ.ኤስ ንድፎችን (sketchs) በመሥራት የቆጠራ እና መቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎችን ማዘጋጀት ናቸው።

በሁለቱም የአሠራር ዘዴዎች የካርታ ሥራው የሚከናወነው የጂ.ፒ.ኤስ ሳተላይት መቀበያ መሣሪያዎችንና ሌሎች የካርቶግራፊ ቴክኒኮችን ጥቅም ላይ በማዋል ይሆናል።

ይህን ተግባር በማከናውን የቆጠራ ካርታ ሠራተኞች ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወቱ ይጠበቃል። የቆጠራ ካርታ ሠራተኞች ተግባር በገጠርና በከተሞች የቆጠራ ካርታ ሥራን

ማከናወን ይሆናል። ለዚህም ስለካርታ ፅንሰ-ሃሳቦች፤ ስለቆጠራ ካርታ ሥራ ምንነትና እንዴት እንደሚዘጋጅ ሠራተኞች በቂ ዕውቀት ሊኖራችው ይገባል። በተጨማሪም በካርታ ሥራው የሚዘጋጁ ካርታዎች እንዴት ለሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ማከናወኛ እንደሚውሉ መረዳት ይገባቸዋል።

1.2 <u>የቆጠራ ካርታ ሥራ ዋና ዋና ዓላማዎች</u>

የቆጠራ ካርታ ሥራ ዋና ዋና ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው።

ሀ. <u>የሽፋን ቁጥጥር</u>፡- የቆጠራና የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎች በቆጠራ ወቅት የቤተሰቦችንና የቤቶችን መዘለል ወይም ደጋግሞ መቆጠር እንዳይከሰት ለመቆጣጠር ያስችላሉ።

ለ. <u>የጥራት ቁጥጥር</u>፡- የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎች በቆጠራ ወቅት የቁጥጥር ተግባርን ለማቀናጀትና የመስክ ሥራ ክንውንን በተገቢው መንገድ ለመከታተልና ለመቆጣጠር ያስችላሉ።

ሐ. <u>የሰው ኃይል ብዛት ለመወሰን</u>፡- የቆጠራ ቦታዎችና የመቆጣጠሪያ ቦታዎች መመስረትና ካርታዎችን ማዘጋጀት የሕቤቆኮ ጽ/ቤት ለቆጠራው ሥራ ምን ያህል ቆጣሪዎችና ተቆጣጣሪዎች እንደሚያስፈልጉ በቅድሚያ ለማወቅ ይረዳዋል። በዚህ ዓይነት በቆጠራው ሥራ ወቅት የሰው ኃይል እጥረት እንዳይከሰት ተገቢው ቅደመ ዝግጅት ሊከናወን ይችላል።

መ. <u>ለመስክ ሥራ የሚያስፈልጉ ቁሣቁሶችን (ሎጂስቲክስ) ለመወሰን</u>፡- የቆጠራው ካርታ ሥራ ውጤት ለቆጠራው የሚያስፈልገውን የቅጾችና መጠይቆች ብዛት፤ የጽሕፈት መሣሪያዎች፤ የተሸከርካሪዎች፤ ...ወዘተ ብዛት በቅድሚያ ለማወቅ ይረዳል።

ሠ. <u>ተመጣጣኝ የሥራ ክፍፍል (Fair distribution of workload)</u>፡- ሐገሪቱን በቆጠራና በመቆጣጠሪያ ቦታዎች መከፋፈል በቆጠራ ወቅት እያንዳንዱ ቆጣሪና ተቆጣጣሪ የተመጣጠነ የሥራ ድርሻ እንዲኖራቸው ለማድረግ ይረዳል። ይህም ሁሉም የቆጠራው ሠራተኞች ሥራቸውን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ለመፈጸም ያስችላቸዋል።

ረ. <u>ስታቲስቲካዊ ናሙና ፍሬም ዝግጅት</u>፡- ሐገሪቱን በቆጠራ ቦታዎች መከፋፈል በየጊዜው ለሚካሄዱ የሥነህዝብ፤ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጥናቶች ፍሬም ለማዘጋጀት ይረዳል።

<u>ማስታወሻ</u>

ይህ መመሪያ <u>የአርብቶ አደር</u> አካባቢዎችን በተመለከተ የቆጠራ ካርታ ዝግጅት አሠራርን አይጨምርም።

ምዕራፍ ሁለት

2. ፅንሰ ሃሳቦች፡ ፍቺዎችና መሠረታዊ የቆጠራ ካርታ ሥራ ቅደም ተከተሎች

በዚህ ምዕራፍ የተወሰኑ ፅንሰ ሃሳቦችና ፍቺዎቻቸው ቀርበዋል። በተጨማሪም የቆጠራ ካርታ ሥራ መሠረታዊ ሀሳቦችም ተሰጥተዋል።

2.1 ፅንሰ ሃሳቦችና ፍቺዎች

2.1.1 ቀበሌ፡- በወረዳ ውስጥ የሚገኝ ዝቅተኛ የአስተዳደር ክልል ቀበሌ ይባላል። ባጠቃላይ ቀበሌ በወረዳ ውስጥ የሚገኝ ድንበሩ በግልጽ የሚታወቅና የራሱ ሕጋዊ አመራር ያለው የአስተዳደር አካል ነው። ቀበሌዎች በቤተሰብና በሕዝብ ብዛት በከፍተኛ ደረጃ ሊለያዩ እንደሚችሉ መገንዘብ ያስፈልጋል። በገጠር የገጠር ቀበሌዎች የሚባሉ ሲሆን በከተማ ደግሞ የከተማ ቀበሌዎች ተብለው ይታወቃሉ። (ነገር ግን የገጠር ቀበሌዎች በአንዳንድ አካባቢዎች የተለየ ስያሜ አላቸው። ለምሳሌ በትግራይ ጣቢያ እንደ ቀበሌ ይወሰዳል)።

ሀ. የገጠር ቀበሌ፡- በወረዳ ውስጥ በገጠር አካባቢ የሚገኝ ዝቅተኛ የአስተዳደር አካል ነው። ይህ መስተዳድር በግብርናም ሆነ ከግብርና ውጭ በሌላ ሥራ የተሰማሩ የገጠር ነዋሪዎችን ያቀፈ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ነው።

ለ. የከተማ ቀበሌ፡- በከተማ ውስጥ የሚገኝ ዝቅተኛ የአስተዳደር አካል ሲሆን በውስጡ የሚገኙ የከተማ ነዋሪዎችን ያቀፈ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ነው።

2.1.2 መንደር (Locality)፡- በቀበሌ ውስጥ የሚገኝ በአሰፋፈሩና በአቀማመጡ ተለይቶ የሚታይ አነስተኛ የቆዳ ስፋት ያለውና ሰዎች ሰብሰብ ብለው የሚኖሩበት አካባቢ መንደር ይባላል። በአንድ መንደር ውስጥ ዘርዘር ያሉ ወይም የተቀራረቡ ቤቶች ይኖሩና በርከት ያለ ሕዝብ ሊኖርበት ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ አሠፋፈር በአካባቢው የሚታወቅበት የመጠሪያ ስም ይኖረዋል። አንድ መንደር የገበያ ቦታን፡ ት/ቤትንና የመሳሰሉትን ሊያካትት ይችላል።

2.1.3 ከተማ፡- በአጠቃላይ አነጋገር ከተማ ማለት ሰዎች በአንድ ላይ ተሰባስበው የሚኖሩበትና በዋናነት ከግብርና ውጭ በሆነ የሥራ መስክ ተሠማርተው የሚገኙ 2000 እና በላይ ነዋሪዎች ያሉት ከተማ ይባላል። ሆኖም ለቆጠራ ካርታ ሥራ አመቺነት ሲባል የነዋሪዎች ብዛት ሳይወስናቸው የሚከተሉት እንደ ከተማ ይወሰዳሉ።

ሀ/ የአስተዳደር ዋና ከተሞች

i) የክልል ዋና ከተሞች

ii) የዞን ዋና ከተማዎች ግን በ(i) ውስጥ ያልታቀፉ

iii)የወረዳ ዋና ከተሞች ግን በ(i) ና (ii) ውስጥ ያልታቀፉ

iv) የከተማ ቀበሌዎች የተቋቋመባቸው ግን ከ(i)-(iii) ያልታቀፉ

ለ/ በ«ሀ» ውስጥ ያልታቀፉ ማዘጋጃ ቤት ያላቸው ከተሞች

ሐ/ ከላይ በ«ሀ» ና በ«ለ» ያልታቀፉ፤ 1000 እና በላይ ነዋሪዎች ያላቸውና አብዛኛው ሕዝብ ከግብርና ውጭ በሆነ የሥራ ዘርፍ የተሰማራባቸው መንደሮች እንደ ከተማ ይወሰዳሉ:: ነገር ግን ከ1000 በታች ነዋሪዎች ያሏቸው ሆነው አብዛኛው ሕዝብ ከግብርና ውጪ በሆነ የሥራ ዘርፍ የተሰማራባቸው መንደሮች እንደ ገጠር ይወሰዳሉ::

2.1.4 <u>ወረዳ</u>:- ተቀራራቢ/ኩታገጠም ቀበሌዎችን በማካተት የተመሠረተ ከቀበሌ ቀጥሎ የሚገኝ ከፍ ያለ የአስተዳደር አካል ነው:: ወረዳዎች የየራሳቸው ሕጋዊ ሰውነት ያላቸው ናቸው:: ወረዳዎች የገጠርና የከተማ ወይም የገጠር ብቻ ወይም የከተማ ብቻ የሆኑ ቀበሌዎችን አካተው የተመሠረቱ ሊሆኑ ይችላሉ::

2.1.5 <u>ዞን</u>:- በክልል ውስጥ የሚገኝ ሆኖ፤ ተቀራራቢ/ኩታገጠም ወረዳዎችን በማካተት የተመሠረተ ከወረዳ ቀጥሎ የሚገኝ ከፍ ያለ የአስተዳደር አካል ነው:: ዞኖች የየራሳቸው ህጋዊ ሰውነት ያላቸው ሲሆን ዋና ተግባራቸውም በሥራቸው ያሉትን ወረዳዎች ተግባር ማቀናጀት ነው:: ዞኖች የገጠርና የከተማ ወይም የከተማ ብቻ የሆኑ ወረዳዎችን አካተው የተመሠረቱ ሊሆኑ ይችላሉ::

2.1.6 <u>የቆጠራ ቦታ</u>:- ቤተሰቦችንና ቤቶችን ሳይዘለሉ ወይም ያለ ድግግሞሽ ለመቁጠር በሚያስችል መንገድ የተከለለ የመሬት አካል የቆጠራ ቦታ ይባላል:: ለቆጠራው ሥራ ሲባል አንድ ቆጠራ ቦታ በገጠር ከ150-200 ቤተሰቦች ይይዛል:: (የተበታተነ የሕዝብ አሰፋፈር ባለበት የቤተሰቦች ብዛት ከተጠቀሰው ሊያንስ ይችላል::) በከተማ ደግሞ አንድ የቆጠራ ቦታ ከ150-200 ቤቶችን ይይዛል:: የቆጠራ ቦታ ከከተማ ቀበሌዎች ወይም ከገጠር ቀበሌዎች ጋር ከሚከተሉት በአንዱ መንገድ መዛመድ ይኖርበታል::

ሀ. በአንድ የገጠር ቀበሌ የሚገኘው የቤተሰብ ብዛት ከ150-200 ወይም በታች ከሆነ የገጠር ቀበሌው እንዳለ አንድ የቆጠራ ቦታ ይሆናል:: በተመሳሳይ መንገድ በአንድ የከተማ ቀበሌ የሚገኙ የቤቶች ብዛት ከ150-200 ወይም በታች ከሆነ የከተማ ቀበሌው አንድ የቆጠራ ቦታ ይሆናል::

ለ. አንድ የቆጠራ ቦታ የገጠር ቀበሌ ወይም የከተማ ቀበሌ አካል ሊሆን ይችላል። በሌላ አነጋገር አንድ የገጠር ቀበሌ ወይም የከተማ ቀበሌ ከአንድ የቆጠራ ቦታ በላይ ሊከፋፈል ይችላል።

ሐ. አንድ የቆጠራ ቦታ ድንበር የገጠር ቀበሌን፤ ወይም የከተማ ቀበሌን ድንበር አቋርጦ መሄድ አይኖርበትም።

<u>ማስታወሻ</u>፡- ከላይ ከሀ-ሐ በተጠቀሰው በማንኛውም መንገድ የተመሠረተ የአንድ ቆጠራ ቦታ ክልል በሚገባ መከለልና ድንበሩም በዝርዝር መገለጽ ይኖርበታል።

2.1.7 <u>የመቆጣጠሪያ ቦታ</u>፡- አንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ አጠገብ ላጠገብ የሚገኙ የቆጠራ ቦታዎችን አንድ ላይ አጣምሮ የሚይዝ የመሬት አካል ነው። የመቆጣጠሪያ ቦታ የቆጠራው ሥራ ሽፋን የተሟላ እንዲሆንና ጥራቱንም ለመቆጣጠር የሚረዳ ነው። አንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ በአማካይ 5 የቆጠራ ቦታዎችን ይይዛል። የመቆጣጠሪያ ቦታ ድንበር የወረዳ ድንበርን አቋርጦ መሄድ አይኖርበትም።

<u>ማስታወሻ</u>፡- የመቆጣጠሪያ ቦታዎች ምሥረታ የሚከናወነው በወረዳው ውስጥ የሚገኙት የገጠርና የከተማ ቆጠራ ቦታዎች ምሥረታ ሙሉ በሙሉ ከተጠናቀቀ በኋላ መሆኑ በሚገባ መታወቅ ይኖርበታል።

2.1.8 <u>ቤተሰብ</u>፡- ማለት በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች ብዙውን ጊዜ አብረው የሚኖሩትንና ምግባቸውን በአንድነት አብስለው የሚመገቡ ሰዎችን ያጠቃልላል። የቤተሰብ አባላት ብዛት ሊለያይ ይችላል። ይኸውም አንድ ሰው ብቻውን እንደ አንድ ቤተሰብ ሊቆጠር ይችላል። አብዛኛውን ጊዜ አንድ ቤተሰብ ባልን፤ ሚስትን፤ ልጆችንና ሌሎች ዘመዶችን ይይዛል። የቤተሰብ አባሎች በሥጋ ወይም በጋብቻ የሚዛመዱና የማይዛመዱትን ሊያጠቃልል ይችላል። በሥጋ/በጋብቻ የማይዛመዱ ሲባል እንደ ቤት ሠራተኞች፤ ተቀጣሪ የግብርና ሠራተኞች፤ ጓደኞችና የመሳሰሉት ሊሆኑ ይችላሉ።

የቤተሰብን ትርጉም ከጋብቻ ዓይነት ጋር አዛምዶ ማየት ጠቃሚ ይሆናል። የጋብቻው ዓይነት በአንድ ሚስት ብቻ የተመሠረተ ከሆነ ቤተሰብ ባልን፤ ሚስትን፤ ልጆችን፤ የጉዲፈቻ ልጆችን፤ ሌሎች ዘመዶችንና ዘመድ ያልሆኑትን/ የቤት ሠራተኞችን፤ ተቀጣሪ የግብርና ሠራተኞችን፤ ...ወዘተ/ ሊያጠቃልል ይችላል። ነገር ግን ጋብቻው ከብዙ ሚስቶች ጋር የተመሠረተ ከሆነ /አንድ ወንድ ከአንድ በላይ ሚስቶች ከአሉት/ የሰውየው ሚስቶች ከነልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ...ወዘተ በአንድ ቤት ወይም በተቀራረቡ ቤቶች የሚኖሩና ምግባቸውንም በአንድነት አብስለው የሚመገቡ ከሆነ እንደ አንድ ቤተሰብ ይቆጠራሉ። ነገር ግን የሰውየው ሚስቶች ከነልጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ...ወዘተ በተለያዩ ቤቶች የሚኖሩና ምግባቸውንም

በአንድነት አብስለው የሚይመገቡ ከሆነ ባልየው በቅድሚያ ከአገባትና በህይወት ከአለችው ሚስቱ በስተቀር እያንዳንዳቸው የሰውየው ሚስቶች የየራሳቸው ቤተሰብ እንዳላቸው ሆኖ መቆጠር አለባቸው። ባልየው ደግሞ በቅድሚያ ከአገባትና በህይወት ካለችው ሚስቱ ጋር እንደ ቤተሰብ ይቆጠራል።

2.1.9 <u>መደበኛ የቤተሰብ አባል</u>፦ የአንድ ቤተሰብ መደበኛ አባል የሚባለው በቤተሰቡ ቢያንስ ለስድስት ወራት ባለማቋረጥ የኖረን ግለሰብ ነው። ከስድስት ወር በታች በጊዜያዊነት ከቤተሰቡ የተለዩ ግለሰቦች የተለዩት ቤተሰብ መደበኛ አባል ተደርገው ይወሰዳሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ለስድስት ወራትና ከዚያ በላይ ያለማቋረጥ ከቤተሰቡ የተለዩ ግለሰቦች እንደ ቤተሰቡ መደበኛ አባል አይቆጠሩም። መደበኛ የቤተሰቡ አባላትን በሚገባ ለመለየት እንዲቻል የሚከተሉትን ነጥቦች መገንዘብ ያስፈልጋል።

ሀ. በቤተሰብ ምዝገባ ወቅት በቤተሰቡ የሚገኙ መደበኛ ነዋሪዎች በሙሉ የቤተሰብ መደበኛ አባል ናቸው።

ለ. በቤተሰብ ምዝገባ ወቅት ቤተሰቡን በጊዜያዊነት ከተለዩ ስድስት ወር ያልሞላቸው በሙሉ የቤተሰቡ መደበኛ አባል ተደርገው ይወሰዳሉ።

ሐ. በቤተሰብ ምዝገባ ወቅት ሌላ የመኖሪያ ሥፍራ የሌላቸው ሆነው ቤተሰቡን ከተቀላቀሉ ስድስት ወር ባይሞላቸውም የቤተሰቡ መደበኛ አባል ተደርገው ይወሰዳሉ። ሆኖም እንግዶች ፣ ልጅ ለመውለድ ወደ ቤተሰቡ የመጡ ሴቶች ... ወዘተ፤ በቤተሰቡ ከስድስት ወር በላይ ለመቆየት ካላሰቡ በስተቀር የቤተሰቡ መደበኛ አባል ተደርገው አይወሰዱም። በተመሳሳይ መንገድ የነበሩበትን ቤተሰብ ላይመለሱበት የለቀቁ ግለሰቦች ቤተሰቡን ከለቀቁ ስድስት ወር ባይሞላቸውም የቤተሰቡ መደበኛ አባል ተደርገው አይወሰዱም። የራሳቸውን ጎጆ መስርተው፤ በሥራ ዝውውር ወላጆቻቸውን ተለይተው የሚሄዱ ግለሰቦች ለዚህ እንደምሳሌ ሊወሰዱ ይችላሉ።

መ. በቤተሰብ ምዝገባ ወቅት የቤተሰብ ኃላፊ ወይም ማንኛውም አባል ከቤተሰቡ ለስድስት ወር ወይም ከዚያ በላይ ተለይቶ ከሆነ እንደቤተሰቡ መደበኛ አባል አይቆጠርም።

ሠ. <u>ልዩ ሁኔታ</u>

i) <u>ተማሪዎች</u>፦ ከቤተሰቦቻቸው ተለይተው ትምህርት በሚማሩበት ከተማ የሚኖሩ ተማሪዎች የከተማው ነዋሪ እንጂ ቤተሰቦቻቸው የሚኖሩበት አካባቢ ነዋሪ ተደርገው አይወሰዱም። ነገር ግን ከወላጆቻቸው ጋር እየኖሩ ትምህርት ቤታቸው ወደሚገኝበት ከተማ በየቀኑ የሚመላለሱ ተማሪዎች የወላጆቻቸው ቤተሰብ መደበኛ አባል ተደርገው ይወሰዳሉ።

ii) <u>የጉልበት ሠራተኞች</u>፡- በሥራ ፀባያቸው የተነሣ ቤተሰቦቻቸውን ትተው ራቅ ያለ አካባቢ በመሄድ የካምፕ ኑሮ የሚኖሩ ሠራተኞች ከቤተሰቦቻቸው ከተለዩ አጭር ጊዜም ይሁን ረዥም ጊዜ የሚቆጠሩት በቤተሰቦቻቸው ዘንድ ይሆናል። ሆኖም ሌላ መኖሪያ የሌላቸው ሠራተኞች በካርታ ሥራው ወቅት በሚገኙበት ቦታ ይመዘገባሉ።

iii) <u>የጋርዮሽ መኖሪያ አባላት</u>፡- እስረኞች፤ በመጦሪያ ቤት የሚኖሩ ጡረተኞች፤ ወላጆቻቸው የሞቱባቸውና በሕፃናት ማሳደጊያ የሚኖሩ፤ በሆስፒታል የሚኖሩ የአእምሮ በሽተኞች በሙሉ እንደ ቤተሰብ መደበኛ አባላት ሳይሆን እንደ ጋርዮሽ ነዋሪ ተደርገው መወሰድ አለባቸው። በሌላ በኩል በሆስፒታሎች ተኝተው ሕክምና የሚደረግላቸው ግለሰቦች እንደ ሆስፒታሉ ነዋሪ ሳይሆን የየመጡበት ቤተሰብ መደበኛ አባል ተደርገው ይወሰዳሉ።

2.1.10 <u>የቤተሰብ ኃላፊ</u>፡- በቤተሰቡ አባላት የቤተሰቡ መሪ/ኃላፊ ተደርጎ የሚወሰድ ማንኛውም የቤተሰቡ አባል የቤተሰብ ኃላፊ ይባላል። ኃላፊው ወንድ ወይም ሴት ሊሆን ይችላል። ከአንድ ሚስት በላይ በሚገኝበት የጋብቻ ሁኔታ ሚስቶች የየራሳቸው ቤተሰብ ካላቸው ሚስቶቹ ወይም ትልቅየው/ዋ ልጅ ወይም ቤተሰቡ የወከለው ግለሰብ እንደ ኃላፊ ይወሰዳሉ።

2.1.11 <u>ቤት</u>፡- በአሠራሩ ተለይቶና ራሱን የቻለ የሕንፃ «ነፃ» አካል የሆነ፤ ለመኖሪያ ወይም እንደ ትምህርት ቤት፤ መጋዘን፤ ቡና ቤት፤ ፀጉር ማስተካከያ፤ ማምረቻ ድርጅት ወይም ለሌላ አገልግሎት የሆነ ቤት ይባላል። በቆጠራው ሥራ ወቅት ተንቀሳቃሽ መጠለያዎች፤ ድንኳኖች፤ ተሳታኞች ሁሉ ለሰዎች መኖሪያ እስካገለገሉ ድረስ እንደ ቤት ይቆጠራሉ።

ቤት ማለት «በአሠራሩ ተለይቶ» እና «ራሱን የቻለ» ሆኖ ለመኖሪያ ብቻ፤ ለመኖሪያና ለድርጅት ወይም ለድርጅት ብቻ የሚያገለግልና ለማገልገል የተዘጋጀ ነው።

<u>የቤቱ አሠራር የተለየ ነው</u>፤ የሚባለው ዙሪያውን በግድግዳ የተከለለ ሆኖ ጣራውም በክዳን የተሸፈነ ሲሆንና በውስጡ የሚኖሩት ሰዎች በሚተኙበት ጊዜ፤ ምግባቸውን ሲያዘጋጁና ሲመገቡ ከሌሎች በዙሪያው ከሚኖሩ ሰዎች ለመለየት የሚያስችል ሲሆን ነው። ሆኖም አንዳንድ ጊዜ በግጠራ፤ በፕላስቲክ፤ በካርቶን፤ ...ወዘተ ግድግዳው የተሠራ ወይም የተከበበና ጣራው በፕላስቲክ የተሸፈነ ሆኖ ለድርጅት ወይም ለመኖሪያ የሚያገለግል ቤት ሊያጋጥም ይችላል። ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም ምንም እንኳን የቤትን ትርጉም ባያሟላም ከአገልግሎቱ አንፃር ሲታይ ቤት ስለሆነ እንደ

ቤት ይወሰዳል። ነገር ግን በፕላስቲክና በመሣሣሉት ቁሳቁሶች የሚሠሩና ለማደሪያነት ብቻ ተጠቅመውባቸው ቀን ቀን የሚፈርሱ፤ ለመዋያነት ብቻ የሚያገለግሉ ከሆነ እንደ ቤት አይቆጠሩም። ድንኳኖችም እንደቤት እንደሚቆጠሩ ማስተዋል ያስፈልጋል።

<u>የቤቱ አሠራር ራሱን የቻለ ነው፤</u> የሚባለው ቤቱ ከመንገድ ወይም የጋራ በሆነ መተላለፊያ፤ መሬት፤ ...ወዘተ የራሱ መግቢያና መውጪያ ያለው ሆኖ በውስጡ የሚኖሩት ሰዎች ወደ ቤት ሲገቡ ወይም ከቤት ሲወጡ የሚተላለፉት በሌሎች ቤት ውስጥ በማለፍ ሳይሆን በቀጥታ በራሳቸው መውጪያ ወይም መግቢያ ብቻ ሲሆን ነው።

2.1.12. <u>የጋርዮሽ መኖሪያ፡-</u> በዝምድና ያልተሣሰሩ /የተሣሰሩም ሊሆኑ ይችላሉ/ ከቤቱ የሚገኙ አገልግሎቶችን በጋራ አብረው የሚካፈሉ ሰዎች የሚኖሩበት ሥፍራ ነው። ይኸውም ሆቴል/ሆስቴል፤ አዳሪ ትምህርት ቤቶች፤ የሕፃናት ማሳደጊያዎች፤ የጡረተኞች መጦሪያ ቦታዎች፤ ፀባይ ማረሚያዎች/ወህኒ ቤቶች/፤ የወታደር ካምፖች፤ አድባራት፤ በጋራ የሚኖሩ ሠራተኞች ካምፖች፤ ማቋቋሚያ ማዕከሎች፤ ...ወዘተ እንደ ምሳሌ ሊጠቀሱ የሚችሉ የጋርዮሽ መኖሪያዎች ናቸው።

በአንዳንድ የጋርዮሽ መኖሪያዎች ራሳቸውን የቻሉ ቤተሰቦች ሊገኙ እንደሚችሉ ማወቅ ያስፈልጋል።

2.2 <u>መሠረታዊ የቆጠራ ካርታ አዘገጃጀት ቅደም ተከተሎች</u>

2.2.1 <u>የካርታ ዓይነቶችና አንዳንድ የካርታ ሥራ ጭብጦች፡-</u>

የካርታ ሥራ ዓላማ ስለ መሬት አቀማመጥ የሚያመለክቱ መረጃዎችን ሰብስቦ በመተንተንና ባነሰ መስፈርት በመጠቀም በቀላሉ ሊነበብ በሚችል ሥዕላዊ መንገድ የመሬትን አቀማመጥ ማሳየት ነው። ካርታ ሰዎች ሊረዱ በሚችሉበት መንገድ የመሬትን ገፅታ ከላይ ሲታይ ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ስዕል ሲሆን ለተጠቃሚ ግልጽ ለማድረግ የተለያዩ ፊደሎችና ምልክቶች ይታከሉበታል።

ካርታ ከየትኛውም ከፍታ በታ ሆኖ የሚታየውን የመሬት አቀማመጥና ሌሎች ገፅታዎች የሚያሳይ ሆኖ በተጨማሪም በራሳቸው በግልጽ ሊታዩ የማይችሉ ገጽታዎችን ለምሳሌ እንደ አለም አቀፍ ወሰኖችን፤ የአስተዳደር ክልሎችን፤ የመልከዓ ምድር መጠሪያ ስሞችን ...ወዘተ በማካተት በባለሙያዎች የሚዘጋጅ ነው።

ካርታዎች በሚዘጋጁበት መስፈርት፤ በሚይዟቸው ዝርዝር መረጃዎቻቸውና ጥቅማቸው የሚለያዩ ሲሆኑ በዚህም የተነሳ በተለያዩ ክፍሎች ይከፈላሉ። ለቆጠራ ካርታ ሥራ ዓላማ ሲባል የሚከተሉት የካርታ ዓይነቶችና የእያንዳንዱ ዓይነት መግለጫ ከ(ሀ-ሐ) እንዲሁም የካርታ ሥራ ጭብጦች ማብራሪያ ከ(መ-ከ) ተሰጥቷል።

ሀ. <u>የቶፖግራፊ ካርታ</u>:- የቶፖግራፊ ካርታ በመሬት ላይ ያሉትን ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ገጽታዎችን አቀማመጥ በአግድመትና በከፍታ ሊለካ በሚችል መልኩ የሚያሳይ ካርታ ነው። የከፍታ በታዎች አቀማመጥ ወይም /Relief/ በካርታው ላይ ኮንቱር በሚባሉ መስመሮች የሚታይ ነው።

ለቆጠራ ካርታ ሥራ አገልግሎት የሚከተሉትን ሦስት የካርታ መስፈርቶች እንጠቀማለን።

እነዚህም:- 1) ከፍተኛ መስፈርቶች:- 1:10,000 እና በላይ

2) መካከለኛ መስፈርት:- 1:20,000 እስከ 1:100,000

3) አነስተኛ መስፈርት:- 1:250,000 እና በታች

ለ. <u>የከተማ ካርታ</u>:- በከፍተኛ መስፈርት የተሰራ ሆኖ የጎዳናዎችን ስርጭትና የሕንጻዎችን አቀማመጥ እንዲሁም ጎልተው የሚታዩ ሌሎች ገፅታዎችን የሚያሳይ ካርታ የከተማ ካርታ ይባላል።

ሐ. <u>መነሻ ካርታ (BASE MAP)</u>:- መሠረታዊ የሆኑ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ገፅታዎችን የሚገልፁ መረጃዎችን የሚያሳይ እና ለሌላ የካርታ ሥራ እንደመነሻ የሚያገለግል ሆኖ በውስጡ ተጨማሪ መረጃዎችን ለማካተት የሚያስችል ማንኛውም ዓይነት ካርታ መነሻ /ቤዝ/ ካርታ ይባላል።

ለቆጠራ ካርታ ሥራ ሲባል ከላይ በ«ሀ» ና በ«ለ» የተጠቀሱት የካርታ ዓይነቶች በቂ ዝርዝር መረጃዎች እስካካተቱና የተሠሩበት መስፈርት ተስማሚ እስከ ሆነ ድረስ እንደ መነሻ/ቤዝ/ ካርታ ያገለግላሉ።

መ. <u>የካርታ ዝርዝር መረጃ</u>:- የካርታ ዝርዝር መረጃ ካርታው ተሻሽሎ በተሠራበት እና በተጠናቀረበት ቀን በመሬት ላይ የሚገኙትን የተለያዩ ገፅታዎች በካርታው ላይ የሚያሳይ መረጃ ነው። የግንባታና የማፍረስ ሥራዎች በየጊዜው የሚከናወኑ በመሆናቸው ቀደም ብሎ የተሠራ ካርታ በእነዚህ ለውጦች የተነሳ የወቅቱን የግንባታና የአሠፋፈር ገጽታዎች እንዳለ ላያንፀባርቅ ይችላል። ይህ ሁኔታ ደግሞ ከፍተኛ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ለውጦች በሚካሄዱባቸው አካባቢዎች በይበልጥ ይከሰታል። ይህንን ሁኔታ ለማስተካከል ሁል ጊዜ <u>የማጠቃለያና የማመላከቻ</u> ዘዴዎችን መጠቀም ይገባል።


ሠ. <u>ማጠቃለያ (Generalization)</u>:- በካርታ ውስጥ የሚካተት ዝርዝር መረጃ ብዛት በካርታው መስፈርት ይወሰናል። ካርታ ግልጽነቱ በማይጎዳ ሁኔታ የተቻለውን ያህል ዝርዝር መረጃ ማካተት ይኖርበታል። በተጠቀጠቀ የሰው ሠራሽ ገጽታዎች የተሞላ አካባቢ ካርታ ሲሰራለት ሁለንም ገጽታዎች በካርታው ውስጥ ማካተቱ የካርታውን ተነባቢነት ስለሚጎዳ በአንባራዊ አነጋገር የአካባቢውን ገፅታ በማያጓድል መልኩ ጥንቃቄ በማድረግ አነስተኛ የሆኑ ገጽታዎችን ከካርታው ማስወገድ ያስፈልጋል። ለምሣሌ ብዛት ያላቸው ጅረቶችና ሌሎች ተፈጥሮአዊ ገጽታዎች በሚገኙበት አካባቢ ለሚሠራ ካርታ አነስተኛ ጠቀሜታ ያላቸውን ጅረቶችና የተፈጥሮ ገጽታዎች በመተው ከፍያለ ጠቀሜታ ያላቸውንና በአካባቢው የሚታወቁትን ብቻ በካርታው ማካተቱ በቂ ይሆናል። የማጠቃለያው ሥራ ደረጃ ከሚሠራው ካርታ ሥራ ጥቅም ጋር የተያያዘ ነው።


ረ. <u>ማመላከቻ /Symbolization/</u>:- በመሬት ላይ የሚታዩትን ገጽታዎች በፊደል ወይም በቅርጽ በመወከል ውክልናው ምን እንደሚያመለክት በካርታ መግለጫ ማስቀመጥ የተለመደ የካርታ አሠራር ነው። በተለያየ መስፈርት የተሠራ የአንድ አካባቢ ካርታ የሚጠቀመው ማመላከቻ አንድ ዓይነት ነው። ነገር ግን የካርታው አጠቃቀም ለተለያየ ዓላማ በሚሆንበት ጊዜ ለማመላከቻ የሚያገለግሉት ምልክቶች በመጠኑም ቢሆን ሊለዋወጡ ይችላሉ። በካርታው ላይ የሚሰፍሩት የማመላከቻ ምልክቶች ከአቅጣጫዎች ጋር የተገናዘበ ማዕከላዊ ሥፍራና አቀማመጥ /ሰሜን ምሥራቅ፣ ደቡብና ምዕራብ/ በመሬት ላይ ከሚገኘው ተመሣሣይ የማዕከላዊ ሥፍራና አቀማመጥ ጋር የተጎዳኘ መሆን አለበት።

<u>የተለያዩ የምልክት ዓይነቶች</u>:-

i) <u>የነጥብ ምልክቶች</u>

ሀ. <u>ዓይነታዊ የነጥብ ምልክቶች</u>


ጂኦሜትሪያዊ 

ሥዕላዊ 

ፊደል Fe. Mg. C.S.A P.O.B PHCCO

ሥዕል 2.1ሀ


ለ. መጠናዊ የነጥብ ምልክቶች:-



ሥዕል 2.1ለ


ii) የመስመር ምልክቶች:-

ሀ. ዓይነታዊ የመስመር ምልክቶች



ሥዕል 2.2ሀ


ለ. መጠናዊ የመስመር ምልክቶች /ውፍረት/



ሥዕል 2.2ለ

iii) የስፋት ምልክቶች (Area Symbols):-

ሀ. ዓይነታዊ የስፋት ምልክቶች (Qualitative Area Symbols):-




Patttern

Screen

ሥዕል 2.3ሀ

ለ. መጠናዊ የስፋት ምልክቶች (Quantitative Area Symbols)



Screen


ሥዕል 2.3ለ

ሰ. ተፈጥሮአዊ ገፅታዎች (Physical Features):- ስለ መሬት ቅርጽና ገፅታ ካለው የመረጃ ብዛትና ጥራት የተነሳ የመሬት ቅርጽና ገፅታ ኮንቱር ተብለው በሚጠሩ የመሬት ገጽታ ማሳያ መስመሮች በካርታ ላይ እንዲታዩ ይደረጋል:: በተለያዩ መስፈርቶች የተዘጋጁ ካርታዎች ላይ ኮንቱር በመጠቀም ዋነኛ የመሬት ቅርጾችንና ገፅታዎችን በማየት በቂ መረጃ ማግኘት ይቻላል::

I. <u>ኮንቱሮች</u>:- በመሬት ላይ የሚገኙ የተለያዩ የተፈጥሮ ገፅታዎችን /ተራራ፣ ገደል፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ...ወዘተ/ ከባሕር ወለል በላይ ያላቸውን ተመሣሣይ የከፍታ ነጥብ በማገናኘት የሚያሳዩ በካርታ ላይ የሚሳሉ የሃሳብ መስመሮች ኮንቱሮች ይባላሉ። ለቆጠራ ካርታ ሥራ በአብዛኛው የሚያጋጥሙን በኖርማል ኮንቱሮች የተሠሩ ካርታዎች ናቸው።

<u>ኖርማል ኮንቱሮች</u>:- የካርታ ተጠቃሚውን ለመርዳት ሲባል ፣ካርታው ላይ ከሚሰመሩት መስመሮች መካከል እያንዳንዱ አምስተኛ የኮንቱር መስመር ወፈርና ደመቅ ያለ ነው። እነዚህ አምስተኛ መስመሮች አመልካች (Index) ኮንቱር ፣መባል ይታወቃሉ።ቀሪዎቹ መስመሮች ደግሞ መካከለኛ (Intermediate) ኮንቱር ይባላሉ። ከፍተኛ የመልክዓ ምድር /ቶፖግራፊ/ አቀማመጦች ባሉበት አንዳንድ ሥፍራዎች በካርታው ላይ በኖርማል ኮንቱሮች መካከል ያለው ስፋት (interval) ከፍ ያለ ሊሆን ይችላል። ይህ አንዳንድ የታወቁ መልክዓ ምድራዊ ገፅታዎችን በካርታው ላይ በትክክል ለማስፈር ስለሚያስችግር ተጨማሪ (Supplementary) ኮንቱሮችን በማስገባት የኮንቱር ስፋቱን ማጥበብ አስፈላጊ ይሆናል።


<u>ኖርማል ኮንቱሮች</u>



ሥዕል 2.4


II. <u>የኮንቱሮች ባሕሪያት</u>:- የኮንቱሮችን ባህሪያት በቅድሚያ መረዳት ኮንቱሮችን በትክክለኛ መንገድ ለመጠቀም ያስችላል:: ስለዚህ ዋና ዋና የኮንቱሮች ባህሪያት እንደሚከተለው ቀርበዋል::

1. ኮንቱሮች ያልተቆራረጡ ወጥ መስመሮች ናቸው::
2. ለኮንቱር መስመሮች የሚሰጠው ቁጥር ከባህር ወለል በላይ ከፍታን በመከተል ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ በመጨመር ነው:: የሚሰጡት የኮንቱር ቁጥሮች ከሚከተሉት ባንዱ መንገድ ሊሆን ይችላል::




ሥዕል 2.5

3. በኮንቱር መስመሮች መካከል ያለው ክፍተት ሠፊ ሲሆን መስመሮቹ የሚያመለክቱት ከፍታው በዝግታ የሚጨምር ዳገታማ ሥፍራን ነው::
4. በኮንቱር መስመሮች መካከል ያለው ክፍተት ጠባብ ከሆነ መስመሮቹ የሚያመለክቱት ከባድ ዳገትን ነው::



ሥዕል 2.6

5. ኮንቱሮች እርስ በእርስ አይተላለፉም:: እንዲሁም የኮንቱር መስመሮች ዥው ያለ ገደል ወይም ሏፏቴ ያለበት ቦታ ላይ ካልሆነ በስተቀር አይነካኩም::
6. የኮንቱር መስመሮች ከዥረቶች ጋር እና እርስ በርሳቸው ትይዩ የመሆን አዝማሚያ ያሳያሉ:: ይህ ደግሞ በመሬት ቅርጽ ላይ የሚታይ ለውጥ በአብዛኛው ዝግ ያለ መሆኑን የሚያመለክት ነው::
7. እያንዳንዱ የኮንቱር መስመር በሚታይበት ካርታ ላይ ወይም ከካርታው ውጭ ዙሮ ይገጥማል::
8. በማንኛውም ሁለት ተከታታይ ኮንቱሮች መካከል ያለው ርቀት መጠን /የተለየ መሆኑ ካልተጠቀሰ በስተቀር/ ተመሣሣይና እኩል ነው::




ሥዕል 2.7

በስዕል 2.7 እንደተመለከተው ሁሉ በማንኛውም ተከታታይ ኮንቱሮች መካከል ያለው ርቀት 100 ነው።

አሁን ደግሞ የሚከተሉት የመሬት አካሎች (/ኮረብታ፣ አምባ/Plateau/፣ ሏሏቴ፣ ስፐር፣ ሸለቆ፣ ገደል) በኮንቱር አማካይነት በካርታ ላይ እንዴት እንደሚታዩ እንመልከት።


<u>ኮረብታ /Hill/</u>:- ኮረብታ አንድ የመሬት አካል ሆኖ አካባቢው ካሉት የመሬት አካሎች ከፍ ያለ ቦታ ነው።



ሥዕል 2.8


<u>ሸለቆ (Valley)</u>:- በከፍተኛ ቦታዎች መካከል የሚገኝ የ"V" ቅርጽ ያለው ዝቅተኛ የመሬት አካል ነው።

<u>ስፐር (Spur)</u>:- በሸለቆዎች ወይም በወንዞች ዳር እና ዳር የሚገኝና ወጣ ብሎ የሚታይ የመሬት አካል ነው።




ሥዕል 2.9

<u>ገደል (Cliff)</u>:- ቀጥ ያለ የከፍተኛ መሬት አካል ገደል ይባላል። ቀጥ ያለ ከፍታ ያለውም ስፐር ገደል ነው። ገደል በካርታ ላይ የሚቀርበው ሰፊ መስመር በሚፈጥሩና መጨረሻ በሚገጥሙ ወይም በጣም በሚቀራረቡ ኮንቱሮች ነው።




ሥዕል 2.10

ፏፏቴ (Waterfall):- ወደ ሸለቆ ወይም ወደ መሬት ወለል ቀጥ ብሎ የሚወርድ ቅጽበታዊ የወንዝ ፍሳሽ ፏፏቴ ይባላል:: ኮንቱሮች ፏፏቴ ያለበት ቦታ ላይ ይገጥማሉ::



ሥዕል 2.11

አምባ (plateau):- ቀጥ ያለ ዳገት ያለው ከፍተኛ የመሬት ጫፍ ላይ የሚገኝ ሜዳማ የመሬት አካል አምባ ይባላል:: አምባ ላይ የቆሙ የተለያዩ ከፍታ ቦታዎች ሊኖሩ ይችላሉ::



ሥዕል 2.12

ሸ. ሰው ሰራሽ ገጽታዎች (Cultural features):- ሰው ሠራሽ ገጽታዎች በመሬት ላይ በሰው የተገነቡ የተለያዩ የግንባታ ሥራ ውጤቶች ናቸው:: ዋና ዋናዎቹ የሰው ሠራሽ ገፅታዎች የሚከተሉት ናቸው::

i) ከተሞች:- በአነስተኛ መስፈርት የተሰሩ ካርታዎች ላይ ከተሞች የሚመለከቱት በክብ ቅርጽ ነው:: የከተማ ሙሉ የስፋት መጠን ሊወከልባቸው በሚችሉ የከፍተኛ መስፈርት የተሰሩ ካርታዎች ላይ ግን የከተማ ካርታ የጎዳናዎችን ስርጭት ስርዓት የሚያመለክቱ መስቀልኛ መስመሮች አካቶ ሊዘጋጅ ይችላል:: ይህ የመንገዶች ሥርጭት ስርዓት ግን በመሬት ላይ ያለውን የመንገዶች ትክክለኛ አውታር ላያሳይ ይችላል::

ii) መንገዶች:- በጥንታዊ ካርታዎችም ላይ ቢሆን መንገዶችን በሁለት መስመሮች ማሳየት የተለመደ ነበር:: በከፍተኛ መስፈርት ካርታዎች ላይ ግን አነስተኛ መንገዶችን በማስቀረት ዋና ዋናዎቹን ብቻ በሁለት መስመሮች ሳይሆን በአንድ መስመር እንዲታዩ ይደረጋል::

iii) ሌሎች:- አብዛኛዎቹ የአነስተኛ መስፈርት ካርታዎች ከከተማዎች፣ ከመንገዶች፣ ከባቡር ሐዲዶችና ከወሰን ክልሎች ሌላ ምልክቶችን አያካትቱም:: በከፍተኛ መስፈርት ካርታዎች ላይ ግን እንደ ቤተክርስቲያኖች፣ ማዕድን ሥፍራዎች፣ ትምህርት ቤቶችና የመሳሰሉት ገፅታዎችን አግባብ ባላቸው ምልክቶች በተጨማሪነት ያካትታሉ::

ቀ. የካርታ መስፈርት:- የመሬት ገፅታ ትክክለኛ መጠን በካርታ ላይ በተመጣጣኝ መንገድ ለማስቀመጥ /ለመወከል/ የሚረዳ ዘዴ የካርታ መስፈርት ይባላል::

i) የካርታ መስፈርት ዓይነቶች

1. ወካይ ክፍልፋይ (Representative Fraction (RF)):- ይህ ቀላል ክፍልፋይ ወይም ረሽዮ የሆነ የመስፈርት መግለጫ ነው:: ወካይ ክፍልፋይ ለምሣሌ በ1:50,000 ወይም 1/50,000 የአፃፃፍ ዘዴ ሊገለፅ ይችላል:: ይህ ማለት አንድ ዩኒት በካርታ ላይ 50,000 ዩኒት በመሬት ላይ ይወክላል ማለት ነው::

2. በቃላት የሚገለፅ (Verbal Statement):- በካርታ ላይ ያለን ርቀት መሬት ላይ ካለ ርቀት ጋር በማዛመድ በቃላት የሚገለጽበት ዘዴ ነው:: ለምሳሌ 1:50,000 ወካይ ክፍልፋይ ተሰልቶ በቃላት ሲገለፅ "1 ሴንቲ ሜትር በካርታ ላይ 0.5 ኪሎ ሜትር በመሬት ላይ" ተብሎ ሊገለፅ ይችላል::

ማስታወሻ፡ 1ኪ.ሜ = 1000 ሜ፡ 1ሜ = 100 ሴ.ሜ


1ኪ.ሜ = 1000X100 = 100,000 ሴ.ሜ

ይህም 1ሴ.ሜ በካርታ ላይ 50,000 ሣ.ሜ በመሬት ላይ ይወክላል::

ስለዚህ 50,000/ (100 X1000) = 1/2 = 0.5 ኪ.ሜ

1ሳ.ሜ በካርታ ላይ 0.5 ኪ.ሜ በመሬት ላይ ይሆናል ማለት ነው::

3. <u>የግራፍ ወይም የባር መስፈርት</u>፡- በካርታ ላይ የሚቀርብ፤ በመሬት ርቀት መለኪያ የዩኒቶችን ርዝመት ለማሳየት የተሸነሸነ መስመር ነው። ይህ የባር መስፈርት የካርታ ተጠቃሚው ከቦታ ቦታ ያለን ርቀት በትክክል እንዲለካ ያስችለዋል።



መስፈርት 1:50,000

ሥዕል 2.13

<u>ሠንጠረዥ 2.1</u>፡- የተለመዱ የካርታ መስፈርቶች በካርታና በመሬት ላይ የሚወክሉት ተመጣጣኝ ርቀት መጠን፤

የካርታ መስፈርቶች	1ሣ.ሜ በካርታ ላይ	1ኪ.ሜ በመሬት ላይ
1:1000000	10 ኪ.ሜ በመሬት ላይ	1 ሚ.ሜ ካርታ ላይ
1:500000	5 ኪ.ሜ »	2 ሚ.ሜ »
1:250000	2.5 ኪ.ሜ »	4 ሚ.ሜ »
1:125000	1.25 ኪ.ሜ »	8 ሚ.ሜ »
1:100000	1 ኪ.ሜ »	1 ሣ.ሜ »
1:50000	0.5 ኪ.ሜ »	2 ሣ.ሜ »
1:25000	0.25 ኪ.ሜ »	4 ሣ.ሜ »
1:20000	0.2 ኪ.ሜ »	5 ሣ.ሜ »
1:10000	0.1 ኪ.ሜ »	10 ሣ.ሜ »
1:5000	50 ሜትር »	20 ሣ.ሜ »
1:2000	20 ሜትር »	50 ሣ.ሜ »

ii) <u>መስፈርት ስለመለወጥ</u>፡- ለቆጠራ ካርታ ሥራ ተስማሚ የሆኑ በባለከፍተኛ መስፈርት መነሻ/ቤዝ ካርታዎች በማይኖሩበት ጊዜ የተገኘውን የዝቅተኛ/መካከለኛ መስፈርት መነሻ/ቤዝ ካርታ ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ ሊገኝ ይችላል። ከዝቅተኛ/መካከለኛ መስፈርት ወደ ከፍተኛ መስፈርት ባደገው ካርታ ውስጥም ለቆጠራ ካርታ ሥራ ጠቃሚ የሆኑ ተጨማሪ ዝርዝር መረጃዎችን ማካተት ይችላል።

የመነሻ/የቤዝ ካርታው መስፈርት በተለያዩ የመስፈርት መለወጫ ዘዴዎች ሊለወጥ ይችላል። ከዘዴዎቹም መካከል ፕሮጀክሽኑ፤ ፎቶግራፌ፤ ፓንቶግራፊና ተመሳሳይ ስኳር (Similar Square) ይገኙባቸዋል። ለቆጠራ ካርታ ሥራው መስፈርት መለወጥ/ማሳደግ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከላይ ከተጠቀሱት ዘዴዎች ውስጥ የተመሣሣይ ስኳር (Similar Square) ዘዴ በጥቅም ላይ ይውላል።

የካርታ መስፈርት በተመሣሣይ ስኳር ዘዴ መለወጥ፡-

ይህ ዘዴ መስፈርቱ እንዲያድግ በተፈለገው ካርታ ላይ ያሉትን ግሪድ ስኳሮች የመምረጥ ከሌሉ የማስመርጎ፡ ጎንና ርዝመታቸውን የመለካትና ተመሳሳይ የሆኑ ነገር ግን ጎንና ርዝመታቸው በተፈለገ መጠን ያደጉ ስኳሮችን በማሳደጊያ ወረቀት ላይ መሣልን ያጠቃልላል።

በተመሳሳይ ዘዴ የካርታ ማሳደግ ተከታታይ ቅደም ተከተሎች፡

ስቴፕ 1፡- በሚያድገው ካርታ ላይ ወንፊት መልክ ያላቸው ስኳሮችን ሳል ወይም ምረጥ፤

ምሣሌ፡- 1ሴ.ሜ X 1 ሴ.ሜ ስኳሮች


ስቴፕ 2፡- በማሳደጊያ ወረቀት ላይ ተመሳሳይ ግን ከፍ ያሉ ወንፊት መልክ ያላቸው ስኳሮች ሥራ፤

ምሣሌ፡- 2ሴ.ሜ X 2ሴ.ሜ ስኳር

ስቴፕ 3፡- በሚያድገው ካርታ ላይ ያሉ ዝርዝሮችና ምልክቶች በከፍተኛ ጥንቃቄ አንፃራዊ ስፍራቸውን እንደያዙ ወደ ማሳደጊያው ወረቀት ላይ ማስመሪያና እርሳስ በመጠቀም አስተላልፍ።

የቆጠራ ቦታ ካርታን ለማሳደግ ባለ A4 ሚሊ ሜትር የግራፍ ወረቀት ይሰጣል። ስለ ካርታ ማሳደግ ስዕል 2.14 እና 2.15 በምሣሌነት ተመልከት።


የቆጠራ ቦታ ካርታ የመጀመሪያ መጠን



1:50,000

ስዕል 2.14

A4 መጠን ያለው የሚሊ ሜትር ግራፍ ወረቀት ላይ ያደገ የቆጠራ ቦታ ካርታ



1:25,000

ሥዕል 2.15

በ. <u>አቅጣጫ</u>፡- በመሬት ላይ ያሉ አቅጣጫዎች ሃሳባዊ ናቸው። ለዚህም ምክንያቱ የመሬት አፈጣጠር ድቡልቡል በመሆኑና መነሻና መድረሻ እንዲሁም ጠርዝ የሌለው በመሆኑ ነው። በመሠረተ ሃሳብ ደረጃ ሰሜን-ደቡብ ከሜሪዲያን መስመሮች ጋር ተዛማጅ ሲሆን ምስራቅ-ምዕራብ ደግሞ ከላቲቲዩድ ትይዩ መስመሮች ጋር ተዛማጅ ነው። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱ ሁለት አቅጣጫዎች ማለትም ሰሜን-ደቡብ እና ምስራቅ-ምዕራብ ከዋልታዎች አካባቢ በስተቀር ቀጥታ ተቋራጭ ናቸው። የሜሪዲያንና የላቲቲዩድ መሥመሮች ለኮምፓስ አቅጣጫዎች መሠረት ናቸው። በኮምፓስ ላይ የሚታይ አቅጣጫ ከእውነተኛው አቅጣጫ በመጠኑ ይለያልና ምክንያቱም ኮምፓስ ሙሉ በሙሉ የማግኔት ውጤት ስለሆነ በማግኔት ላይ የሚገኝ የሰሜን-ደቡብ አቅጣጫ ከሜሪዲያን መስመሮች ጋር ሙሉ በሙሉ ትይዩ አይሆንም።

ተ. <u>የካርታ የጎን መረጃ</u>፡- የካርታ የጎን መረጃዎች በካርታው ጎኖች የሚገኙና ካርታውን በሚገባ ለመረዳት የሚረዱ ናቸው። የካርታ የጎን መረጃዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ፡-

i. <u>ርዕስ</u>፡- የካርታው ርዕስ በካርታው የሚታየውን አካባቢ ስምና በካርታው ማሳየት የተፈለገውን ጉዳይ ማመልከት ይኖርበታል።

ii. <u>መስፈርት</u>፡- የካርታው መስፈርት ምን ያህል እንደሆነ መገለጽ ይኖርበታል። መስፈርቱ በአህዝ እና በግራፍ መልክ ቢጠቀስ የበለጠ ጠቃሚ ይሆናል።

iii. <u>ሰሜናዊ አቅጣጫ</u>፡- የካርታው ሰሜናዊ አቅጣጫ በቀስት መታየት ይኖርበታል። ምንም እንኳን የሰሜናዊ አቅጣጫውን በካርታው አናት አካባቢ ማሳየት የተለመደ ቢሆንም በወረቀቱ ላይ የካርታው አቀማመጥና የመረጃዎች አሠፋፈር የሰሜን አቅጣጫን ያመለክታል።

iv. <u>መግለጫ</u>፡- የካርታው መግለጫ ወይም መፍቻ በካርታው ውስጥ የሠፈሩትን ምልክቶችና ምሕጻረ ቃሎች በሙሉ በሚያስረዳ መንገድ መዘጋጀት ይኖርበታል።

v. <u>ተጨማሪ ካርታ</u>፡- አንድ የተወሰነ የጥናት አካባቢን ጂኦግራፊያዊ አቀማመጥ በአንድ አነስተኛ መጠን ያለው የሀገር ካርታ ውስጥ የሚያሣይ ካርታ ነው። ይህ ካርታ በአንድ ሀገር ውስጥ የአንድን አካባቢ አንፃራዊ ሥፍራና አቀማመጥ ለማሣየት ይረዳል።


vi. <u>አመልካች/ጠቋሚ ካርታ</u>፡- አንዳንድ ጊዜ አንድን አካባቢ በአንድ የካርታ ወረቀት ብቻ ማስፈር ያዳግታል። ስለዚህ አካባቢውን ሙሉ በሙሉ ማስፈር የሚቻለው በተለያዩ ወረቀቶች ላይ ይሆንና ትክክለኛውን የአካባቢውን ስዕል ለማየት የተለያዩትን ወረቀቶች ማገጣጠም ያስፈልጋል። ካርታዎችን በቀላሉ ለመለየትና በትክክል ለማገጣጠም እንዲረዳ በያንዳንዱ ወረቀት ላይ የወረቀቶቹ

ተከታታይ ቁጥር፤ የወረቀት ቁጥር፤ የትኛው ወረቀት ከየትኛው ወረቀት በየትኛው አቅጣጫ እንደሚከተል የሚያመለክት መለያ ቁጥር፤ ወዘተ የሚያሳይ መረጃ አመልካች/ጠቋሚ ካርታ ይባላል።

ቸ. <u>ስፋትን በስኴር ዘዴ መገመት</u>፡- የተስተካከለ ቅርጽ የሌላቸውን ካርታዎች ስፋት በስኴር ወረቀት ቢመጠቀም ለመገመት የስኴር ዘዴ ቀላሉና ከስፋት መገመቻ ዘዴዎች አንዱ ነው። ስፋቱ ሊገመትለት የታሰበው ካርታ መስፈርት ከታወቀና ትክክለኛ የስኴር ወረቀት ካለ የስፋት ግምት በአጥጋቢ መንገድ ሊሰላ ይችላል።

የሚከተሉት ተከታታይ የአሰራር ቅደም ተከተሎች የአንድን ቆጠራ ቦታ ስፋት ለመገመት ያስችላሉ።

1. ስፋቱ ሊገመትለት የታሰበውን የአስተዳደር አካል ወይም የቆጠራ ቦታ ድንበር ብርሃን በሚያሳልፍ ወረቀት (Tracing paper) ላይ መሣል፤
2. ድንበር የተሣለበትን ወረቀት በግራፍ ወረቀት ላይ መደረብ፤
3. በድንበሩ ውስጥ የሚገኙ ሙሉና ባለ 1ሣ.ሜ ስኴሮችን መቁጠር፤
4. በድንበሩ ውስጥ የሚገኙ ግማሽና በላይ ስኴሮችን መቁጠር፤
5. ከላይ በተራ ቁጥር (3) እና (4) የተገኙትን ስኴሮች ቁጥር በመደመር ውጤቱን በካርታው መስፈርት ማባዛት። ይህ ውጤት የቆጠራ ቦታውን ስፋት ግምት ይሰጣል።



ሥዕል 2.16

<u>ለምሳሌ</u>፡- ከዚህ በላይ የቀረበው ስዕል በድንበሩ ውስጥ 16 ሙሉ ስኴሮችና 10 ግማሽና በላይ ስኳሮች ካሉ በድምሩ 26 ስኴሮች አሉ ማለት ነው። የካርታው መስፈርት 1:50000 ቢሆን፤ ይህ መስፈርት ወደ ኪ.ሜ ሲለወጥ፡-

50000/(100 X 1000) = 1/2 ኪ.ሜ ይሆናል::

ይኸውም:- 1ሳ.ሜ = 1/2 ኪ.ሜ

1ሳ.ሜ ስኳር = 1/4 ኪ.ሜ ስኳር

26 ሳ.ሜ ስኳር ወደ ኪ.ሜ ስኳር ሲለወጥ

26 X 1/4 = 6.5 ኪ.ሜ ስኳር

ይህ የቆጠራ ቦታው ስፋት ግምት በመሬት ላይ ይሆናል::

2.2.2 <u>የካርታ አነባበብ ቅደም ተከተሎች</u>

ካርታን በሚገባ ለማንበብና ለመረዳት ጥንቃቄ የተሞላበት ጥናትና የማገናዘብ ችሎታ ያስፈልጋል:: መጠነኛ የጂኦግራፊ ዕውቀት ያለውና ጠለቅ ያለ ትኩረት የሚያደርግ ሰው የተለያዩ እውነታዎችን ከካርታ ላይ ማንበብ ይችላል:: "ካርታን በሚገባ መረዳት መጽሐፍን የማንበብን ያህል ነው" የሚል አባባል አለ:: ስለዚህ ካርታን ለማንበብ የሚከተሉትን ቅደም ተከተሎች መከተል ያስፈልጋል::

ሀ. የሚነበበውን ካርታ በጠረጴዛ ላይ ወይም መሬት ላይ ዘርግተህ አስቀምጥ፤

ለ. የቆምክበትን ሥፍራ የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ በመውሰድ በመነሻ ካርታ ላይ አስፍር፤

ሐ. በካርታው ላይ ያሉት ዝርዝር መረጃዎች አቀማመጥ (ለምሳሌ. ተራራ፤ መንገድ) በመሬት ላይ ካላቸው አቀማመጥ ጋር ትይዩ እንዲሆን አድረግ፤

መ. የጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያውን የቦታ ገፅ በመጠቀም እና መሣሪያውን ይዘህ በመንዝ ሰሜናዊ አቅጣጫን አገናዝብ:: የጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያው በቦታ ገጹ አናት ላይ የምትንዝበትን አቅጣጫ በቁጥር ይገልፃል:: ስለዚህ ሰሜንን ለማግኘት መሣሪያውን ይዘህ ስትንዝ በገፁ እናት ላይ መሣሪያው 0° እስኪያነብ ድረስ አቅጣጫህን በመቀያየር መንዝ ይኖርብሀል:: መሣሪያውን ይዘኸው ካልተንዝክ በስተቀር አንድ ቦታ ብትቆም አቅጣጫዎችን ሊያነብልህ እንደማይችል መገንዘብ ይኖርብሀል:: (ዕዝል I ሥዕል 2 እና 4 ተመልከት)

ሠ. የሰሜን አቅጣጫን ካገናዘብክ በኋላ ሌሎችን አቅጣጫዎች በተመሣሣይ መንገድ አገናዝብ:: በመሣሪያው የቦታ ገፅ አናት ላይ ለምሥራቅ 90°፤ ለደቡብ 180° እና ለምዕራብ 270° እስክታነብ ድረስ አቅጣጫህን በመቀያየር መንዝ ይኖርብሃል ማለት ነው::

ረ. በአካባቢው የሚገኙ በግልፅ የሚታወቁ ገፅታዎችን (መንደሮች፤ ቤተ ክርስቲያን፤ የገበያ ቦታ ...ወዘተ) በመለየትና የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ በመውሰድ በመነሻ ካርታው ላይ አስፍር::

ሰ. ለይተህ ያስፈርካቸው ገፅታዎች በትክክል መለየታቸውንና መቀመጣቸውን አረጋግጥ፤

ሸ. በካርታው መስፈርት መሠረት ርቀቶችን ገምት፤

ቀ. በካርታው መፍቻ መሠረት በመሬት ላይ የሚገኙ ዝርዝር መረጃዎችን በሚገባ ለይ፤

በ. በካርታው ላይ ያልሰፈሩ ነገር ግን በአካባቢው የተሰሩ ግንባታዎች ካጋጠመህ ካርታው የተሠራበትን ቀን ተመልከት፤

ተ. ስለአካባቢው መረጃ ለማግኘት የአካባቢውን ሰዎች (አርሶ አደሮች/እረኞች) ከመጠየቅ ወደኋላ አትበል፤

ቸ. ሰዎች አካባቢያቸውን ጠንቅቀው ስለሚያውቁ ስለቦታ ስሞች ስትጠይቅ መሪ ጥያቄዎች(Leading Questions) በማቅረብ ፋንታ አውጣጭ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መልስ አግኝ፤

ኀ. ከአንድ በላይ ስሞች ያላቸው ቦታዎችና የተፈጥሮ ገፅታዎችን በሚገባ ለይ፤

ነ. የአስተዳደር ድንበሮችን የጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያህን በመጠቀም በሚገባ ለይ። የበለጠ እርግጠኛ ለመሆን የአካባቢውን ባለሥልጣናትና አካባቢውን ጠንቅቀው የሚያውቁ ሰዎችን ጠይቅ።

<u>ማስታወሻ</u>፡-

1. በመነሻ ካርታነት እየተጠቀምክበት ያለው ካርታ የተገጣጣሚ ካርታዎች ማውጫ (Index) ከሌለው፤ የሎንግቲዩድና ላቲቲዩድ፤ የግሪድ መስመሮች ወይም የካርታ ዝርዝር መረጃዎችን በመጠቀም ካርታዎችን ማገጣጠም ትችላለህ።

2. የቦታ ስሞች በካርታ ላይ ሲፃፉ በሰሜን አቅጣጫ ትይዩ መፃፍ የተለመደ አሠራር ነው። ካርታው የሰሜን አቅጣጫ ምልክት (North Arrow) ከሌለው የዝርዝር መረጃዎችን አፃፃፍ በመከተል የሰሜን አቅጣጫን ማግኘት ይቻላል።

3. ከላይ በተጠቀሰው ዘዴ የሰሜን አቅጣጫ ማግኘት ካልተቻለህ የፀሐይን መውጫና መጥለቂያ አቅጣጫ (ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ) በመከተል የሰሜንና ደቡብ አቅጣጫ በግምት ማግኘት ይቻላል።

4. የአካባቢ ስሞች አጠያየቅ ጥሩ የሚሆነው ከአንድ የተወሰነ ቦታ በመነሳት የጥምዝምዞሽ አካሄድን በመከተል ይሆናል።

ምዕራፍ ሶስት

3. የጂ.ፒ.ኤስ (GPS) አጠቃቀም

3.1 መግቢያ

የቆጠራ ካርታ ሥራን በበቂ እውቀትና በአስተማማኝ መንገድ ለማከናወን እንዲረዳ የጂ.ፒ.ኤስ (Global positioning system) መሠረታዊ ሃሣቦችና የጀርሚን II^{+}/12 ጂ.ፒ.ኤስ መቀበያ መሣሪያዎች አጠቃቀም በስፋት ይብራራል። ስለዚህ እያንዳንዱ የካርታ ሠራተኛ በካርታ ሥራ ወቅት ለሚያከናውነው የእለት ከእለት ተግባር የጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያ አጠቃቀምን ጠንቅቆ ማወቅ ይኖርበታል።

3.2 ጂ.ፒ.ኤስ (GPS) ምንድነው?

ጂ.ፒ.ኤስ ማለት ምድርን በቀን ሁለት ጊዜ የሚዞሩና መረጃዎችን ወደ መሬት የሚያሰራጩ ከ24 በላይ ሣተላይቶችን የያዘ ሲስተም ነው።

የጂ.ፒ.ኤስ መቀበያ መሣሪያዎች /Receivers/ በአሜሪካ መንግሥት (USA) የመከላከያ ዲፓርትመንት (መ/ቤት) አማካይነት ወደ ጠፈር በተላኩና ምድርን በሚዞሩ ከ24 በላይ ሳተላይቶች የሚልኳቸውን መልዕክቶች (Signals) በመቀበል በመሬት ያለን የአንድ ነጥብ ቦታ (position) በትክክል ለማመልከት የሚረዳ መሣሪያ ነው። የጂ.ፒ.ኤስ መረጃ መቀበያ መሣሪያዎች (Receivers) የሣተላይት መረጃውን ከተቀበሉ በኋላ የአንድን ሥፍራ ከምድር ወገብና ከመካከለኛ ሜሪዲያን ርቀት (Positioning) ላቲትዩድና ሎንግቲዩድ ለማወቅና ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ አስቀድሞ በታወቁና በተለዩ አቅጣጫዎች ለመጓዝ (NAVIGATION) ያስችላሉ። በአሁኑ ጊዜ የመሣሪያዎቹ ጠቀሜታ እየጐላ በመምጣቱ ለሲቪል አገልግሎቶች (ለቆጠራ ካርታ ሥራ፣ ለመዝናኛ፣ ለንግድ ... ወዘተ) መዋል ጀምረዋል።

በመሠረቱ ጂ.ፒ.ኤስ በማንኛውም ሥፍራ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። ነገር ግን በምድር ዋልታዎች አካባቢና የሣተላይት መልዕክቶችን ለመቀበል በማይቻልባቸው ቦታዎች ለምሳሌ በህንፃዎች፣ በዋሻዎችና በባሕር ውስጥ የጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያን መጠቀም አይቻልም።

ለቆጠራ ካርታ ሥራ አገልግሎት ስለሚውሉት GARMIN GPS II^{+}/12 መሣሪያዎች ባህሪያትና አጠቃቀማቸውን በተመለከተ ዘርዘር ያሉ መሠረተ ሀሳቦች ከዚህ በታች ቀርበዋል።

የGPS II⁺/12 መሣሪያዎች በጠፈር ላይ መሬትን ከሚዞሩ 24 ሣተላይቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር የሚሠሩ ናቸው። የእነዚህም ሣተላይቶች ግልጋሎት የአንድን ነጥብ ቦታ በመሬት ላይ ለማመልከት የሚያስችሉ የሬዲዮ ግንኙነት (Radio Signals) መፍጠር ነው። በእነዚህም Radio Signals አማካኝነት በመጠቀም የአንድን ነጥብ ቦታ የላቲቲዩድና ሎንግቲዩድ ንባብ መፈለግ ይቻላል።

በጀርሚን ጂ.ፒ.ኤስ II⁺/12 መሣሪያዎች የሚሰበሰበው መረጃ አስተማማኝነት በሣተላይቶች አማካኝነት በሚፈጠረው የሬዲዮ ግንኙነት (Radio Signals) ጥንካሬና ደካማነት የተወሰነ ነው። በተጨማሪም የዚህ መሣሪያ መረጃ አስተማማኝነት በ15 ሜትር ርቀትና በ49 ጫማ ከፍታ የተወሰነ ነው።

የአንድ ነጥብ ቦታ የላቲቲዮድ፣ የሎንግቲዮድ እና ከፍታ (Latitude, Longitude & Altitude) ንባብ ጥሩ ነው የሚባለው የሬድዮ ግንኙነቱ በጣም ጠንካራ ሲሆን ነው። ይህም ማለት የጀርሚን ጂ.ፒ.ኤስ II⁺/12 መሣሪያዎች 3 ወይም/ እና ከዚያ በላይ በሕዋ ላይ ካሉት ሣተላይቶች ጋር ግንኙነት ከፈጠሩ ነው።

በጀርሚን ጂ.ፒ.ኤስ II⁺/12 መሣሪያዎች የተሰበሰበው መረጃ፡-

- የአስተዳደርና የቆጠራ ክልሎችን ድንበር ለመከለል፣
- በቆጠራ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሰውሰራሽና ተፈጥሮአዊ ቦታዎችን አንፃራዊ ሥፍራ (Location) በሎንግቲዮድና ላቲቲዩድ ለማወቅ፣
- በዚህም የቆጠራ ቦታ ካርታ ክልሎችን ውስጣዊ ይዘትና ድንበር በእርግጠኝነት በመነሻ ካርታ (Base Map) ላይ ለማስፈርና
- በተጨማሪ ለቦታዎች በተሰበሰቡት የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔት ንባቦች ላይ ተመስርቶ በGIS (Geographic Information System) የቆጠራ ውጤቶችን በመተንተን እና ከካርታዎች ጋር በማጣመር የአትላስ ካርታዎችን ለማዘጋጀት ያስችላል። እነዚህም የአትላስ ካርታዎች ለተጠቃሚ ግልፅና ከፍ ያለ ተነባቢነት ያላቸው መረጃዎችን ይዘው ስለሚዘጋጁ ጠቀሜታቸው ጉልህ ነው።

በቆጠራ ካርታ ሥራ ወቅት በመሬት ላይ የሚገኙ ቦታዎች በካርታ ላይ ያላቸውን አንፃራዊ ሥፍራ ለመወሰን በላቲቲዩድና ሎንግቲዩድ ምትክ የምንጠቀመው የዩ.ቲ.ኤም /UTM/ (Universal Transverse Mercator) ኮኦርዲኔቶችን ይሆናል። በጀርሚን ጂ.ፒ.ኤስ II⁺/12 መሣሪያዎች ላይ እነዚህ ኮኦርዲኔቶች "ምሥራቃዊ" ("Eastings") (ምሥራቅ-ምዕራብ) እና "ሰሜናዊ" ("Northings") (ሰሜን-ደቡብ) በሚል መልክ ይነበባሉ።

3.3. የጂ.ፒ.ኤስ መቀበያ መሣሪያ ደካማ ጎኖች

አጠቃላይ ደካማ ጎኖች፡- የጂ.ፒ.ኤስ አገልግሎት በአንዳንድ አካባቢዎችና አጠቃቀሞች የተወሰነ ነው። በከተሞች እና ጥቅጥቅ ያለ ደን ባላቸው አካባቢዎች ዋናው ችግር የጂ.ፒ.ኤስ መልዕክቶችን (Signals) የመቀበል አስቸጋሪነት ነው። ይህም የሆነው አንድ በትክክል የሚሠራ የጀርሚን ጂ.ፒ.ኤስ መልእክት መቀበያ መሣሪያ ቢያንስ ከአራት ሣተላይቶች ጥርት ያለና ያልተዛባ መልእክት መቀበል ስለሚኖርበት ነው። እነዚህ መልእክቶች (Signals) ውሃን፡ አፈርን፡ ግድግዳን፡ ሰንጥቀው ማለፍ ካለመቻላቸውም በተጨማሪ በድልድዮች፡ ህንፃዎችና በመጠኑም ቢሆን በደን ሽፋን ሳቢያ አቅጣጫቸው ሊዛባ መቻሉ ሊላው ደካማ ጎናቸው ነው። ጥርት ያለና ያልተዛባ ንባብ ለማግኘት ከእነዚህ አካባቢዎች ገለጥ ያለ ቦታ በመፈለግ በመሣሪያው ምልክቶች ን መቀበል ያስፈልጋል።

የጀርሚን ጂ.ፒ.ኤስ II$^+$/12 መቀበያ መሣሪያዎች ካሉት ደካማ ጐኖች ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉትን ናቸው:-

- በአራት A.A መጠን አልካላይን ባትሪ ድንጋዮች እስከ አንድ ሣምንት ብቻ ስለሚያገለግል የባትሪ ድንጋይ ወጪ ማብዛት፡
- ከ10 እስከ 20 ሜትር ድረስ ስህተት ሊፈጥሩ ስለሚችሉ የአንድን ነጥብ ቦታ በቀላሉ በመነሻ ካርታ (Base Map) ላይ በእርግጠኝነት ለማስፈር ከባድ መሆኑ፡

3.4. የጂፒኤስ መቀበያ መሣሪያ መሠረታዊ ባህሪያትና አጠቃቀም

የጀርሚን ጂ.ፒ.ኤስ II$^+$/12 መሣሪያ በዛ ያሉ ባህሪያት (features) አሉት። ነገር ግን ለቆጠራ ካርታ ሥራ መሠረታዊ የሆነና አጠቃቀማቸውን በደንብ ማወቅ የሚገባን ባህሪያት (features) የሚከተሉት ናቸው።

- የጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያውን ኃይል እንዲያገኝ ማድረግ (Powering the receiver)፡
- የጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያውን ፕሮግራም ማድረግና ለስራ ማዘጋጀት (Programming and Initializing the receiver)፡
- የሳተላይት ገፅ (Satellite page)፡
- የነጥብ ቦታ ገፅ (position page)፡
- ዩቲኤም ኮኦርዲኔቶችን ማስፈር (Plotting UTM coordinates)፡

3.4.1 <u>የመቀበያ መሣሪያውን ኃይል እንዲያገኝ ማድረግ፡ (Powering the receiver)</u>፡-

የጀርሚን ጂ.ፒ.ኤስ II⁺/12 መቀበያ መሣሪያዎች አራት ባለ AA መጠን አልካላይን ባትሪ ድንጋይ በአንድ ጊዜ ይጠቀማል። ባትሪ ድንጋዮችን ወደ መሣሪያው ለመጨመር መጀመሪያ የባትሪውን መክደኛ በመክፈት ሁለት የባትሪ ድንጋይ ማስገቢያ ቀዳዳዎች ከፖዘቲቭ (+) እና ኔጋቲቭ (-) ምልክቶቻቸው ጋር ይገኛሉ። ስለዚህ የፖዘቲቭ (+) ምልክት ባለበት ቀዳዳ ሁለት ባትሪ ድንጋዮችን፡ የባትሪ ድንጋዮቹን የ(+) ምልክት ወደ ላይ (ውጪ) አድርጎ መጨመር፡ የኔጋቲቭ (-) ምልክት ባለበት ቀዳዳ ደግሞ የሁለቱን ባትሪ ድንጋዮች የ(-) ምልክት ወደ ላይ (ውጪ) አድርጎ መጨመርና መክደን ያስፈልጋል። (ሥዕል 3.1 ተመልከት)

ሥዕል3.1 የጂፒኤስ መሣሪያ የባትሪ ድንጋዮች አገባብና አቀማመጥ



ሥዕል 3.1

<u>ማሳሰቢያ</u>፡- ትክክለኛ ያልሆነ የበትሪ ድንጋዮች አቀማመጥ በተጠቃሚው ሰው ላይ አደጋ እና በመሣሪያው ላይ ውድመት ያስከትላል። ስለዚህ የባትሪ ድንጋዮች በሚጨመሩበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ተገቢ ነው።

አራቱም ባትሪ ድንጋዮች በተገቢው ቦታ መግባታቸውን ካረጋገጡ በኋላ በባትሪ ድንጋዩ መክደኛ ላይ የምትገኘውን ቀለበት በመያዝ ወደታች ተጭኖ ወደ ቀኝ በማዞር መግጠም ያስፈልጋል። የመሣሪያውን የባትሪ ድንጋዮች መሸፈኛ ለመክፈት በመሣሪያው የታችኛው አካል ላይ የሚገኘውን ቀለበት በመያዝ ወደ ታች ተጭኖ ወደ ግራ በማዞር መክፈት ይቻላል።

ባትሪ ድንጋዮቹን ለመቆጠብ እንዲረዳ መሣሪያው በሥራ ላይ ካልሆነ ማጥፋት (turned off) ያስፈልጋል። ሁል ጊዜ ተለዋጭ ባትሪ ድንጋዮችን ይዞ መገኘት ተመራጭ ነው። ምክንያቱም "Battery Power is low" የሚል ምልክት በScreen ላይ ስናይ አሮጌውን ባትሪ ድንጋይ በማውጣት አዲሱን ባትሪ ድንጋይ መተካት ያስችለናል። ሆኖም ግን የባትሪ ድንጋዮን ኃይል ለመቆጠብ መሣሪያውን ስናጠፋ ባትሪ ድንጋዮን ከውስጡ ማውጣት አስፈላጊ አይደለም።

መሣሪያውን ለማብራት (on) እና ለማጥፋት (off) በመሣሪያው ላይ የሚገኘውን ቀይ የአምፑል ምልክት ያለበት ቁልፍ (button) መጫን ያስፈልጋል። መሣሪያውን ለማብራት ይህንን ቁልፍ ስንጫን በscreen ላይ የእንኳን ደህና መጡ "Welcome" መልዕክት እናያለን። መሣሪያውን ለማጥፋት ግን ይህንን ቁልፍ (button) ለ3 ሴኮንዶች ያህል ተጭኖ መቆየት ያስፈልጋል።

3.4.2 <u>የመቀበያ መሣሪያውን ፕሮግራም ማድረግ እና ለሥራ ማዘጋጀት (Programming and Initializing the Receiver)</u>

በጀርሚን ጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያ መረጃዎችን የመሰብሰብ ሥራ ከመጀመሩ በፊት መሣሪያው፦

ሀ. ፕሮግራም (Program) እና

ለ. ለኢትዮጵያ በሚያመች መልኩ ለሥራ ዝግጁ (Initialize) መደረግ አለበት። እነዚህ ተግባራት የሚከናወኑት መሣሪያውን ለመጀመሪያ ጊዜ የምንጠቀምበት ከሆነ ብቻ ነው። መሣሪያውን በተከታታይ ጥቅም ላይ አውለነው ከሆነ ግን እነዚህ ተግባራት በተደጋጋሚ አይከናወኑም።

መሣሪያውን በአግባቡ ለመጠቀም ፕሮግራም ማድረግና ለሥራ ዝግጁ ማድረግ በጣም አስፈላጊ ስለሆኑ በደንብ መታወቅና መጤን ይገባቸዋል። በሥራችን ወቅት ሥህተት እንዳይፈጸም የሚከተሉትን የአሠራር ቅደም ተከተሎች ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል።

ሀ. የመቀበያ መሣሪያውን ፕሮግራም ማድረግ (Programming the Receiver)

በመጀመሪያ ልናደርግ የሚገባን መሣሪያውን ፕሮግራም ማድረግ ነው። መሣሪያውን ካበራን (on) በኋላ እንኳን ደህና መጡ "Welcome" የሚል መልዕክት በScreen ላይ ይመጣል። ከዚያም ወዲያውኑ ይህ Screen ወደ ሳተላይት ገፅ (ሁለት ትንሽና ትልቅ ክቦች (circles) የያዘ ገፅ) ይለወጣል። የሳተላይት ገጽ የትኛው እንደሆነ ለማወቅ ዕዝል I ተራ ቁጥር 1 ተመልከት በዚህ ጊዜ Quit የሚለውን ቁልፍ (key) በመጫን የዋናው ገፅ (Main Menu) ማለትም በዕዝል I ሥዕል 5 ላይ የተመለከተው ገጽ እንዲመጣ ማድረግ ያስፈልጋል። በዚህ ገፅ ላይ ከሚገኙት ዝርዝሮች ውስጥ 'Setup menu' በመምረጥ 'Enter' በመጫን 'System menu' የያዘው ዝርዝር ይመጣል። ከእነዚህ ዝርዝሮች ውስጥ መጀመሪያ 'System Setup' ቀጥሎ 'Navigation setup' በሚከተለው ቅደም ተከተል ፕሮግራም ይደረጋሉ።

i. System Setup

(Setup Menu) ላይ እንዳለን የላይ ወይም የታች አቅጣጫ (up-down arrows) ቁልፍ በመጫን System የሚለው ላይ ስንደርስና ሲያቀልመው "Enter" የሚለውን ቁልፍ መጫን ያስፈልጋል። በዚህ ጊዜ ወዲያው System setup የሚል ገፅ ይመጣል። እዚህ ገፅ ላይ የምናገኛቸው Mode, Time, Date, Offset, Hours, Contrast እና Light ናቸው።

እያንዳንዱን ለመምረጥ የላይ ወይም የታች አቅጣጫ (Up-down arrow) ቁልፎችን መጫን፣ ከዚያም "Enter" ቁልፍ መጫን ያስፈልጋል። በዚህ ጊዜ በውስጣቸው ያሉትን ዝርዝሮች ማየት እንችላለን። አሁንም የላይ ወይም የታች አቅጣጫ (up-down arrow) ቁልፎችን በመጫን የምንፈልገው ዝርዝር ላይ ስንደርስና ሲያቀልመው "Enter" ቁልፍ በመጫን የምንፈለገውን እንመርጣለን። በዚህ መሠረት ከMODE በመጀመር ከላይ የተዘረዘሩትን በሙሉ ፕሮግራም ማድረግ ያስፈልጋል።

MODE:- በመስክ ሥራ ወቅት 'NORMAL' የሚለው የካርታ ስራ መረጃዎችን ለመሰብሰብ የምንጠቀመው ነው። በMODE ሥር 'SIMULATOR' እና 'POWER SAVE' የሚባሉ አማራጭ ቢኖሩም ለካርታ ሥራ አንጠቀምባቸውም።

DATE & TIME:- ቀንና ሰዓትን በተመለከተ ምንም ማስተካከያ አይደረግም።

OFFSET:- ይህ ለኢትዮጵያ +03 ላይ መስተካከል ይኖርበታል።

HOURS:- ሰዓትን በ'AM' ወይም 'PM' ወይም (24 hours) ፕሮግራም ማድረግ ይቻላል።

CONTRAST:- ይህ የመሣሪያው ስክሪን ለዓይናችን ግልጽ በሆነ መንገድ እንዲታይና መረጃዎችን በጉልህ ማንበብ እንዲቻለን የሚረዳ ነው። በተሰጠው አግድመት በተቀመጠ ስኬል ባር ላይ የግራና ቀኝ አቅጣጫ ቁልፎችን በመጠቀም ስክሪኑን ማጥቆርና ማንጣት ይቻላል። ወደ ቀኝ በContrast Scale Bar ላይ በአቅጣጫ ቁልፎች በመታገዝ ስንሄድ ኮንትራስት ይጨምራል (ስክሪኑ ይነጣል)፡ መረጃዎች በጉልህ ይታዩናል ማለት ነው። በአብዛኛው ግማሽ ወይም በስኬልባሩ ሁለት ሦስተኛው ላይ ብናደርገው ጥሩ ነው።

LIGHT:- ይህ በ15 Sec ላይ መስተካከል አለበት።

ii. NAVIGATION SETUP:- የመጀመሪያውን ፕሮግራም የማድረግ ተግባር እንደጨረስን 'QUIT' የሚለውን ቁልፍ ብንጫን ወደ 'Setup menu' ገፅ መልሶ ይወስደናል። በመቀጠልም የላይና ታች አቅጣጫ ቁልፎችን በመጠቀም 'NAVIGATION' የሚለውን መርጠን 'ENTER' ቁልፍ ስንጫን በNAV Setup ገፅ ላይ የሚከተሉት ይገኛሉ። POISTION FORMAT (THE Co-ordinate system), MAP DATUM, CDI SCALE, UNITS AND HEADING. በመቀጠልም 'ከ Position Format' በመጀመር ከላይ ለተዘረዘሩት ሁሉ አስፈላጊ የፕሮግራም ማስተካከያ ይደረግላቸዋል።

POSITION FORMAT: ለዚህ UTM/UPS የሚለውን መርጠን 'ENTER' የሚለውን ቁልፍ እንጫናለን። በዚህ ሥር ያሉ ሌሎች አማራጮችን ለካርታ ሥራ አንጠቀምባቸውም።

MAP DATUM:- ለዚህ "ADINDAN" የሚለውን መርጠን 'ENTER' ቁልፍ እንጫናለን። ከ 'ADINDAN' በስተቀር ሌሎች አማራጮች በካርታ ሥራ አንጠቀምባቸውም ።

CDI SCALE:- ይህ በ0.25 ላይ መስተካከል ይኖርበታል።

UNITS:- በሚለው ሥር ደግሞ "METRIC" የሚለውን መርጠን 'ENTER' ቁልፍ በመጫን እንመርጣለን። በዚህ ሥር ያሉ ሌሎች አማራጮች ለካርታ ሥራ አንጠቀምባቸውም።

HEADINGS:- ለዚህ ምንም ማስተካከያ አይደረግም።

ይህንን እንደጨረስን "PAGE" የሚለውን ቁልፍ ሁለት ጊዜ በመጫን ወደ ሣተላይት ገፅ (Satellite page) መሄድ እንችላለን። በመቀጠል የምንሠራው መሣሪያውን በኢትዮጵያ ውስጥ ለሚሠራ የጂፒኤስ መረጃ አሰባሰብ ሥራ ዝግጁ ማድረግ (Initialize) ይሆናል።

ለ. <u>መቀበያ መሣሪያውን ለሥራ ዝግጁ ማድረግ፣ (Initializing the Receiver)</u>

በመጀመሪያ መሣሪያውን ግልፅ በሆነና ጥሩ የሰማይ ዕይታ በሚገኝበት አካባቢ ይዞ መሄድ ያስፈልጋል። በመቀጠልም በሣተላይት ገፅ ላይ ምንም ዓይነት ሣተላይት ከመታየቱ በፊት "ENTER" የሚለውን ቁልፍ መጫን ያስፈልጋል። በመቀጠልም የወደታች አቅጣጫ ቁልፍን (Down Arrow key) በመጠቀም 'SELECT COUNTRY FROM LIST' የሚለው ሲገኝ 'ENTER' ቁልፍን በመጫን ይመረጣል። ከዚያም በዝርዝሩ ከሚታዩት አገሮች መካከል 'ETHIOPIA' የሚለውን ስናገኝ "Enter" ቁልፍ በመጫን መምረጥ ያስፈልጋል። ከ 'Select country from list' ውስጥ 'Ethiopia'ን ከመረጥን በኋላ መሣሪያው ስላለንበት ሥፍራ ተስማሚ ሣተላይቶችን ማፈላለግ ይጀምራል፣ በመቀጠልም በ10 ደቂቃ ውስጥ ቦታውን ያገኘዋል።

<u>ማሳሰቢያ፡-</u> በመቀበያ መሣሪያው "Select country from list" የሚለውን ባህሪይ በመጠቀም 'Ethiopia'ን መምረጥ ካልቻልን <u>ለምሣሌ</u> "Afghanistan" ወደ ሚለው ዘለሎ የሚመለስ ከሆነ "Autolocate" የሚለውን ባህሪይ መጠቀም ይቻላል። ይህንን ባህሪይ (Autolocate) ለመምረጥ የወደ ላይና የወደ ታች ቁልፎችን /up down arrow keys/ በመጠቀም "Autolocate" የሚለው ከተመለከተ የኋላ "ENTER" የሚለውን ቁልፍ መጫን ያስፈልጋል። በዚህ ጊዜ መሣሪያው ራሱ ያለበትን አገር መፈለግ ስለሚጀምር ምንም መነካካት አያስፈልግም። ምክንያቱም ራሱ ፈልጐ ለማግኘት ከ10-15 ያህል ደቂቃዎች ሊወስድበት ስለሚችል ነው።

3.4.3 <u>የሳተላይት ገፅ (Satellite page)</u> (ዕዝል I ሥዕል 1 ተመልከት)

መሣሪያውን እንዳበራነው 'Welcome' የሚል ገፅ ይመጣል። መሣሪያው የራሱን ዝግጅት /Self Test/ ካደረገ በኋላ ወዲያውኑ በሣተላይት (Satellite Status page) /ዕዝል I ተራ ቁጥር 1 ተመልከት/ ይተካና ሣተላይቶችን የማፈላለግና የማግኘት ሥራ ያከናወናል። በዚህ

ወቅት ከገፁ አናት በስተግራ በኩል 'ACQUIRING' የሚል መልዕክት መታየቱን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው። መሣሪያውን በቀን ውስጥ በተደጋጋሚ ከተጠቀምንበት ሳተላይቶችን በቀላሉ ስለሚያገኝ መልዕክቱን ሳያመለክት ወደ ነጥብ ቦታ ገፅ (Position page)) /ዕዝል I ተራ ቁጥር 2 ተመልከት/ ሊያልፍ ይችላል።

የመቀበያ መሣሪያው ከሣተላይቶች ጋር ግንኙነት ሲፈጥር ላገኛቸው ሣተላይቶች ለእያንዳንዳቸው Signal strength bar በማሳየት ከስሩ የሳተላይቶችን ቁጥር ያሳያል። ቁጥሮቹም ከ1-32 ናቸው።

ሣተላይቶችን የመፈለግና የማግኘት ሂደት በሦስት ደረጃዎች ይገለፃል።

1. የሣተላይት ግንኙነት ማመላከቻ ባር <u>የማይታይ ከሆነ</u> የመቀበያ መሣሪያው ሣተላይቶችን በማፈላለግ ላይ መሆኑን ያመለክታል።
2. የመልዕክት ማመልከቻው ባር ውስጡ <u>ነጭ (Hollow or white) ሆኖ</u> ከታየ ደግሞ መቀበያ መሣሪያው ከሣተላይቶች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ መረጃ እየሰበሰበ መሆኑን ያመለክታል።
3. የመልዕክት ማመላከቻው ባር ውስጡ ወደ ጥቁርነት ከተለወጠ የመቀበያ መሣሪያው አስፈላጊውን መረጃ ሰብስቦ ጨርሷል ማለት ነው። የጀርሚን II^+/12 መቀበያ መሣሪያ በአንድ ጊዜ እስከ አሥራ ሁለት ከሚሆኑ ሣተላይቶች መረጃ መሰብሰብ ይችላል።

የመሣሪያው የመረጃ አሰባሰብ ሂደት ያለበት ደረጃ በገፁ አናት በስተግራ በኩል ይታያል። በዚህ መሠረት፡-

- (ACQUIRING) የሚል ፅሁፍ ሲታይ መሣሪያው ሣተላይቶች በማፈላለግ ላይ መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል።
- '2D NAV' የሚል ፅሁፍ ሲታይ ደግሞ መሣሪያው ቢያንስ ከሦስት ሣተላይቶች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ የሁለትዮሽ ልኬትን (two-dimensional) ማለትም 'Easting' እና 'Northing' ቀምሯል ማለት ነው።
- '3D NAV' የሚል ፅሁፍ ሲታይ ደግሞ መሣሪያው ቢያንስ ከአራት እና በላይ ሣተላይቶች ጋር ግንኙነት ፈጥሮ፣ ትክክለኛነቱ የጨመረ/የተሻለ የሦስትዮሽ ልኬት (three-Dimensional) መረጃ ቀምሯል ማለት ነው። ይኸውም የምስራቃዊ፡

የሰሜናዊና የክፍታን /Easting, Northing and Altitude/ መረጃዎች ማግኘት ይቻላል ማለት ነው።

የተቀሩት የሣተላይት ገፅ ባህሪያት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

- በገጹ/በስክሪኑ አናት በስተቀኝ በኩል ግምታዊ የፖዚሽን ስህተት (Estimated position Error/EPE/) ይገኛል።
  EPE የኮኦርዲኔቶችን ግምታዊ የአግድሞሽ ትክክለኛነት በሜትር የሚያሳይ ነው።
- የሰሜን አቅጣጫ (North point):- የሰሜን አቅጣጫን የሚያሣይ ነው።
- የባትሪ ድንጋይ ኃይል መጠን አመልካች (Battery power indicator) ደግሞ የባትሪ ድንጋዩ ኃይል ሙሉ F(Full) እና ባዶ E(Empty) በሚል የሚያሣይ ነው። ባትሪ ድንጋዩ ማለቁን የሚያሣይ መልዕክት (Battery is low) እና በአመልካቹ E(Empty) የሚል ሲታይ ወዲያው አዲስ ባትሪ ድንጋይ መቀየር አስፈላጊ ነው። ነገር ግን Memory battery low የሚለው መልዕክት ሲታይ ወዲያው ለተቆጣጣሪው በማሳወቅ አዲስ AA መጠን ያላቸው ባትሪ ድንጋዮችን በመሣሪያው ውስጥ በመክተት ማጥፋትና በግምት ለአምስት ቀናት በማስቀመጥ የመሣሪያውን የውስጥ ሜሞሪ ባትሪ (Internal memory battery) ማስተካከል ይቻላል።

3.4.4 <u>የነጥብ ቦታ ገፅ (Position page)</u> (ዕዝል I ሥዕል 2 ተመልከት)

የነጥብ ቦታን ንባብ ለማመልከት የሚያስችሉ በቂ የሆኑ የሣተላይት መረጃዎችን (Signals) እንደሰበሰበ ወዲያውኑ የሣተላይት ገፅ (Satellite page) በነጥብ ቦታ ገፅ (position page) ይተካል።

- 3D NAV የሚለው ዕሁፍ እንደታየ PAGE የሚለውን ቁልፍ በመጫን ወደ ነጥብ ቦታ ገፅ /position page/ መሄድ የምንችል ሲሆን QUIT የሚለውን ቁልፍ በመጫን ደግሞ ወደ ሣተላይት ገፅ /Satellite page/ መመለስ ይቻላል።

  <u>ማሳሰቢያ</u>፡- ልክ የጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያው እንደበራ በሣተላይት ገፅ 2D NAV ወይም 3D NAV የሚል ንባብ ከመታየቱ በፊት ሆን ብለን PAGE የሚለውን ቁልፍ በመጫን ወደ ነጥብ ቦታ ገፅ /position page/ ከሄድን፣ በዚህ ነጥብ ቦታ ገፅ /position page/ ላይ የምናገኘው ንባብ ባለፈው ጊዜ መሣሪያው ያነበባቸውን /የመዘገባቸውን የኮኦርዲኔት ንባቦች (coordinates) ነው።

በነጥብ ቦታ ገፅ (Position page) ላይ የሚከተሉት ይገኛሉ።

- Compass display:- ይህ በእንቅስቃሴ ላይ ከሆንን በእያንዳንዱ እንቅስቃሴ ወቅት ያለውን የአንግል ንባብ (current bearing) የሚያሳይ ነው። የአንግል ቤሪንግ ከተገኘ በኋላ ከዚህ ቤሪንግ በመነሳትና 0^0 እስኪገኝ ድረስ በመንቀሳቀስ የቦታውን የሰሜን አቅጣጫ ማግኘት ይቻላል። (ዕዝል I ሥዕል 2 ተመልከት)

- Track Indicator:- ይህ የምንጓዝበትን አቅጣጫ የሚያመለክት ነው።

- "Compass display" እና "Track Indicator" በእንቅስቃሴ ላይ ካልሆንን አያገለግሉም።

- Speed:- በእንቅስቃሴ ላይ ከሆንን የምንጓዝበትን ፍጥነት በሰዓት ምን ያህል ኪ.ሜትር (Km/hr) እንደሆነ የሚያመለክት ነው።

- Total distance travelled (trip odeometer):- ይህ ጠቅላላ የተጓዝነውን ርቀት በኪ.ሜ. ምን ያህል እንደሆነ የሚያሳይ ነው። አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ሁሉ በኦዶ ሜትሩ /Odeometer/ የተነበበውን ቁጥር በማጥፋትና ወደ ዜሮ በመቀየር (Resetting) እንደ አዲስ እንዲቆጥር ማድረግ ይቻላል።

- Altitude:- ያለንበትን ከፍታ በዚሁ ገፅ ላይ ማንበብ ይቻላል። በጣተላይት ገፅ ላይ 2D NAV የሚለው ከታየ የከፍታ ንባቡ ያለፊውን የነጥብ ቦታ ከፍታ የሚያሳይ ሲሆን 3D NAV የሚለው ከታየ ግን አሁን ያለንበትን የነጥብ ቦታ ከፍታ ንባብ ይሰጠናል።

- TIME:- በገፁ የታችኛው ጠርዝ አካባቢ TIME በሚለው ሥር ሰዓትን በ12 ወይም በ24 ሰዓት አቆጣጠር ያሳያል።

3.4.5 የዩ.ቲ.ኤም /UTM/ ኮኦርዲኔቶችን ማስፈር (Plotting UTM Coordinates):-

የቦታ ገፅ ከሚሰጠው ከፍተኛ ጥቅም መካከል ያለንበትን ነጥብ ቦታ ንባብ በ'UTM' ኮኦርዲኔቶች ኢስቲንግና ኖርዚንግ ማሳየቱ ነው።

በካርታ ሥራ ወቅት የምንጠቀመው UTMን ብቻ ስለሆነ በመሣሪያው GPS ስክሪን /Screen/ ላይ የምናገኘውን የዩ.ቲ.ኤም /UTM/ ኮኦርዲኔቶች እንዴት መተርጐምና በኮኦርዲኔቶች መዝገቢያ ቅፅ ላይ መመዝገብና በካርታዎች ላይ ማስፈር እንደሚቻል በመመሪያው በስፋትና በጥልቀት ይገለፃል። ለካርታ ሥራው ውጤታማነት እነዚህን የኮኦርዲኔቶች አተረጓጐምና አሰፋፈር በሥልጠናና በመስክ ልምምድ ወቅት መከታተልና መረዳት በጣም ወሳኝ ነው።

i. <u>ምሥራቃዊ (Eastings) እና ሰሜናዊ (Northings) ንባቦችን በ2-2-3 አሀዞች (digits) መከፋፈል።</u>

በስክሪኑ ላይ የምናነባቸው የUTM ንባቦች የሚከተሉት ናቸው። በስክሪኑ 'Position' አርዕስት ሥር የቦታው ግሪድ ዞን ቁጥር፣ ለምሳሌ (36P፣ 37P፣ 38P፣ 36N፣ 37N፣ 38N ወዘተ)፣ በዚሁ መሥመር በላይኛው የኢስቲንግ ንባብ፣ በሥረኛው ደግሞ UTM በሚለው ትይዩ የኖርዚንግ ንባብ ይገኛል። የግሪድ ዞን ቁጥር ለካርታው ሥራ ስለማንጠቀምበት አይመዘገብም። የኢስቲንግና ኖርዚንግ ንባቦች ግን ለካርታ ሥራ በጣም ጠቃሚ ስለሆኑ በመጀመሪያ የኢስቲንግ ቀጥሎ የኖርዚንግ ንባቦችን በማንበብ በኮኦርዲኔቶች መመዝገቢያ ቅፅ ላይ መመዝገብ ያስፈልጋል። ሁለቱም ንባቦች ባለሰባት አሀዝ (digit) ቁጥሮች ናቸው።

ለአተረጓገምና ለማስፈር (Plotting) እንዲያመች እያንዳንዱን ንባብ በ2-2-3 አሀዝ አግባፍ በመከፋፈል መመዝገብ ያስፈልጋል። ይህ የአግባፍ ዘዴ ኮኦርዲኔቶችን በቀላሉ በመመዝገቢያ ቅፅና በካርታዎች ላይ ለማስፈር ይረዳል።

<u>ለምሣሌ</u>፡- የኢስቲንግ 0392629 እና የኖርዚንግ 0830758 የሚል ባለሰባት አሀዝ ንባቦችን ብናገኝ ወዲያው መተርጐምና መከፋፈል ያለብን 03-92-629 እና 08-30-758 በማድረግ ነው።

ይህ ማለት የመጀመሪያዎቹ ሁለት አሀዞች /ዲጂቶች/ (03 እና 08) የሚወክሉት 100ኪ.ሜ ስኴር ሥፍራን ሲሆን ቀጣዮቹ ሁለት አሀዞች /ዲጂቶች/ (92 እና 30) ደግሞ በ100 ኪ.ሜ ውስጥ የ1ኪ.ሜ ስኴር ሥፍራን ነው። ይህ ከ100 ኪ.ሜ. ስኴር የደቡብ ምዕራብ ማዕዘን በመነሳት ወደ ጎን እና ወደ ላይ በኪ.ሜትሮች የሚለካ ርቀት ነው። እንዲሁም የመጨረሻዎቹ ሦስት አሀዞች /ዲጂቶች/ (629 እና 758) ደግሞ ከ1ኪ.ሜ

ስኬር የደቡብ ምዕራብ ማዕዘን በመነሳት ወደ ጎን (Horizontal) እና ወደ ላይ (Vertical) አቅጣጫዎች ያለውን ርቀት በሜትር የሚያሳዩ ናቸው።

ii. <u>የዕይታ ግምት (Visualization) እና በትክክል ማስፈር (Actual Plot)</u>

የዩቲኤም /UTM/ ንባቦችን ወደ ካርታ ወይም ግሪድ ወረቀት ላይ በምናሰፍርበት ጊዜ የሚከተሉትን ማጤን ያስፈልጋል።

ሀ. የዕይታ ግምት (Visualization) እና

ለ. በትክክል ማስፈር (Actual Plot) ናቸው።

የዕይታ ግምቱ በካርታው ወይም ከግሪድ ወረቀቱ ላይ በየትኛው ግሪድ ስኬር ውስጥ መረጃው እንደሚሰፍር ለመገመት ይረዳል። ትክክለኛው ማስፈር ደግሞ በእርሳስና በማስመሪያ በመጠቀም የሚከናወን እና የገፅታውን ትክክለኛ ነጥብ ቦታ (Position) የሚያሣይ ይሆናል።

ከላይ በምሳሌው እንደተጠቀሰው ከ Easting (03-92-629) እና ከ Northing (08-30-758) ቁጥሮች ውስጥ ለዕይታ ግምት ጠቃሚ ቁጥሮች 92-6 እና 30-7 ናቸው። በዚህም መሠረት 92 (Easting) እና 30 (Northing) መስመሮችን ማየትና የሚቋረጡበትን ቦታ (intersection Point) ፈልጎ የማግኘት ሥራ ይከናወናል። በመቀጠልም ሁለቱ መስመሮች ከሚቋረጡበት ቦታ 600 ሜትር ወደ ምሥራቅና 700 ሜትር ወደ ሰሜን በግምት በማየት የመረጃው ነጥብ ቦታ ግምታዊ አካባቢ ማግኘት ሥራ ይከናወናል። ይህ ሥራ እንግዲህ በ1ኪ.ሜ ስኬር ውስጥ የሚከናወን ነው።

ትክክለኛውን ነጥብ ቦታ ለማስፈር /Actual plot/ ጥቅም ላይ የሚውሉት የመጨረሻዎቹ ሦስቱ አሀዞች ማለትም 629 ሜትር (East) እና 758 ሜትር (North) ናቸው። የመጀመሪያው ንባብ ከ92 ግሪድ መስመር ወደ ምሥራቅ 629 ሜትር ላይ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ከ30ኛው ግሪድ መስመር ወደ ሰሜን 758 ሜትር ላይ ይገኛል። እንግዲህ ሁለቱ የሚቋረጡበት ነጥብ የአንድ ሥፍራ ትክክለኛ ነጥብ ቦታ (Position) ያመለክታል ማለት ነው።

ነገር ግን ትክክለኛውን ነጥብ ቦታ ከማስፈራችን በፊት የመጨረሻዎቹ ሦስት አሀዞች በመስፈርቱ መሠረት ከሜትር ወደ ሚ.ሜ መቀየር ይኖርባቸዋል። የምንጠቀምበት መነሻ ካርታ መስፈርት ቢለያይም ከሜትር ወደ ሚ.ሜ በመቀየር ማባዣ የማግኘቱ ዘዴ ሁልጊዜም ተመሳሳይ ነው። አሠራሩን በሚገባ ለመረዳት ይቻል ዘንድ የሚከተሉት ምሣሌዎች በተለያዩ መሥፈርቶች ቀርበዋል። በ1፡50000 መስፈርት ካርታ ላይ መረጃዎችን ማስፈር ቢያስፈልግ፡-

- በ1፡50000 ካርታ ላይ 2ሚ.ሜ (20ሚ.ሜ) በመሬት ላይ 1000 ሜትሮች (1ኪ.ሜ) ይወክላል፡ በዚሁ መሠረት የUTM ንባብ የመጨረሻ ሦስት አሀዞችን ከሜትር ወደ ሚ.ሜ ለመቀየር የሚረዳ ማባዣ ቁጥር በሚከተለው አኳኋን ማግኘት ይቻላል።

- የ1፡50000 መስፈርት፡-

  1ሳ.ሜ = 50000 ሳ.ሜ

  1ሳ.ሜ = 500 ሜ

- በመሬት ላይ በUTM ግሪድ መስመሮች መካከል ያለው ርቀት 1000 ሜትር ነው። ስለዚህ በ1፡50000 መስፈርት 1000 ሜትር ርቀት የሚወክለው በ2ሣ.ሜትር ነው።

  ይህም፡ 1ሳ.ሜ = 50000 ሳ.ሜ

  1ሳ.ሜ = 500 ሜ

  ? = 1000 ሜ

  $$\frac{1000\ \text{ሜ} \times 1\text{ሳ.ሜ}}{500\text{ሜ}} = 2\ \text{ሳ.ሜ}$$

- በመቀጠል የማባዣ ቁጥር 2ሳ.ሜን ለ1000ሜ በማካፈል ይገኛል።

  2ሳ.ሜ ÷ 1000ሜ = 0.002

- ለ1፡50000 መስፈርት የ"UTM" ግሪድ መስመሮች የመጨረሻዎቹን ሦስት አሀዞች በ0.002 በማባዛት ወደ ሣ.ሜ መቀየር ይቻላል ማለት ነው።


  በተመሳሳይ አካኋን በ1፡25000፣ በ1፡10000፣ በ1፡5000፣ በ1፡2500 እና በ1፡2000 መስፈርቶች ባላቸው ካርታዎች ላይ መረጃዎችን ለማስፈር እንዲረዳ መስፈርቶቹንና ተስማሚ ማባዣዎችን የያዘ ሠንጠረዥ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 3.1 የተለያየ መስፈርት ላላቸው መነሻ ካርታዎች የማባዣ ቁጥሮች

መስፈርት	ማባዣ
1፡50,000	0.002
1፡25,000	0.004
1፡10,000	0.01
1፡5000	0.02
1፡2500	0.04
1፡2000	0.05

ማሳሰቢያ፡- በካርታ ላይ በምናሰፍርበት ጊዜ የመሣሪያውን ግምታዊ የነጥብ ቦታ ንባብ ስህተት (Estimated Position Error/EPE) ከግንዛቤ ውስጥ ማስገባት አለብን። ምክንያቱም በተለይ 1፡10000 ወይም 1፡5000 ወይም 1፡2500 መስፈርት በምንጠቀምበት ጊዜ የጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያው ላይ ባለው ከ15-20 ሜትር ስህተት ትክክለኛውን ቦታ ለማመልከት ችግር ሊገጥመን ይችላል። ከላይ የተጠቀሰው ችግር ሲያጋጥመን ያገኘነውን የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ በቀጥታ ከማስፈር ይልቅ የራሳችንን ግምት በመጠቀም ትክክለኛውን ቦታ ማመልከት ይኖርብናል።

ለምሳሌ፡- የጂፒኤስ ንባቡ አንድን ፎቅ ከመንገድ በስተቀኝ ሆኖ እያለ በስተግራ ሊያደርገው ይችላል። በዚህ ጊዜ የራሳችንን ግምት በመጠቀም ፎቁን በስተቀኝ ባለው ትክክለኛ ሥፍራ ላይ ማስፈር ይኖርብናል።



መስፈርተ 1:50000

ምዕራፍ አራት

4. የቆጠራ ካርታ ሥራ በገጠር አካባቢዎች

4.1 በገጠር አካባቢዎች የቆጠራ ቦታ መመስረቻ መመዘኛ ነጥቦች፡-

በገጠር አካባቢዎች የቆጠራ ቦታ አከላለል መሠረት የሚያደርገው የገጠር ቀበሌዎችን ይሆናል።

በገጠር የቆጠራ ቦታዎች አከላለል በሚከተሉት ዋና ዋና መመዘኛ ነጥቦች ላይ በመመሥረት ይከናወናል።

4.1.1 የቤተሰብ ብዛት በቆጠራ ቦታ ውስጥ፡- አንድ የቆጠራ ቦታ በአማካይ ከ150-200 ቤተሰቦችን እንዲይዝ ተደርጐ ይመሠረታል። ሆኖም በአንዳንድ ሁኔታዎች የተነሳ የቆጠራ ቦታን ከዝቅተኛ የአስተዳደር ክልል ወሰን ላለማስወጣት እና የቆጠራ ቦታውን ስፋት መጠን ለመጠበቅ ሲባል ይህንን ገደብ መጣስ የግድ ሊሆን ይችላል።

4.1.2 የቆጠራ ቦታ ስፋት፡- የቆጠራ ቦታ ሲመሠረት የቆዳ ስፋቱ ሌላው ግምት ውስጥ መግባት የሚገባው አስፈላጊ ነጥብ ነው። የሕዝቡም አሰፋፈር ሁኔታ የቆጠራ ቦታውን ስፋት ይወስናል።

እንደ አጠቃላይ መመሪያ የሚከተለውን ማስቀመጥ ይቻላል።

ሀ. የተበታተነ /የላላ/ የሕዝብ አሰፋፈር ባለበት አካባቢ የሚመሠረት የቆጠራ ቦታ የቆዳ ስፋት ከፍ ያለ ይሆናል። ስለሆነም በዚህ ዓይነቱ ቆጠራ ቦታ ሊኖር የሚገባው የቤተሰብ ብዛት ወደ ዝቅተኛው ገደብ ማለትም ወደ 150 ይጠጋል።

ለ. ጥቅጥቅ ወይም ችፍግ ያለ የሕዝብ አሰፋፈር ባለበት አካባቢ የሚመሠረት የቆጠራ ቦታ የቆዳ ስፋት አነስ ያለ ይሆናል። ስለሆነም በዚህ ዓይነቱ የቆጠራ ቦታ ሊኖር የሚገባው የቤተሰብ ብዛት ወደ ከፍተኛው ገደብ ማለትም ወደ 200 ይጠጋል።

ሐ. ለየት ያለ ሁኔታ ሲኖር ማለትም አስቸጋሪ የመሬት አቀማመጥና በጣም የተበታተነ የሕዝብ አሰፋፈር ሲያጋጥም በአንድ ቆጠራ ቦታ የሚኖረው የቤተሰብ ብዛት ከ150 ያነሰ ሊሆን ይችላል። በተጨማሪ በዚህ ጊዜ የቆጠራ ቦታው ስፋት በቆጠራ ወቅት አንድ ቆጣሪ ሊሸፍነው በሚችለው መጠን መገደብ እንዳለበት መገንዘብ ያስፈልጋል። እንደዚህ ለየት ያለ ሁኔታ ሲያጋጥም ካርታ ሠራተኛው ከተቆጣጣሪው ጋር በመወያየት ተገቢውን የአሠራር ዘዴ መቀየስ ይኖርበታል።

4.1.3 የቆጠራ ቦታ ወሰን ከአስተዳደር መዋቅር አንጻር፡-

አንድ የገጠር ቀበሌ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የቆጠራ ቦታዎች ሊወጣው ይችላል። ይሁንና አንድ የቆጠራ ቦታ አንድን የገጠር ቀበሌ አቋርጦ ሊመሠረት አይገባውም።

በተጨማሪ አንድ የገጠር ቀበሌ በአንድ ወረዳ ውስጥ ብቻ መታቀፍ ይኖርበታል። ስለዚህ የቆጠራ ቦታ ወሰኖች በማያሻማ መንገድ መለየትና መገለጽ ይኖርባቸዋል።

4.2 <u>በገጠር አካባቢዎች የቆጠራ ቦታ መመስረቻ ተከታታይ ቅደም ተከተሎች</u>፡-

የቆጠራ ካርታ ሥራ ዋነኛ ግቡ የቆጠራ ቦታዎች መመሥረት ነው። የቆጠራ ቦታዎችን የመመሥረት ተግባር በርከት ያሉ የካርታ ሥራ ቅደም ተከተሎችና ምዝገባዎችን የማካሄድ ሂደቶችን የሚያጠቃልል ሲሆን ለዚህም የተለያዩ ካርታዎች እንደ ተስማሚነታቸው ጥቅም ላይ ይውላሉ። በመሆኑም የሚከተሉትን ተከታታይ ቅደም ተከተሎች በካርታ ሥራው ወቅት በጥንቃቄ መከተል ከካርታ ሠራተኛው የሚጠበቅ ነው።

<u>ስቴፕ 1</u>፡- በሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት የካርቶግራፊ ቡድን በወረዳ ደረጃ <u>ተፈላጊ የሆኑትን መነሻ (ቤዝ) ካርታዎች ቆጠራ አካሂዷል</u>። በሥራ ምድባችሁ የቆጠራ ቦታን ለመሥራት የሚያገለግሉ መነሻ ካርታዎች ይደርሳችኋል። ካርታዎችን ከተረከባችሁ በኋላ ግን የተመደባችሁበት ወረዳ በካርታው ላይ መኖሩንና አለመኖሩን ማረጋገጥ ኃላፊነታችሁ ነው። ይህም ማለት የተረከባችኋቸው ካርታዎች ወረዳውን ሙሉ በሙሉ የሚሸፍኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ አለባችሁ። የተረከባችሁት የወረዳ መነሻ (ቤዝ) ካርታ ለናንተ የሚያስፈልግ ካልሆነ ወይም ወረዳችሁ በመነሻ (በቤዝ) ካርታው ሙሉ በሙሉ ካልተሸፈነ ጉዳዩን ለተቆጣጣሪያችሁ በአፋጣኝ በማስረዳት ተገቢውን ካርታ ማግኘት ይኖርባችኋል። መነሻ ካርታዎቹን አጣርቶ የመረከብ ሥራ ወደ ተመደባችሁበት ወረዳ ከመሄዳችሁ በፊት መከናወን ይኖርበታል።

<u>ስቴፕ 2</u>፡- ወደ ተመደባችሁበት ወረዳ በመሄድ የወረዳውን አስተዳዳሪ ወይም ተወካዩን ስለመጣችሁበት ዓላማ አስረዱ። አስፈላጊውን ትውውቅ ካደረጋችሁ በኋላ በወረዳው ውስጥ የሚገኙትን ዝቅተኛ የአስተዳደር ክልሎችን /የገጠር ቀበሌዎችን፤ ከተማዎችንና የጋርዮሽ መኖሪያዎችን የተሟላ ዝርዝር እንዲሰጣችሁ ጠይቁ። ከዚህ በኋላ የገጠር ቀበሌዎችን በቅጽ ገ-1 የጋርዮሽ መኖሪያዎችን ደግሞ በቅጽ ገ-3 መዝግቧቸው። ለቆጠራ ቦታ መመሥረቻ የተሰበሰበውን የገጠር ቀበሌዎች ዝርዝር ለተቆጣጣሪው በማቅረብ ማረጋገጫ ማግኘት አስፈላጊ ነው።

<u>ስቴፕ 3</u>፡- የመመዝገቢያ ቅጾች ገ-1 እና ገ-3ን ካጠናቀቃችሁ በኋላ ስለ ወረዳው ግንዛቤ ሊኖራችሁ ይገባል። ከዚያም በወረዳው ተወካይ ተባባሪነት <u>የወረዳውን ወሰን በመነሻ (በቤዝ) ካርታ ላይ ትከልላላችሁ</u>። ይህን በምታደርጉበት ወቅት የወረዳው ተወካይ ወዲያውኑ የወረዳውን ወሰን ይነገረናል ብላችሁ መጠበቅ የለባችሁም። ስለዚህ ለአከላለሉ የሚጠቅማችሁን መረጃ እንዲሰጣችሁ የሚረዱ ጥያቄዎችን በቅድሚያ ልትጠይቁት ይገባል።

በመጀመሪያ በአራቱ ማዕዘናት ማለትም በሰሜን፤ በምሥራቅ፤ በደቡብና በምዕራብ ያለውን የወረዳውን አቅጣጫ እንዲነግራችሁ ጠይቁት:: ካርታው ላይ የተጠቀሱ አንዳንድ የቦታ ስሞችን በመጥቀስ በወረዳው ውስጥ መኖርና አለመኖራቸውን ጠይቁ:: አንዳንዶቹ ቦታዎች በወረዳው ውስጥ ሌሎቹ ደግሞ ከወረዳ ወሰን ውጭ ናቸው ሊሏችሁ ይችላሉ:: የወረዳው ወሰን ወንዝ፤ ተራራ፤ ሸለቆ፤ አውራ ጐዳና፤ የእግር መንገድ፤ ጫካ ወይም ለጥ ያለ ሜዳ ሊሆን ይችላል:: ወሰኑንም በካርታው ላይ እርሳስ በመጠቀም ምልክት አድርጉበት:: ምልክት የማድረጉንም ሥራ ወረዳውን በሁሉም አቅጣጫ እስክትከልሉ ድረስ ቀጥሉ::

<u>ስቴፕ 4</u>:- አሁን ዋነኛ የመስክ ሥራችሁን ከየት እንደምትጀምሩ ከወረዳው ተወካይ ወይም ከገጠር ቀበሌው ሊቀመንበር ወይም ከግብርና ልማት ሠራተኛ መወያየት ትጀምራላችሁ:: ሥራውን የምትጀምሩበትን የገጠር ቀበሌ ከለያችሁ በኋላ ወደ ገጠር ቀበሌ ጽ/ቤት በመሄድ ከወረዳው ጽ/ቤት የተዘጋጀላችሁን የትብብር ደብዳቤ ለሊቀመንበሩ በመስጠት ስለሥራው ዓላማ አስረዱ:: ከዚያም የገጠር ቀበሌውን ወሰን እንዲያሳያችሁ ትጠይቃላችሁ:: ይህን ስታደርጉ የገጠር ቀበሌውን በመዞር ድንበሩን በሚገባ በመለየት <u>በድንበር ነጥቦች</u> ላይ የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ በመውሰድ በመነሻ ካርታው ላይ በእርሳስ ትከልላላችሁ:: በተጨማሪም የጂ.ፒ.ኤስ ንባቦቹን በቅጽ ገ-6 ክፍል 2 ላይ ትመዘግባላችሁ:: በዚሁ ጊዜ ለቆጠራ ቦታዎች ምሥረታ ይረዳ ዘንድ የገጠር ቀበሌው ምን ያህል የቆጠራ ቦታዎች ሊወጣው እንደሚችል ለመገመት የሚያስችል መረጃ ከገጠር ቀበሌ አመራር አባላትና ከራሳችሁ ግንዛቤ ማግኘት ይኖርባችኋል:: የገጠር ቀበሌው ድንበር የወረዳውም ድንበር ከሆነ ቀደም ብላችሁ <u>በስቴፕ 3</u> ያካለላችሁትን የወረዳ ድንበር ትክክለኛነት አሁን ማረጋገጥ ይኖርባችኋል::

<u>ማስታወሻ</u>:- <u>የድንበር ነጥቦች</u> የሚባሉት:-

ሀ. ድንበሩ የሚያቋርጣቸው ወንዞች፤ መንገዶች፤ አጥሮች፤ የኃይል መስመሮች የእግር መንገዶች፤ ...ወዘተ ሊሆኑ ይችላሉ::

ለ. በሜዳማ አካባቢዎች ላይ ለሚያልፉ ድንበሮች ደግሞ የድንበር ነጥቦች የድንበሩ መታጠፊያዎች (Nodes) ይሆናሉ::

ሐ. የተፈጥሮ ገፅታዎችን (ለምሣሌ ወንዝን) ለሚከተል ድንበር ደግሞ የቀበሌው ድንበር ወንዙ የሚነሣበትና የሚደርስበት ነጥብ የድንበር ነጥብ ይሆናል::

ስቴፕ 5፡- አሁን በቀበሌው ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦችን በመመዝገብ የቆጠራ ቦታዎችን የመመስረት ሥራ ትጀምራላችሁ። ለዚህም በመጀመሪያ ከገጠር ቀበሌው ሰሜናዊ ጫፍ በመጀመር በየመንደሩ ያሉትን ቤተሰቦች የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጽ/ቅጽ ገ-2/ በመጠቀም ምዝገባ ታካሂዳላችሁ። ምዝገባው ሲደረግ የጥምዝምዞሽ አካሄድን /Serpentine manner/ በመጠቀም ይሆናል። የምዝገባው ሂደት ለአንድ የቆጠራ ቦታ ምሥረታ በሚያስፈልገው የቤተሰብ ብዛት መገታት ይኖርበታል። በሌላ አነጋገር ቤተሰቦችን በምትመዘግቡበት ወቅት ምዝገባው በታሳቢ የቆጠራ ቦታ እየተገደበ መሆን አለበት። በየቆጠራ ቦታ ውስጥ ለቤተሰቦች ተከታታይ ተራ ቁጥር /001, 002 ...ወዘተ/ እየሰጣችሁ ትሄዳላችሁ። በገጠር ቀበሌው ውስጥ ያሉትን ቤተሰቦች መዝግባችሁ እስክታጠናቅቁ ድረስ በተሰጡት መመዘኛ ነጥቦች በመመርኮዝ የቆጠራ ቦታዎች ታካልላላችሁ። በምዝገባው ወቅት ቤተሰብን ከአንድ ጊዜ በላይ የመመዝገብ ወይም ሳይመዘገብ የመዝለልን ሥጋት ለማስወገድ በተመዘገበው ቤተሰብ መኖሪያ ቤት በር ላይ ጠመኔ/ኾክ/ በመጠቀም RCC (Rural Census Cartography) የሚል ምልክት ትጽፋላችሁ። በካርታው ላይ በቆጠራ ቦታ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ መንደሮች፡ ፍልውሃዎች፡ ት/ቤቶች፡ ጤና ጣቢያዎች፡ የፀሎት ቦታዎች፡ የገበያ ሥፍራዎች፡ ታሪካዊ ቦታዎች፡ ...ወዘተ የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ በመውሰድና በቅጽ ገ-6 ክፍል 3 ላይ በመመዝገብ ተገቢ ምልክታቸውን ተጠቅማችሁ በመነሻ ካርታው ላይ አሥፍሯቸው። በመንደሩ አማካይ ሥፍራ ላይ ጂ.ፒ.ኤስ ንባብ የተወሰደበት ነጥብ በመነሻ ካርታው ላይ በሚሰፍረው የመንደር ምልክት ላይ ትክክለኛ ቦታውን ይዞ መስፈር ይኖርበታል። በተጨማሪም በገጠር ቀበሌው ውስጥ በተመሰረቱ የቆጠራ ቦታዎች በሙሉ የተነበቡ የውስጥ ገፅታ የጂ.ፒ.ኤስ ንባቦች ለገጠር ቀበሌው የድንበር ነጥቦች ወደተሞሉበት ቅፅ ገ-6 ክፍል 3 ይተላለፋሉ።

በገጠር ቀበሌው ያሉት ቤተሰቦች በሠፈራ ወይም መንደር ምሥረታ ምክንያት በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ መንደሮች የተሰባሰቡ ከሆነና የአሰፋፈሩ ሁኔታ የተዘበራረቀ ከሆነ፡ በዚህም የተነሳ የሚከናወነው የቤተሰቦች ምዝገባ ለመዝለልና ለመደጋገም ሁኔታ የተጋለጠ ከሆነ በምዕራፍ 5 ውስጥ በተገለፀው ቅደም ተከተል በመጠቀም የካርታ ንድፍ ሥራ መሠራት ይኖርበታል። ከዚያም የቆጠራ ቦታዎች ሽንሸና በተሰጠው መመዘኛ መሠረት ይከናወናል። ሆኖም የንድፍ ሥራው አስፈላጊነት ከተቆጣጣሪ ጋር በመመካከር መወሰን ይኖርበታል።

የመንደሩን የቤተሰብ ብዛት ግምት በቅድሚያ ማወቅ ለቆጠራ ቦታ ምሥረታ ጠቃሚ መረጃ ይሰጣል። የቆጠራ ቦታዎች ሲመሠረቱ ድንበራቸውን በመነሻ (በቤዝ) ካርታ ላይ ማስፈር አስፈላጊ ነው። አንድ የገጠር ቀበሌ አንድና ከአንድ በላይ የቆጠራ ቦታዎች ሊወጣው ይችላል። የቆጠራ ቦታዎች ወሰን ሲካለል የማጣቀሻ መለያ ነጥቦች (Reference points) ለምሣሌ ፡ ቤተክርስቲያን፡ መስጊድ፡ ት/ቤት ...ወዘተ ከቆጠራ ቦታው ወሰን ውስጥና በማዕዘናት ላይ ሊገኙ ስለሚችሉ የእነዚህን ሥፍራዎች የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ በመውሰድ በመነሻ ካርታው ላይ ማስፈር ያስፈልጋል። በሌላ በኩል ደግሞ ከቆጠራ ቦታው ወሰን ውጭ የሚገኙና ለመግለጫ በማጣቀሻነት የሚጠቅሙ ነጥቦች ለምሳሌ የመኖሪያ ቤቶች፡ ቤተክርስቲያን፡

መስጊድ፤ ት/ቤት ...ወዘተ የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ በመውሰድ ሳያስፈልግ በመነሻ ካርታው ላይ አንባራዊ ስፍራቸውን ይዘው መስፈር ይኖርባቸዋል።

ማስታወሻ፡- የጂ.ፒ.ኤስ (GPS) መሣሪያውን በመጠቀም የቀበሌውን ድንበር በምትከልሉበት ወቅት በድንበር ነጥቦች ላይ ሁሉ ማንበብ ይኖርባችኋል። ይህም በቅጽ ገ-6 ክፍል 2 ላይ መሞላት ይኖርበታል። እንዲሁም በገጠር ቀበሌው ውስጥ የሚገኙ መንደሮች፤ ት/ቤቶች፤ ክሊኒኮች፤ መስጊዶች፤ ቤተክርስቲያኖች ...ወዘተ የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ በመውሰድና በተዘጋጀው ቅፅ /ቅፅ ገ-6 ክፍል 3/ ላይ በመሙላት የቆጠራ ካርታውን በምታዘጋጁበት ወቅት እነዚህ ምልክቶች በካርታው ላይ መስፈር ይኖርባቸዋል። ለቆጠራ ቦታ አከላለል ወይም ቦታዎችን ለማገናዘብ የሚያስችሉና የድንበር መግለጫን ለመፃፍ የሚያግዙ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ምልክቶች/ወንዞች፤ ኩሬዎች፤ መንገዶች፤ ድልድዮች፤ ...ወዘተ/ የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ ሳያስፈልግ በመነሻ ካርታው ላይ አንባራዊ ሥፍራቸውን እንደያዙ መስፈር ይኖርባቸዋል። የጂ.ፒ.ኤስ አጠቃቀምን በተመለከተ በምዕራፍ 5 የቀረበውን መመሪያ መመልከት ይቻላል።

ስቴፕ 6፡- ወደ ካምፓችሁ በመመለስ ከመስክ የሰበሰባችኋቸውን ዝርዝር መረጃዎች በማካተት ግልጽ የሆነ የቆጠራ ቦታ ካርታ አዘጋጁ። የምትሰሩበት አካባቢ የሕዝብ አሠፋፈር ጥቅጥቅ ያለ ከሆነና የቆጠራ ቦታው ስፋት በባለ 1:50,000 መስፈርት መነሻ (ቤዝ) ካርታ ላይ ዝርዝር መረጃዎች ለማስገባት በማይመች ደረጃ አነስተኛ ከሆነ ከፍ ባለ መስፈርት የቆጠራ ቦታውን ካርታ መስራት ይኖርባችኋል። ለዚህም የሚሆን A4 መጠን ያለው የግራፍ ወረቀት ይሰጣችኋል።

ማስታወሻ፡- አነስተኛ የቆጠራ ቦታ ለማሳደግ በምዕራፍ 2 የተሰጠውን የማሳደጊያ ቴክኒክ ትጠቀማላችሁ። ነገር ግን ካርታ የማሳደጉን ሥራ ስትሠሩ የተለመዱትን የመስፈርት ዓይነቶች መጠቀም ይኖርባችኋል። ለምሣሌ 1:25000 ወይም 1:10000

ስቴፕ 7፡- የሚቀጥለው ሥራ ደግሞ ወደ መስክ ተመልሳችሁ በመሄድ የማጣሪያ ሥራ መሥራት ይሆናል። የሰራችሁት የቆጠራ ቦታ ካርታ ምን ያህል ትክክል እንደሆነና አስፈላጊ የሆኑ የመሬት ገፅታዎች በካርታው መካተታቸውን ታጣራላችሁ። ካርታው እርማት የሚያስፈልገው ከሆነ እዚያው መስክ ላይ እርማቱን አድርጉ። የያዛችሁት ካርታ በባለትልቅ መስፈርት ስለሆነ በመነሻ/ቤዝ ካርታው ላይ ያልተካተቱን መለያ ምልክቶች ልትጨምሩ ትችላላችሁ። በተጨማሪም ሰያዛችሁት የቆጠራ ቦታ ካርታ ላይ አዋሳኝ የቆጠራ ቦታዎች አቀማመጥና ወሰኖችን ምልክት አድርጉ። የጐረቤት ቆጠራ ቦታዎች የጋራ ወሰኖች በሁሉም ቆጠራ ቦታዎች ካርታ ላይ መታየት ይኖርበታል።

በተዘጋጀው የድንበር መግለጫ ቅጽ /ቅጽ ገ-5/ ላይ የቆጠራ ቦታውን ወሰን በሚገባ ትገልጻላችሁ። ነገር ግን በመጀመሪያ በቅጽ ገ-5 መግቢያ በሚለው ባዶ ቦታ ወደ ቆጠራ ቦታው እንዴት መድረስ እንደሚቻል ባጭሩ መግለጫ መፃፍ ይኖርባችኋል። ገለጻው የሚጻፈው /የድንበር መግለጫ ጽሑፍ በሚለው ቦታ/ ከቆጠራው ቦታ ሰሜናዊ ጫፍ በመጀመር ከዚያም ምሥራቅ፤ ደቡብና ምዕራብ አቅጣጫ በመከተል ይሆንና በመጨረሻም ከመነሻው ቦታ ደርሶ ይገጠማል። ይህ የቆጠራ ቦታ የመጨረሻ

መለያ ቁጥር ከመሰጠቱ በፊት አደናጋሪ ሁኔታ እንዳይፈጠር ጊዜያዊ መለያ ቁጥር ይሰጠዋል። /የመለያ ቁጥር አሰጣጥ በስቴፕ 10 ላይ ተብራርቷል።/

ስቴፕ 8፡- ወደ ስድስት የሚጠጉ የቆጠራ ቦታዎች ከተመሠረቱ በኋላ ያለቀለት (የተጠናቀቀ) የቆጠራ ቦታ ካርታ ኮፒ በትረፊንግ ወረቀትና በቀለም በመጠቀም ለማዘጋጀት አንድ ቀን በካምፕ ማሳለፍ ያስፈልጋል። /ስዕል 3.2 ተመልከት/ ለእያንዳንዱ የቆጠራ ቦታ የቆጠራ ቦታውን ዶክሜንቶች (ማለትም የቆጠራ ቦታ ካርታ፤ የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅፅ /ቅፅ ገ-2/፤ የቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫ ቅፅ /ቅፅ ገ-5/ እና የቆጠራ ቦታ የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች መመዝገቢያ ቅፅ /ቅፅ ገ-6/) በማሰባሰብ አንድ ላይ በፋይል አስቀምጧቸው፤ መላውን ወረዳ በቆጠራ ቦታ ሸንሽናችሁ እስክታበቁ ድረስ ይህን የአሠራር ቅደም ተከተል ተጠቀሙ። ለዚህ ሥራ በካምፕ የምትቀመጡበት ቀን የአካባቢው የገበያ ቀን ወይም አመት በዓል፤ በአጠቃላይ የመስክ ሥራችሁን በተገቢው ሳምንወን የማትችሉበት ቀን ቢሆን ይመረጣል።

ስቴፕ 9፡- የቆጠራ ቦታ ካርታዎች ተመሳሳይ መስፈርት ሊኖራቸው ይገባል። የካርታ ሥራውን በምትሰሩበት ወቅት በገጠር ቀበሌዎች መካከል የይገባኛል ችግር ቢገጥማችሁ ከወረዳ አስተዳዳሪ፤ ከገጠር ቀበሌ አመራርና ከአካባቢው ሽማግሌዎች ጋር በመመካከር ችግሩን ለማስወገድ ሞክሩ። የድንበር አለመግባባቱ በወረዳዎች መካከል ከሆነ ችግሩን ለመፍታት ጉዳዩ በቀጥታ የሚመለከታቸው የወረዳ ኃላፊዎች በሚገኙበት መፍትሔውን መፈለግ ይገባል። ይህ ጉዳይ ሲፈጠር ወዲያውኑ ለተቆጣጣሪው ማመልከት ይኖርባችኋል። ካርታው ማሳየት የሚገባው ሕዝብ የሰፈረበትን ሥፍራ ብቻ ሳይሆን መላውን የመሬት አካል መሆን አለበት። በመሆኑም የምትሰሩት ካርታ ምንም ዓይነት ሥፍራ መዝለል አይገባውም። የተሰማራችሁበት ወረዳ በቆጠራ ቦታዎች ተሸንሽኖ ካበቃ በኋላ ወደ ወረዳው ዋና ከተማ በመሄድ መነሻ (ቤዝ) ካርታው ላይ ያሰፈራችኋቸውን ዝርዝር መረጃዎች በማካተት የወረዳውን ካርታ ታዘጋጃላችሁ። ይህ የወረዳ ካርታ የእያንዳንዱን የቆጠራ ቦታ አቀማመጥ፤ መለያ ቁጥርና የማገናዘቢያ መለያ ነጥቦችን (Reference points) ማሳየት ይኖርበታል። ወረዳውን የሚያዋስኑ የአስተዳደር እርከኖች (ክልል፤ ዞን፤ ወረዳ ...ወዘተ) ገደቦችን በዚህ ካርታ ላይ ማሳየት አትርሱ፤ ስማቸውንም በተገቢው ሥፍራ አስቀምጡ። ሁለትና ከዚያ በላይ የአስተዳደር እረከኖች ወሰን በአንድ ቦታ ላይ ሲያጋጥሙ ለምሳሌ የወረዳው ወሰን የክልሉ ወሰን ከሆነ በካርታ ላይ የሚሰፍረው የከፍተኛው አስተዳደር እርከን ማለትም የክልሉ ወሰን ምልክት ይሆናል።

ስቴፕ 10፡- በአሁኑ ወቅት ወረዳው በምን ያህል የገጠር ቀበሌ እና የቆጠራ ቦታዎች እንደተከፋፈለ ታውቃላችሁ። የእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ አንጻራዊ ሥፍራ በወረዳው ካርታ ላይ ከተሳለ በኋላ ከወረዳው ሰሜናዊ አካባቢ በመጀመር በጠመዝማዛ አካሄድ ለእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ ባለ ሦስት አሃዝ ተከታታይ የመለያ ቁጥር /001፤ 002፤ 003፤ ...ወዘተ/ ትሰጣላችሁ። የቆጠራ ቦታዎች መለያ ቁጥር አሰጣጥ ደግሞ በየገጠር ቀበሌ ማህበሩ ውስጥ የተወሰነ ይሆናል። የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር በባለ ሁለት አሃዝ ይሰጣል። አንድ የገጠር ቀበሌ አንድ የቆጠራ

ቦታ ብቻ ካለው መለያ ቁጥሩ 01፤ ከሁለት በላይ ካለው ደግሞ 01፤ 02፤ ... ወዘተ ይሆናል። ከዚያም የቆጠራ ቦታዎች አንጻራዊ ሥፍራቸውን ባዘጋጃችሁት የወረዳ ካርታ ላይ በየገጠር ቀበሌ ማህበሩ ውስጥ ታሳያላችሁ።

<u>ለምሣሌ</u>:- ወረዳው 33 የገጠር ቀበሌዎች ቢኖሩትና የመጀመሪያው የገጠር ቀበሌ ሁለት የቆጠራ ቦታዎች ቢወጡት በወረዳው ካርታ ላይ የመለያ ቁጥር 001-01 ለመጀመሪያው 001-02 ለሁለተኛው የቆጠራ ቦታ ትሰጣላችሁ። የመጨረሻው የገጠር ቀበሌ /ሰላሣ ሶስተኛው/ ሦስት የቆጠራ ቦታዎች ቢወጣው የሚሰጣቸው መለያ ቁጥር 033-01፤ 033-02 እና 033-03 ይሆናል። ይህ እንዲህ ሆኖ በገጠር ቀበሌ ውስጥ ለሚፈጠሩ ልዩ የቆጠራ ቦታዎች የሚሰጠው መለያ ቁጥር 91,92,93 ...ወዘተ ይሆናል። ይህ ዓይነቱ የመለያ ቁጥር አሰጣጥ በወረዳው የሚገኙትን የገጠር ቀበሌዎችና የቆጠራ ቦታዎች አንጻራዊ ሥፍራ ያመለክታል።

<u>ማስታወሻ</u>:- የገጠር ቀበሌና የቆጠራ ቦታ የመለያ ቁጥር አሰጣጥ ከተከናወነ በኋላ መለያ ቁጥሮቹ ወደ ቆጠራ ቦታ ካርታ፣ ወደ ድንበር መግለጫ ቅጽ/ቅጽ ገ-5/፤ ወደ ቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጽ/ቅጽ ገ-2/፤ እና ወደ ሌሎች አስፈላጊ ሰነዶች መወራረስ ይኖርባቸዋል።

<u>ስቴፕ 11</u>:- ለገጠር ቀበሌዎችና ለቆጠራ ቦታዎች መለያ ቁጥር ሰጥታችሁ ካበቃችሁ በኋላ ወረዳውን በመቆጣጠሪያ ቦታዎች እርሳስ በመጠቀም ከፋፍሉት። <u>አንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ በአማካይ /ልዩ የቆጠራ ቦታን ጨምሮ/ አምስት የቆጠራ ቦታዎች</u> ማቀፍ ይኖርበታል። በአንዳንድ አጋጣሚዎች የመቆጣጠሪያ ቦታ በመጠኑም ቢሆን ከአምስት በታች ወይም በላይ የቆጠራ ቦታዎችን ሊይዝ ይችላል። የመቆጣጠሪያ ቦታዎች በሚመሰረቱበት ወቀት የሚከተሉትን ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

ሀ. የቆጠራ ቦታዎች የቆዳ ስፋት ትልቅ ሲሆን በአንዱ የመቆጣጠሪያ ቦታ የሚታቀፉ የቆጠራ ቦታዎች ብዛት ከአምስት ሊያንስ ይችላል። ወይም ደግሞ አብዛኛዎቹ በአንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ የሚታቀፉ የቆጠራ ቦታዎች የያዙት የቤተሰብ ብዛት ከፍተኛ ሲሆን /ከ200 በላይ ቤተሰቦች/ ቁጥራቸው ከአምስት ሊያንስ ይችላል። በሌላ በኩል በመቆጣጠሪያ ቦታው የሚታቀፉ አብዛኛዎቹ ቆጠራ ቦታዎች የያዙት ቤተሰብ ብዛት ዝቅተኛ ሲሆንና /ከ150 ቤተሰብ በታች/ የቆዳ ስፋታቸው ትልቅ ካልሆነ የመቆጣጠሪያ ቦታው ከአምስት በላይ የቆጠራ ቦታዎችን ሊያቅፍ ይችላል።

ለ. በአንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ የሚካተቱ የቆጠራ ቦታዎች እርስ በእርስ ኩታ-ገጠም መሆን ይኖርባቸዋል። በእነዚህ የቆጠራ ቦታዎች መካከል ተቆጣጣሪው ከቦታ ቦታ ተዘዋውሮ እንዳይሰራ የመጓጓጥ ችግር የሚፈጥሩ ከፍተኛ መሰናክሎች /ለምሳሌ ትልቅ ወንዝ፤ ተራራ፤ ወዘተ/ ሊኖር አይገባም። የእነዚህ መሰናክሎች መኖር በአንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ ውስጥ የሚታቀፉ የቆጠራ ቦታዎችን ብዛት ከአምስት በታች ወይም ከአምስት በላይ እንዲሆን ሊያስገድድ ይችላል።

ሐ. አንድ የገጠር ቀበሌ ራሱን ችሎ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የመቆጣጠሪያ ቦታ ሊወጣው ይችላል። አንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ ከአንድ በላይ ቀበሌዎችን አካቶ በሚመሰረትበት ወቅት ቀበሌዎቹ ሙሉ በሙሉ እንጂ የቀበሌዎቹን ከፊል የቆጠራ ቦታዎች አካቶ ሊመሠርት አይችልም። በሌላ በኩል ደግሞ የአንድ አነስተኛ ከተማ የቆጠራ ቦታዎች ከገጠር ቀበሌ የቆጠራ ቦታዎች ጋር በመጣመር በአንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ ሊካተቱ ይችላሉ።

መ. የመቆጣጠሪያ ቦታዎች ተዘጋጅተው ካበቁ በኋላ ከሰሚናዊ አቅጣጫ በመጀመርና የጥምዝምዞሽ አካሄድን በመጠቀም 01፤ 02፤ 03፤ ... ወዘተ በማለት ለእያንዳንዱ የመቆጣጠሪያ ቦታ በእርሳስ ባለሁለት አሃዝ ተከታታይ የመለያ ቁጥር ስጡ። ከዚያም የተቆጣጣሪያችሁን አስተያየትና ውሣኔ ካገኛችሁ በኋላ የመቆጣጠሪያ ቦታዎችን ድንበር በቀይ ማርከር ከልሉ።

ሠ. ሁለት ተጨማሪ የወረዳ ካርታ ኮፒ ታዘጋጁና ከሦስቱ አንዱን የወረዳ ካርታ በመውሰድ የመቆጣጠሪያ ቦታዎችን/በምሳሌ፤ ...ወዘተ/ እያቆረጣችሁ ታወጣላችሁ። ቆርጣችሁ ያወጣችሁትን እያንዳንዱን የመቆጣጠሪያ ቦታ በአዲስ ፋይል ላይ ትለጥፋላችሁ። በፋይሉ የውስጥ ገጽ ላይ «የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ» በሚል ርዕስ ሥር በክፍል 3.4.2 እንደታየው ዝርዝር መረጃዎችን ታካትታላችሁ። በመጨረሻም ይህንን የመቆጣጠሪያ ቦታ ፋይል በእርሱ ውስጥ የታቀፉ የቆጠራ ቦታዎች ፋይሎች ላይ ደርባችሁ አንድ ላይ ታስራላችሁ። በተጨማሪም በመቆጣጠሪያ ቦታው ውስጥ ያሉ የቀበሌዎችን የድንበር ነጥቦች የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ የያዘ ቅፅ /ቅፅ ገ-6/ን በዚሁ ፋይል ውስጥ ትጨምራላችሁ።

ስቴፕ 12፡- እዚህ ላይ የካርታ ሠራተኛው በተመደበበት ወረዳ የካርታ ሥራውን አጠናቋል። ቀጥሎ ተቆጣጣሪው በተሰጠው የክንውኖች ዝርዝር መሠረት የተሰሩት ሥራዎች ትክክለኛ መሆናቸውን በጥንቃቄ ማጣራት ግዴታው ነው። በዚህም መሠረት በተሰራው የቆጠራ ቦታ ካርታ፤ የቤተሰብ ምዝገባ፤ የቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫ፤ የመቆጣጠሪያ ቦታዎች ሽንሽናና የወረዳ ካርታ ሥራ በአጥጋቢ ሁኔታ መሠራቱንና በወረዳው ውስጥ የሚገኙትን የገጠር ቀበሌዎች፤ የቆጠራ ቦታ ካርታዎች፤ የቆጠራ ቦታ መግለጫዎች፤ የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጾች፤ እንዲሁም በወረዳው የሚገኙ ከተማዎች፤ ከፍተኞችና ቀበሌዎች ዝርዝር፤ የቆጠራ ቦታ ካርታዎች፤ የቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫዎች፤ የቤቶችና ቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጾች እና ሌሎች ተፈላጊ ሰነዶችን ጥራትና ብዛት ካረጋገጠ በኋላ ለዚህ ሥራ በተዘጋጀው የመረካከቢያ ቅጽ ላይ በጥንቃቄ ይመዘግባል።

ይህ ምዝገባ የሚዘጋጀው በሦስት ኮፒ ሲሆን ከተዘጋጀ በኋላ የተሟላ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚመለከተው ተቆጣጣሪ ይፈርምበታል። በዚህም መሠረት ተቆጣጣሪው አንድ የመረካከቢያ ኮፒ ለራሱ አስቀርቶ ሌሎች ሰነዶችን፤ የተጠናቀቁ የቴክኒክ ቅጾችንና ካርታዎችን ለአስተባባሪዎች አሳልፎ ያስረክባል።

ስቴፕ 13፡- አስተባባሪው ከተቆጣጣሪው የተረከባቸውን ሰነዶች ትክክለኛና የተሟሉ መሆናቸውን ካረጋገጠ በኋላ ለኮሚሽኑ ጽ/ቤት እስኪያስረክብ ድረስ በእንክብካቤ ማቆየት ይኖርበታል። ከዚያም በተዘጋጀው የመረካከቢያ ቅጽ አማካይነት አስተባባሪው ዕቃዎቹን ለኮሚሽኑ ጽ/ቤት ያስረክባል።

ማስታወሻ፡- የወረዳው የቆጠራ ካርታ ሥራ ሲጠናቀቅ የከተማና የገጠር ቅጾችንና ካርታዎችን ከመስክ ወደ ሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት ለማስተላለፍ ካርታዎችንና ቅያችን ማረካከቢያ ቅፅ /ቅፅ ካቅመ/ን መጠቀም ያስፈልጋል።

4.3 በቆጠራ ቦታ ምሥረታ ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮች፡-

በተለያዩ ምክንያቶች የቆጠራ ቦታዎች የተለያየ ቅርጽና መጠን ሊኖራቸው ይችላል። ለምሣሌ ያህል አንድ የገጠር ቀበሌ አንድ የቆጠራ ቦታ ብቻ ወይም ደግሞ ከአንድ በላይ የቆጠራ ቦታዎች ሊወጣው ይችላል። በየትኛውም ሁኔታ ቢሆን የቆጠራ ቦታው ድንበርና የዝቅተኛው አስተዳደር ወሰን ግልጽ በሆነ መንገድ መታየት አለባቸው። በመስክ ላይ ሊያጋጥሙ ከሚችሉ ችግሮች መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

ሀ. በመስክ ሥራ ወቅት ተጐራባች አስተዳደር ክፍሎች የድንበር አለመግባባት ሊኖራቸው ይችላል። በዚህን ጊዜ ችግሩ የሚመለከታቸው የአስተዳደር ኃላፊዎች በተገኙበት በቆጠራ ካርታ ሥራ ዓላማ አንፃር እንዲፈታ ማድረግ ያስፈልጋል።

ለ. በአንድ ወረዳ ውስጥ በጐረቤት ወረዳ አስተዳደር ሥር የሆነ የኪስ መሬት ሊያጋጥም ይችላል። በዚህ ጊዜ የኪስ መሬቱ በካርታ ሥራው የሚሸፈነው በአካል በሚገኝበት ወረዳ ውስጥ በተመደቡት የካርታ ሥራ ቡድኖች እንጂ በሚያስተዳድረው ወረዳ ሥር በሚንቀሳቀሱ የካርታ ሥራ ቡድኖች መሆን የለበትም። ለዚህ ዓይነቱ አካባቢ የመለያ ቁጥር አሰጣጥ ግን በአስተዳደር በታቀፈበት ወረዳ ውስጥ ይሆናል።

ሐ. አንዳንድ ጊዜ በአንድ ቀበሌ ሥር የሚተዳደሩ ሆነው ግን በአካል የተነጠሉ የገጠር ቀበሌ አካሎች ያጋጥማሉ። በዚህን ጊዜ እነዚህን የተነጣጠሉ አካባቢዎች ራሳቸውን የቻሉ የቆጠራ ቦታዎች በማድረግ መውሰድ ያስፈልጋል።

መ. በአንድ የገጠር ቀበሌ ውስጥ ሰፍረው ግን በሌላ የገጠር ቀበሌ አባል የሆኑ ቤተሰቦችም ሊያጋጥሙ ይችላሉ። እነዚህ ቤተሰቦች በሚካሄደው የቤተሰብ ምዝገባ ወቅት በአካል በሚገኙበት የገጠር ቀበሌ እንጂ በአስተዳደር በሚገኙበት የገጠር ቀበሌ በኩል መመዝገብ የለባቸውም። ሆኖም በቅጽ ገ-2 ላይ እነዚህን ቤተሰቦች በተመለከተ ያሉበትን ሁኔታ በአስተያየት መግለፅ ያስፈልጋል።

ሠ. በወረዳው ውስጥ የሚገኙ የጋርዮሽ መኖሪያዎች የወረዳውን ጽ/ቤት በማነጋገር በቅጽ ገ-3 ላይ ከተመዘገቡ በኋላ በመስክ ላይ ደግሞ ዝርዝሩ እንዲጣራ ይደረጋል። ማለትም የቆጠራ ቦታዎች በሚመሠረቱበት ወቅት ቅጽ ገ-3 የተሟላ እንዲሆን ይደረጋል። በተጨማሪም በቆጠራ ቦታው ውስጥ የጋርዮሽ መኖሪያውን አንጻራዊ ሥፍራ፤ ጂ.ፒ.ኤስ በማንበብና በቅጽ ገ-6 ክፍል 3 በመመዝገብ በመነሻ ካርታው ላይ ማስፈር ያስፈልጋል። እንዲሁም ጠቅላላ የነዋሪዎችን ብዛት ከነመጠሪያ ስማቸው ማስገባት ያስፈልጋል።

ሆኖም በጋርዮሽ መኖሪያው ያሉት የነዋሪዎች ብዛት ከ100 በታች ከሆነና በዚሁ መኖሪያ ውስጥ ቤተሰቦች የሚኖሩ ከሆነ እነዚህ ቤተሰቦችና የጋርዮሽ መኖሪያው ስም ከነነዋሪዎቹ በቅጽ ገ-2 ላይ ይመዘገባሉ። ከዚያም የቤተሰቡን ተራ ቁጥር በመጥቀስ በቅፁ ግርጌ ቤተሰቡ በየትኛው የጋርዮሽ መኖሪያ እንደሚኖር አስተያየት ይፃፋል። በቆጠራ ቦታ አመሠራረት ወቅት እነዚህ ቤተሰቦች በአካባቢው ከሚገኙ ሌሎች ቤተሰቦች ጋር ተደምረው ቁጥራቸው ከ150-200 ከሆነ በአንድ የቆጠራ ቦታ ውስጥ እንዲካተቱ ይደረጋል።

ረ. አንድ መቶና ከዚያ በላይ ነዋሪዎች የሚገኙባቸው በገጠር ቀበሌ ውስጥ የሚገኙ የጋርዮሽ መኖሪያዎች እንደ ልዩ የቆጠራ ቦታዎች ተወስደው 91,92, ...ወዘተ በማለት መለያ ቁጥር ይሰጣቸዋል። አንድ መቶና ከዚያ በላይ ነዋሪዎች የሚገኙባቸው የጋርዮሽ መኖሪያዎች ያያዙት ቦታ ስፋት ትልቅ ከሆነ እነዚህ የጋርዮሽ መኖሪያዎች «ራሳቸውን የቻሉ የቆጠራ ቦታዎች» በመሆን ልክ እንደማንኛውም የቆጠራ ቦታ የራሳቸው ድንበር ተለይቶ ካርታ ይሰራላቸዋል። ልዩ የቆጠራ ቦታዎች በሚሆኑ የጋርዮሽ መኖሪያዎች ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦች ደግሞ በቅጽ ገ-4 ላይ ይመዘገባሉ።

ሰ. አንዳንድ አካባቢዎች በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወረዳዎች ድንበር ላይ የሚገኙ ጥቅጥቅ ያሉ መንደሮች (ሠፈራዎች) ሊኖሩ ይችላሉ። ለምሣሌ በኦሮሚያ ክልል ምዕራብ ሐረርጌ ዞን መረባ የሚባል መንደር በጭሮና በጡሌ ወረዳዎች ድንበር ላይ ይገኛል። የመረባ መንደር አካሎች ባላቸው የአስተዳደር ግንኙነት መሠረት ተወስደው የካርታ ሠራተኛው በሚሠራበት ወረዳ የሚገኘውን የመንደር አካል ብቻ በቆጠራ ቦታ መከፋፈል ይኖርበታል። ቀሪውንና በአዋሳኝ ወረዳ ውስጥ የሚገኘውን የመንደር አካል ደግሞ በዚያኛው ወረዳ ተመድቦ የሚሠራው የካርታ ሠራተኛ እንዲሠራው ይደረጋል። /ለዚህም ማስረጃ ስዕል 3.1ን ተመልከት።/

ሸ. በተመሳሳይ መንገድ በሁለት ኩታ-ገጠም የገጠር ቀበሌዎች ድንበር ላይ ያረፈ መንደር (ሠፈራ) ሊገጥም ይችላል። በዚህ ወቅት የቀበሌው ድንበር መጀመሪያ ከተለየ በኋላ የዚህ ሰፈራ አካላት ባላቸው የአስተዳደር ግንኙነት መሠረት የካርታ ሥራ ይሠራላቸዋል።

ቀ. በገጠር ቀበሌዎች የታቀፉ/ ያልታቀፉ/ የመንግስትና የግል ሰፋፊ እረሻዎች፤ ፓርኮች፤ የግጦሽ መሬቶች፤ ደኖች፤ ለተለያዩ አገልግሎት የተገነቡ ካምፖች/ የወታደር ካምፕ፤ ሕፃናት አምባ ወዘተ.../ ካጋጠመው የቆጠራ ካርታ አሰራርና መለያ ኮድ አሰጣጥ እንደሚከተለው ይሆናል::

1/ ከላይ የተዘረዘሩት ሥፍራዎች/ ሰፋፊ እርሻ፤ ደን ፤የግጦሽ መሬት ወዘተ/ በአንድ ቀበሌ ድንበር ውስጥ ተጠቃለው የሚገኙ ወይም በዛ ባሉ ቀበሌዎች ላይ ሊገኙ ይችላሉ:: በሁለቱም ሁኔታዎች የእነዚህ ስፍራዎች ካርታ ከቀበሌው/ ከቀበሌዎች ጋር የሚሰራ ሳይሆን ለብቻቸው ድንበር ተበጅቶላቸው ይሰራሉ::


2/ እንዚህ ሥፍራዎች ውስጥ ቤተሰቦች የሚኖሩ ከሆነ ምዝገባው በሚመለከተው ቅፅ ሆኖ ሥፍራው በቆጠራ ቦታዎች ይከፋፈላል::

3/ ሥፍራው በቆጠራ ቦታዎች ከተከፋፈለ የመለያ ቁጥር አሰጣጡ ከ401 ጀምሮ ሲሆን ለቆጠራ ቦታዎች ካዱ 401-01፤ 401-02 ወዘተ እየተባለ እንዲሰጥ፤ ይሆናል::

4/ ሥፍራው ቤተሰብ የሌለውና ባዶ ከሆነ የሥፍራው ስም/ እርሻ፤ ደን፤ ፓርክ ወዘተ/ ተብሎ ይፃፍና 401 ጀምሮ ኮድ ይሰጠዋል::

ሠዕል 3.1

መረባ


ጡሉ ወረዳ
ወደ አርሻ ገበያ
አብዱረሂማን ጳደ
ዘመድኩን አለሙ
ተከስተ ፀጋ
ንጉሴ ሎሳ
አብዱላ አሊ
ወደ ሜሮ
ሜ ሮ ወ ረ ዳ
መስፈርት 1:50000
መግለጫ
የወረዳ ድንበር
የገጠር ቀበሌ ድን,
የስጋ መኪ.መን.
የእግር መንገድ
መንደር
ቤተክርስቲያን
ሳርቤት
ቆርቆሮ ቤት
ክሊኒክ
የገበያ ቦታ
ተራራ

4.4 የገጠር አካባቢ ካርታዎች ዲዛይንና ይዘት፡-

ለገጠር አካባቢዎች ሶስት ዓይነት ካርታዎች መሠራት ይኖርባቸዋል። እነዚህም የቆጠራ ቦታ፤ የመቆጣጠሪያ ቦታና የወረዳ ካርታዎች ናቸው።

4.4.1 የቆጠራ ቦታ ካርታ፡- የቆጠራ ቦታ ካርታ መጠን በመሬት ላይ በሚታየው የቆጠራው ቦታ የቆዳ ስፋት ይወሰናል። ቢሆንም የአንድ ቆጠራ ቦታ ካርታ ዝርዝር መለያ ነጥቦችን በካርታው ውስጥ በብቃት ለማሳየት በማያስችል መንገድ ማነስ እንደሌለበት መገንዘብ ያስፈልጋል። የቆጠራ ቦታን ከመነሻ (ቤዝ) ካርታ ላይ የማሳደግ ሥራ የሚሠራው ጠቃሚ ዝርዝር መለያ ነጥቦችን ለመጨመር እና በትክክል እንዲሰፍሩ ለማድረግ እንዲያስችል መሆኑን መዘንጋት የለበትም።

የቆጠራ ቦታ ካርታ የሚከተሉትን ነጥቦች በተገቢው ሥፍራቸው ማካተትና ማሳየት አለበት። (ስዕል 3.2 ተመልከት)

ሀ. የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ክልል፤ ዞን፤ ወረዳና የገጠር ቀበሌ ስሞች፤

ለ. የገጠር ቀበሌ የመለያ ቁጥር፤

ሐ. የቆጠራ ቦታው የመለያ ቁጥር፤

መ. በቆጠራ ቦታው ውስጥ ያሉትን ጠቅላላ የቤተሰቦች ብዛት፤

ሠ. በቆጠራ ቦታው ባሉ የጋርዮሽ መኖሪያዎች ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎች (ካለ) ጠቅላላ ብዛት፤

ረ. ግምታዊ የቆጠራ ቦታው የቆዳ ስፋት፤

ሰ. የቆጠራ ቦታው ወሰን (ተለይተው የሚታወቁ ገፅታዎች ተከትሎ የተከለለ ማለትም እንደ ወንዞች፤ መንገዶች፤ ድልድዮች፤ ... ወዘተ)፤

ሸ. የመሬት ላይ ገፅታዎች (ወንዞች፤ የመኪና መንገዶች፤ የእግር መንገዶች፤ ድልድዮች፤ ...ወዘተ)፤

ቀ. የመንደሮች፤ ት/ቤቶች፤ የጤና ማዕከላት፤ ቤተክርስቲያኖች፤ መስጊዶች፤ እንዲሁም ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች መስጫ ተቋማት አቀማመጥ፤

በ. ጠቃሚ የሆኑ መለያ (Reference) ገፅታዎች (ጎላ ብለው የሚታዩ ቤቶችና ሰፋፊ እርሻዎች ...ወዘተ)፤

ተ. በቆጠራ ቦታው ወሰን የሚገኙ ተጎራባች ወረዳዎች፤ የገጠር ቀበሌዎችና የቆጠራ ቦታዎች ስሞችና የወሰን መገናኛ ነጥቦች፤

ቸ. የሰሜናዊ አቅጣጫ አመልካች፤

ኀ. በካርታው የግራ ጐን በታች በኩል የሚጻፉ የልዩ ምልክቶች መፍቻ /ማስታወሻ/፤

ነ. በካርታው የሠፈሩ የተለያዩ ምልክቶችን የሚያስረዳ መግለጫ /ሌጀንድ/፤

ኘ. የካርታው መሰፈርት፤

ከ. የመቆጣጠሪያ ቦታ መለያ ቁጥር፤

አ. የቆጠራ ቦታው ካርታ ተሰርቶ የተጠናቀቀበት ቀን፤ የካርታ ሠራተኛውና የተቆጣጣሪው ስምና ፊርማ።

ሥዕል 4·2

ክልል	ኦሮሚያ
ዞን	ደቡብ ምዕራብ ሸዋ
ወረዳ	ኢሉ
የገጠር ቀበሌ ስም	ሙሎሳታያ
የገጠር ቀበሌ መ/ቁ	ዋር·005

የሊ/መንበር ስም	አበባው ዋጹ
የቆጠራ ቦታ መ/ቁ	005-02
የቤተሰብ ብዛት	200
ግምታዊ ስፋት	2·5ኪ·ሜ·ስ
የመቆጣጠሪያ ቦታ መ/ቁ ..	03



መስፈርት 1:50,000

መፍቻ
1·ካሉ ተሾመ
2·አሰፋ መርጋ
3·ቀነኒ ብረቱ
4·ከበቡሽ አክልሉ
5·ሌሊሴ ጋዲሳ

መግለጫ	
—··—	የገ/ቀበሌ ድንበር
———	የቆጠራ ቦታ ድንበር
- - - - - - - -	የእግር መንገድ
	መንደር
A	የገ/ቀበሌ ጽ/ቤት
	ክሊኒክ
	ወፍጮ ቤት፣ የገበያ ቦታ
	ቆርቆሮ ቤት፣ ሣር ቤት

የረዳት ካርታ ሠራተኛ ስም ታሪኩ ጀቤሳ ፊርማ ቀን 06/06/96

የተቆጣጠሪ ስም ቱሉ ጐሳምሳ ፊርማ ቀን 06/06/96

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
የገጠር ቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫ ቅፅ

ቅጽ ገ-5

ክፍል 1፡- የአካባቢ መለያ

1			2			3			4				5		
ክልል	1	2	ዞን	3	4	ወረዳ	5	6	የገጠር ቀበሌ	7	8	9	የቆጠራ ቦታ	10	11
ኦሮሚያ			ጊቤ-ሸካ ማጂ-ዚኞ			ሺሌ			ሙሉ ሳታሚ	0	0	5	005-02	0	2

ክፍል 2፡- የቆጠራ ቦታ አድራሻ መግለጫ

6. መግቢያ ዓዘሂህ ዓቒጠራ ቦታ ዓሰሞን መነሻ ሩፋን ሳሎበርሙ ዱ ቤት በለተሰሞን-ቀዳጊ በሚቀጥ ሂ·ግ ሳ·ሚ ዓሃፅ በመጋዝ ዓሸቶ ከሰ ጀቤቸ ቆርቆሮ ቤት ወዴ ውጫ ሺዳር ጉ ዓገኛ ል ::

7. የቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫ

ሰሜን ፡- ዓሸቶ ካሰ ጀቤቸ ቆርቆሮ ቤት ወዴ ውጫ ሺዳርጉ በመገሰት ሻቆቅጠጪጪ ወዴ ሞሰራቅ በሚዳርግ ሃብቷ ወዴ ጋበ ጅማት ዓሚከለዳጪ በአቅር መንገዱ እዓትዋሰኒ በግሞት ፲·3 ሳ·ሚ ዓሃል ሃተጋዘ በኃላ ዓሸቶ ዕጓሃ ሂኣሳር ቤተ ወዴ ውጭ ሺዳርጉ ዓሰሚት ክለለ ዓቆመ ል ::

ምሰራቅ ፡- ዓሰሚት ክፈሃ ካቆመቦት ቦታ ለመነሻት መሬት ለመሬት እዓተወሰነ ዓመሪሮ ሊሰሮ ጉ·ማ ሳር ቤት ወዴ ውስጥ ዓሸቶ ራጋ መሪጋ ሳር ቤት ወዴ ውጭ ኤዳርጉ ጀነሽ ሃተጋዘ በኃላ ዓሸቶ ካሰ ተሸመ ሳር ቤት ወዴ ውስጥ ዓሸቶ ጀቤቸ ጥቂ ሳር ቤት ወዴ ውጭ ዓሸቶ ሻነባል ተፃ ወደጪ ቤት ውስጥ ዓሸቶ ባጋ መሪጋ ሳር ቤት ወዴ ውጫ ኤዳርጉ ወሪሶ ቀሪና ዓገጦር ቀበሌ ጅንበር ለዳርሲ ሃወሪሶ ቀሪና ዓገጦር ጋር በግሞት ዐ·6 ሳ·ሚ ዓሃል ጎዋሰኒ በኃላ ዓሸቶ በጀጀ ብርቱ ሳር ቤት ወዴ ውጭ ኤዳርጉ ዒሞስረ ቅ ክለለ ዓቦቋ ል ::

ዳቡብ ፡- ጊሞስረ ቅ ክለል ካቆመቦት ቦታ ለመነሻት ዒሞፎር ቡ ጉ ኧቅጠጪ ከመዩ ዝመሬት ለመሬት እዓተጋሰኒ ዓሸቶ ሩሰፃ መሪጋ ሣር ቤት ወዴ ውስጥ ዓመሪሮ ቀ ሃኒ ብሪቱ ሳር ቤት ወዴ ውጭ ዓመሪሮ ክለቡ ሽኳሊሁ ሳር ቤት ወዴ ውስጥ ዓመሪሮ ሊሊቱ ጋዴሳ ሳር ቤት ወዴ ውጭ ዓሸቶ ባሊቸ ካበዴ ሳር ቤት ወዴ ውስጥ አዳርጉ ጀነሽ ሃተጋዘ በኃ/ ዓሸቶ ካሰ ዴሞሰ ሳር ቤት ወዴ ውጭ ኤዳርጉ ዓዳቡ ክለለ ዓቦቋ ል ::

ምዕራብ ፡- ዓዳቡ ክለል ካቆመቦት ቦታ ለመነሻት መሬት ለመሬት እዓተቋሰኒ በግሞት ፩·ጉ ሳ·ሚ ዓሃል ሃተጋዘ ቦ ጅ/ ዓተጎሰ ቡ ዓሰሚት ክለለ ሰዳርሰ ዓሞስረ ቡ ክለለ ዓቦቋ ል ::

ማሳሰቢያ፡ የድንበር ማገናዘቢያ መለያ ነጥቦች (Reference Points) የሚሆኑት ቋሚና በግልፅ ተለይተው የሚታዩ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ገፅታዎች ሲሆኑ የሌላ ቆጠራ ቦታ ድንበር እንደድንበር ማገናዘቢያ መለያ ነጥቦች (Reference Points) መወሰድ የለባቸውም::

የካርታ ሠራተኛው ስም ፓ·ርላ· ጀቤለ ፊርማ ቀን 7/6/96

የተቆጣጣሪው ስም ቱሉ ጎለንሶላ ፊርማ ቀን 06/08/86

4.4.2 <u>የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ</u>:- የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ ያካተታቸውን የቆጠራ ቦታዎች አንጻራዊ አቀማመጥ የሚያሳይ የወረዳ ካርታ አካል ነው:: /ስዕል 3.3 ተመልከት::/

የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ የሚከተሉትን ነጥቦች በተገቢው ሥፍራቸው ማካተትና ማሳየት አለበት::

ሀ. የመቆጣጠሪያ ቦታው የሚገኝበትን ክልል፤ ዞንና ወረዳ ስሞች፤

ለ. የመቆጣጠሪያ ቦታው የሚያካትታቸው ቀበሌዎች ስምና መለያ ቁጥር፤

ሐ. የመቆጣጠሪያ ቦታው የመለያ ቁጥር፤

መ. በመቆጣጠሪያ ቦታው ውስጥ የተካተቱ የቆጠራ ቦታዎች የመለያ ቁጥርና ብዛታቸው፤

ሠ. የጠቃሚ ምልክቶች (መንደሮች፤ ት/ቤቶች፤ ቤተክርስቲያኖች፤ መስጊዶች፤ ...ወዘተ)፤

ረ. የአጐራባች መቆጣጠሪያ ቦታዎች የወሰን መገናኛ ነጥቦች እና የመለያ ቁጥሮች፤

ሰ. የሰሜናዊ አቅጣጫ አመልካች፤

ሸ. በካርታው የሠፈሩ የተለያዩ ምልክቶችን የሚያስረዳ መግለጫ /ሌጀንድ/::


ቀ. የካርታው መስፈርት፤

በ. የመቆጣጠሪያ ቦታው ካርታ ተሰርቶ የተጠናቀቀበት ቀኝ፤ የካርታ ሠራተኛውና የተቆጣጣሪው ስምና ፊርማ::

ሠዕል 4·3

ክልል...አሮሚያ
ዞን.....ደቡብ ምዕራብ ሸዋ
ወረዳ...ኢሉ

የገጠር ቀበሌ ብዛት.....1
የቆጠራ ቦታ ብዛት.....4
የመቆጣጠሪያ ቦታ መለያ ቁጥር 03



መስፈርት 1:50,000

መግለጫ

- ደዘንጅ ድንበር
- የመቆጣጠሪያ ቦታ ድንበር
- የገጠር ቀበሌ ድንበር
- የቆጠራ ቦታ ድንበር
- የእግር መንገድ
- የማይደርቅ ወንዝ
- የሚደርቅ ወንዝ
- A መንደር፣ የቀበሌ አስተዳደር ጽ/ቤት
- ፅ/ቤት፣ ክሊኒክ
- የገበያ ቦታ፣ ወፍጮ
- 005-02 የገጠር ቀበሌና ቆጠራ ቦታ መ/ቁጥር
- 03 የመቆጣጠሪያ ቦታ መ/ቁጥር

	ስም	ፊርማ	ቀን
የረዳት ካርታ ሠራተኛ	ታሪኩ ጁቤሳ		18/06/96
የተቆጣጠሪ	ቱሉ ጉሶምሳ		18/06/96

4.4.3 <u>የወረዳ ካርታ</u>:- የወረዳ ካርታ በውስጡ የሚገኙትን የቆጠራ ቦታዎች አንጻራዊ ስፍራቸውን ማሳየት ይኖርበታል። በወረዳው ጽ/ቤት ሆናችሁ የመቆጣጠሪያ ቦታዎችን ለመከለል የምትጠቀሙበት ካርታ ነው። በባለ 1:50,000 እስከ 1:250,000 መስፈርት የተሰራ የወረዳ ካርታ በስዕል 3.4 ከታየው የወረዳ ካርታ ሊተልቅ ይችላል። የወረዳው ጥበትና ስፋት የመስፈርቱን መጠን ይወስናል። የምታዘጋጁት የወረዳ ካርታ በመሬት ላይ የሚገኙ አስፈላጊ የሆኑ የማገናዘቢያ መለያ ነጥቦች (Reference points) በበቂ ሁኔታ ለማስፈር በሚያስችል ደረጃና ባልተጨናነቀ መንገድ መሆን ይኖርበታል። የወረዳ ካርታ የሚከተሉትን ነጥቦች በተገቢው ሥፍራቸው ማካተትና ማሳየት አለበት። /ስዕል 3.4ን ተመልከት/

ሀ. ወረዳው የሚገኝበት የክልል፤ የዞንና የወረዳው ስሞች፤

ለ. በወረዳው ውስጥ የሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች፤ የመቆጣጠሪያ ቦታና የቆጠራ ቦታ ብዛት፤

ሐ. የወረዳው ወሰን (እንደ ወንዞች፤ መንገዶች፤ ተራራዎች፤ ሸለቆዎች ...ወዘተ ተከትሎ የተከለለ)፤

መ. የአጐራባች ወረዳዎች ስሞችና የወሰን መገናኛ ነጥቦች፤

ሠ. በወረዳው ውስጥ የሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች ወሰኖችና ስሞች፤

ረ. በወረዳው ውስጥ የሚገኙ የቆጠራ ቦታዎች ወሰን፤ አቀማመጥና መለያ ቁጥሮች፤

ሰ. በወረዳው ውስጥ የሚገኙ የመቆጣጠሪያ ቦታዎች ወሰን፤ አቀማመጥና መለያ ቁጥሮች፤

ሸ. በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ዋና ዋና መንደሮች፤ ከተሞች ፤ ወንዞች፤ ተራራዎች፤ ጫካዎች፤ የመኪና መንገዶች፤ የእግር መንገዶች፤ የገበያ ቦታዎች፤ ታሪካዊ ሥፍራዎች፤ የኃይማኖት ማዕከሎች፤ ...ወዘተ ስሞችና አቀማመጥ፤

ቀ. የሰሜናዊ አቅጣጫ አመልካች፤


በ. በካርታው የሠፈሩ የተለያዩ ምልክቶችን የሚያስረዳ መግለጫ /ሌጀንድ/፤

ተ. የካርታ መስፈርት፤

ቸ. ካርታውን ያዘጋጀው ሠራተኛ እና ተቆጣጣሪ ስም፤ ፊርማና ሥራው የተጠናቀቀበት ቀን፤

ኀ. ካርታውን በተመለከተ አስፈላጊ የሆነ አስተያየት።

ነ. በየ10,000 ሜትር የሚገኙትን የኢስቲንግና ኖርዚንግ የግሪድ መስመሮች ቁጥራቸውን፤


የኢሉ ወረዳ የቆጠራ ካርታ
ክልል ኦሮሚያ
ዞን ደቡብ ምዕ/ሽዋ
ወረዳ ኢሉ
የገጠር ቀበሌ ብዛት 18
የመተላጠቢያ ቦታ ብዛት 11
የቆጠራ ቦታ ብዛት 60
መግለጫ
የዞን ድንበር
የወረዳ ድንበር
የመተላጠቢያ ቦታ ድግ
የንዑስ ቀበሌ ድንበር
የቆጠራ ቦታ ድንበር
የከተማ መንገድ
የማይደርቅ ወንዝ
ደረቅ ወንዝ
ሌላ ከተማ፣የአስ. ጽ/ቤት
ት/ቤት፣ ክሊኒክ
የሰመዓ ሠ.ጽ/ቤት፣ወናም ቤ
ቤተክርስቲያን፣የንዑስ ቦታ
የውሀ ቦኖ ፣ ድልድይ
012-01 የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር
012- የንዑስ ቀበሌ መ. ቁጥር
07 የመተ. ቦታ መለያ ቁጥር
መለኪያ 1:288,623
ወረዳ
ዞን
ክፍለ ሀገር

4.5 በገጠር አካባቢዎች የካርታ ሥራ ቅጾች ዓይነትና ይዘት

4.5.1 ቅጽ ገ-1:- በወረዳ ውስጥ የሚገኙትን የገጠር ቀበሌዎች መመዝገቢያ ቅጽ:-

ይህ ቅጽ በወረዳ ውስጥ የሚገኙትን ጠቅላላ የገጠር ቀበሌዎች መመዝገቢያ ሲሆን ምዝገባው የሚካሄደው በወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ነው:: ዝርዝሩ የተሟላና ትክክል መሆኑን ለማረጋገጥ በመስክ ሥራ ወቅት አስፈላጊው ማጣራትና ዕርማት ይደረጋል::

ክፍል 1:- የአካባቢ መለያ

አምድ 1-3:- ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ:- በእነዚህ አምዶች የገጠር ቀበሌዎች የሚገኙበት የክልል፣ የዞንና የወረዳ ስሞች ይጻፋል:: ንዑስ ዓምዶች (ካርድ ኮለሞች) 1-6 ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግሉ ምንም አይሞሳባቸውም::

ክፍል 2:- የገጠር ቀበሌዎች ዝርዝር

አምድ 4:- የአካባቢ ስም:- በዚህ አምድ አንድ ወይም ከዚያ በላይ የገጠር ቀበሌዎች የሚጠሩበት የአካባቢ መጠሪያ ስም ይጻፋል:: በአንድ የአካባቢ ሥም የተለያዩ የገጠር ቀበሌዎች የሚጠሩ ከሆነ ለእያንዳንዱ የገጠር ቀበሌ የአካባቢው ስም በመደጋገም ይፃፋል:: አንድ አካባቢ ከአንድ በላይ መጠሪያ ስም ካለው መጀመሪያ በወረዳው አስተዳደር እና በአካባቢው ነዋሪዎች የሚታወቀው ስሙ ተጽፎ ሌላው ስሙ ደግሞ በቅንፍ ውስጥ ይፃፋል:: አካባቢው አንድ የገጠር ቀበሌ ብቻ የያዘ ከሆነና የሁለቱም መጠሪያ አንድ ከሆነ በአምድ 4 እና በአምድ 6 የሚፃፈው ስም አንድ አይነት ይሆናል::

አምድ 5:- ተራ ቁጥር:- በዚህ ዓምድ/በንዑስ ዓምዶች 7-9/ በአምድ 6 ለሚመዘገቡ የገጠር ቀበሌዎች በሙሉ ከ001 በመጀመር ባለሦስት አሀዝ ተከታታይ ቁጥር ይሰጣል::

አምድ 6:- የገጠር ቀበሌ ስም:- በዚህ ዓምድ በወረዳ ውስጥ የሚገኙት የገጠር ቀበሌዎች ስም የሚጻፍበት ነው:: ከአንድ በላይ ስም ላላቸው የገጠር ቀበሌዎች መጀመሪያ በአካባቢው የተለመደው ስም ተጽፎ ሁለተኛው ስም ደግሞ በቅንፍ ይፃፋል::

አምድ 7:- መለያ ቁጥር:- በአምድ 6 ለተመዘገበው የገጠር ቀበሌ የመለያ ቁጥር በዚህ ዓምድ በንዑስ አምዶች 10-12 ይሞላል ::

አምድ 8:- የገጠር ቀበሌ ሊቀመንበር/ተወካይ የኃላፊነት ደረጃ:- በዚህ ዓምድ የገጠር ቀበሌ ማህበሩን ከወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤት ጋር እንደ ድልድይ የሚያገናኘው ኃላፊ የሥልጣን ደረጃ ምን እንደሆነ ተጠይቆ ይጻፋል:: ለምሣሌም ሊቀመንበር፣ ምክትል ሊቀመንበር፣ ፀሐፊ፣ የገጠር ቀበሌ ማህበሩ የኮሚቴ አባል፣ ...ወዘተ::

አምድ 9:- <u>የገጠር ቀበሌ ሊቀመንበር/ተወካይ ስም</u>:- ከላይ በአምድ 8 የኃላፊነት ደረጃ የተጠቀሰለት ሰው ሙሉ ስም በዚህ ዓምድ ይጻፋል::

አምድ 10:- <u>አስተያየት</u>:- ከአምድ 4-9 ድረስ ለተሞሉት መረጃዎች ተጨማሪ ማብራሪያ አስፈላጊ ከሆነ በዚህ ዓምድ ተገቢውን አስተያየት ማስፈር ያስፈልጋል:: የተሰጠው ቦታ የሚያንስ ከሆነ የቅጹን ጀርባ መጠቀምና አስተያየቱ ግን ለየትኛው የገጠር ቀበሌ እንደተሰጠ የገጠር ቀበሌውን ስም ወይም ተራ ቁጥር በመጥቀስ በግልጽ ማሳወቅ ያስፈልጋል::

<u>ጠቅላላ የገጠር ቀበሌዎች ብዛት፤ የገፅ ድምርና ጠቅላላ ድምር</u>:- በወረዳው የሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች ምዝገባ ከተጠናቀቀ በኋላ በቅጹ የቀኝ ግርጌ በተሰጠው ክፍት ቦታ ብዛታቸው ተቆጥሮ ይሞላል:: ከአንድ በላይ ቅፅ መጠቀም አስፈላጊ ሲሆን በየገፁ ያለው የገፅ ድምርና በመጨረሻው ገፅ ላይ ደግሞ ጠቅላላ ድምር መሞፍ ይኖርበታል::

በመጨረሻም የካርታ ሠራተኛው ስም፤ ፊርማና ምዝገባው የተጠናቀቀበት ቀን በተሰጠው ክፍት ቦታ ይሞላል:: ለምዝገባው ትክክለኛነት ማረጋገጫ ተቆጣጣሪውም ቅጹን ከመረመረ በኋላ በተመሳሳይ መንገድ ስሙን ፊርማውንና ቁጥሩን የፈፀመበትን ቀን በተሰጠው ቦታ ያሰፍራል::

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

በወረዳ ውስጥ የሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች

መመዝገቢያ ቅጽ

ቅጽ ገ-1

ክፍል 1: የአካባቢ መለያ

1			2			3		
ክልል	1	2	ዞን	3	4	ወረዳ	5	6

ክፍል 2: የገጠር ቀበሌዎች ዝርዝር

4	5			6	7			8	9	10
	የገጠር ቀበሌው							የገጠር ቀበሌው ተወካይ		አስተያየት
የአካባቢው ስም	ተራ ቁጥር			ስም	መለያ ቁጥር			የኃላፊነት ደረጃ	ስም	
	7	8	9		10	11	12			

4.5.2 ቅጽ ገ-2:- <u>የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅጽ</u>:-

ይህ ቅጽ የቆጠራ ቦታዎችን ለመመሥረት እንዲያስችል ቤተሰቦችን ለመመዝገብ የሚያገለግል ቅጽ ነው:: በገጠር ቀበሌ ውስጥ የሚካሄደው የቤተሰብ ምዝገባ ቤተሰቦች ሳይዘለሉና ሳይደገሙ ከቤት ቤት በመሄድ ይከናወናል:: የቆጠራ ቦታ መከለል ከመከናወኑ በፊት በገጠር ቀበሌው ውስጥ የሚገኙት ቤተሰቦች በሙሉ በሚገኙበት መንደር እና የታሳቢ የቆጠራ ቦታዎችን ምሥረታ ግምት ውስጥ በማስገባት መመዝገብ ይኖርባቸዋል::

ከመቶ በታች ነዋሪዎች በሚገኙባቸው የገጠር የጋርዮሽ መኖሪያዎች ውስጥ የሚገኙ ራሳቸውን የቻሉ ቤተሰቦችና የጋርዮሽ መኖሪያው ስም በውስጡ ከሚኖሩት ነዋሪዎች ብዛት ጋር በቅጽ ገ-2 ላይ መመዝገብ ይኖርባቸዋል::

ክፍል 1:- <u>የአካባቢ መለያ</u>

አምድ 1-5:- <u>ክልል፤ ዞን፤ ወረዳ፤ የገጠር ቀበሌና የተወካይ ስም</u>:- በአምድ 1-4 የክልሉ፤ የዞኑ፤ የወረዳውና የገጠር ቀበሌው ስሞች ይጻፋሉ:: በአምድ 5 ደግሞ የገጠር ቀበሌ ማህበሩ ተወካይ/ኃላፊ ስም ይጻፋል:: ንዑስ አምዶች 1-6 በቢሮ የሚሞሉ ስለሆነ ባዶ ይተዋሉ:: በንዑስ አምዶች 7-9 የገጠር ቀበሌው መለያ ቁጥር ይመዘግባል::

አምድ 6:- <u>የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር</u>:- የቆጠራ ቦታው መለያ ቁጥር በንዑስ አምዶች 10-11 ይመዘግባል::

ክፍል 2:- <u>የቤተሰቦች/የጋርዮሽ መኖሪያዎች ዝርዝር</u>

አምድ 7:- <u>የመንደር ስም</u>:- በዚህ ዓምድ በገጠር ቀበሌው ውስጥ ያሉ ቤተሰቦች የሚገኙበት የመንደር ስም ይጻፋል::

አምድ 8:- <u>ተራ ቁጥር</u>:- በአምድ 9 ለሚመዘገቡ ቤተሰቦች/የጋርዮሽ መኖሪያዎች በዚህ ዓምድ በንዑስ አምዶች 12-14 ከ001 በመጀመር ባለሦስት አሀዝ ተከታታይ ተራ ቁጥር ይሰጣል:: የተራ ቁጥሩ አሰጣጥ በእያንዳንዱ የቆጠራ ቦታ ውስጥ ይሆንና በገጠር ቀበሌው የሚገኙት ቤተሰቦች በሙሉ ሊመዘገቡና ተራ ቁጥር ሊሰጣቸው ይገባል::

አምድ 9:- <u>የቤተሰብ ኃላፊ/የጋርዮሽ መኖሪያ ስም</u>:- በዚህ ዓምድ የቤተሰቡን ኃላፊ/የጋርዮሽ መኖሪያውን መጠሪያ ሙሉ ስም ይጻፋል:: የቤተሰብ ኃላፊው ስም ከመጻፉ በፊት ለቤተሰብ ኃላፊና ለመደበኛ የቤተሰብ አባል በምዕራፍ 2 የተሰጠውን ትርጉም ማጤን ይገባል::

አምድ 10:- <u>የቤተሰብ/የጋርዮሽ መኖሪያ አባላት</u>:- በዚህ ዓምድ የቤተሰቡን መደበኛ አባላት ብዛት /ኃላፊውን ጨምሮ/ በጾታ በመለየት ይጻፋል:: በተጨማሪም ከ100 በታች ነዋሪዎችን በያዘ የጋርዮሽ መኖሪያ የሚኖሩ አባላት ብዛት በጾታ በመለየት ይጻፋል:: የወንዶች ብዛት በንዑስ አምዶች 15-16፤ የሴቶች ብዛት በንዑስ ዓምዶች 17-18 እንዲሁም የሁለቱ ድምር በንዑስ አምዶች 19-20 ይሞላል:: እነዚህ ንዑስ አምዶች ሲሞሉ መደበኛ የቤተሰብ አባላት የሚባሉት እነማን እንደሆኑ ማወቅ ጠቃሚ ነው::

ስለ መደበኛ የቤተሰብ አባላት እና የጋርዮሽ መኖሪያ አባላት ትርጉም በምዕራፍ 2 የተሰጠውን የፅንሰ-ሀሳቦች ፍቺ ጠንቅቆ መረዳት ያስፈልጋል::

አምድ 11:- <u>በቤተሰቡ ውስጥ የጎጆ/ዕደ-ጥበብ ማምረቻ ድርጅት የሚያንቀሳቅስ አባል አለ?</u> በዓምድ 9 ተራ ቁጥር ተሰጥቶት ከተመዘገበው ቤተሰብ ውስጥ የጎጆ/ዕደ-ጥበብ ማምረቻ ድርጅት የሚያንቀሳቅስ አባል ካለ አለ ተብሎ ኮድ "1" ከሌለ ደግሞ የለም ተብሎ ኮድ "2" በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል::

ይህ ዓምድ ከመሞላቱ በፊት ከዚህ በታች የተገለጹትን የድርጅት፤ ማምረት(ማምረቻ) እና የጎጆ/ዕደ-ጥበብ ማምረቻ ድርጅት ትርጉምን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል::

1. <u>ድርጅት</u>:- ድርጅት ማለት በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ያለው አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ የማኅበራዊ ወይም የኢኮኖሚ ተቋም ነው:: ይኸውም የማምረቻ፤ የአገልግሎትና የንግድ ተቋሞችን ያጠቃልላል:: ለምሳሌ ጫማ፤ ዳቦ፤ ጨርቃ ጨርቅ፤ ... ወዘተ አምራቾች፤ የጫማ ዕድሳት፤ የትራንስፖርት፤ የጤና፤ የትምህርት፤ የሕግ፤ የምግብና የመጠጥ አገልግሎት እና ልዩ ልዩ ሽቀጣ ሽቀጥ ንግድ የሚያካሂዱትን ሁሉ ያጠቃልላል::

2. <u>ማምረት (ማምረቻ)</u>:- የጥሬ ዕቃዎችን ወይም የመገጣጠሚያዎችን ቅርጽ ወይም/እና ይዘት መካኒካዊ ወይም ኬሚካላዊ የሆነ ዘዴ በመጠቀም ወደ አዲስ ውጤት የመለወጥና የአካል መገጣጠም ሥራዎችን የማከናወን ተግባር ነው:: ከዚህ በተጨማሪም የደንበኞችን ጥሬ ዕቃ በመጠቀም የማምረት አገልግሎት የሚሰጡ እንደ ልብስ ስፌት፤ የተለያዩ ቅርጽ በማውጣት የብረታ ብረትና የእንጨት ውጤቶችንና የመሳሰሉትን ሥራዎች የሚያከናውኑ እንደ ማምረት ሥራ ይቆጠራሉ::

ለምሣሌ፡- የዳቦ መጋገር፡ የእንጀራ መጋገር፡ ኬክ ማምረት፡ ዱቄት ማምረት፡ መኮሮኒ ማምረት፡ የድንች ጥብስ(ቺፕስ) ማምረት፡ ጠላ መጥመቅ፡ አረቄ ማውጣት፡ ብቅል ማምረት፡ የልብስ ስፌት፡ የስንደዶ ስፌት፡ የሽመና ሥራ፡ የፈትል ሥራ፡ የሹራብ ሥራ፡ የጥልፍ ሥራ፡ የሥጋጃና የሰሌን ሥራ፡ የፈረስ ኮርቻዎች መሥራት፡ የሕትመት ሥራ፡ ቆዳ ማልፋትና መፋቅ፡ መድኃኒት ማምረት፡ የጫማ ሥራ፡ ቆርቆሮ ማምረት፡ የቤት ዕቃዎችና ጌጣጌጦችን በሸክላ መሥራት፡ ሸክላ ማምረት፡ ከሸንበቆና ከቀርከሃ የተሠሩ ጊጣጌጦችና ቅርጫቶች ማምረት፡ ድንጋይን በተለያየ ቅርጽ መጥረብና ማዘጋጀት፡ የአንጥረኛ ሥራዎች፡ በቅጥቀጣና ብየዳ ማረሻዎች፡ መጥረቢያዎችና ቢላዋዎች የመሳሰሉትን ማምረት፡ የቤትና የቢሮ ዕቃዎችን ከተለያዩ ጥሬ ዕቃዎች ማመረትና ሌሎችም ብዛት ያላቸውን የማምረት ሥራዎችን ያካትታል።

ማስታወሻ፡- የቡና ማበጠሪያና መፈልፈያዎች እንደማምረቻ እንደማይቆጠሩ ማስተዋል ያስፈልጋል።

3. የጎጆ/ዕደ-ጥበብ ማምረቻ ድርጅት፡- የሚባለው በአንድ ስፍራ የተለየ አድራሻ ያለው፡ አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ ሆኖ አብዛኛው ምርቱን በእጅ ወይም በእግር (በሰው ኃይል) የሚንቀሳቀስ መሣሪያ በመጠቀም አንድ ወይም የተለያዩ ምርቶችን ለገበያ የሚያመርት የሥራ መስክ ነው።

የገፅ ድምርና ጠቅላላ ድምር፡- የነዋሪዎችን ብዛት በጾታ ለይቶ በመደመር በቅጹ ላይ በየገጹ በአምድ 10 ግርጌ "የገጾች ድምር" በሚለው ቦታ ላይ መስፈር ይኖርበታል። ከዚያም በቆጠራ ቦታው ውስጥ የሚከናወነው ምዝገባ ከተጠናቀቀ በኋላ ጠቅላላ ድምር በቅጹ የመጨረሻ ገጽ ላይ በተሰጠው ክፍት ቦታ መስፈር ይኖርበታል።

በመጨረሻም ቅጹን የሞላው ካርታ ሠራተኛና ተቆጣጣሪው ስማቸውን፡ ፊርማቸውንና ምዝገባው የተጠናቀቀበትን ቀን በተሰጠው ክፍት ቦታ ያስፍራሉ።

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

የቤተሰብ መመዝገቢያ ቅፅ

ቅፅ ገ-2

ክፍል 1:- የአካባቢ መለያ

1			2			3			4				5	6		
ክልል	1	2	ዞን	3	4	ወረዳ	5	6	የገጠር ቀበሌ	7	8	9	የገጠር ቀበሌ ተወካይ	የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር	10	11

ክፍል 2:- የቤተሰቦች/የጋርዮሽ መኖርያዎች ዝርዝር

7	8			9	10							
የመንደር ስም	ተራ ቁጥር			የቤተሰብ ኃላፊ/የጋርዮሽ መኖሪያ ስም	የቤተሰብ አባላት/የጋርዮሽ ነዋሪዎች ብዛት						በቤተሰቡ ውስጥ የጎጂ/ዕደ ጥበብ ድርጅት የሚያንቀሳቅስ አባል አለ?	
					ወንድ		ሴት		ድምር		1 - አለ 2 - የለም	
	12	13	14		15	16	17	18	19	20		ኮድ

4.5.3 ቅጽ ገ-3:- <u>የጋርዮሽ መኖሪያዎች መመዝገቢያ ቅጽ</u>:-

ይህ ቅጽ በወረዳው ውስጥ የሚገኙትን የገጠር የጋርዮሽ መኖሪያዎች በሙሉ ለመመዝገብ ያገለግላል:: በዚህ ቅጽ የሚመዘገቡት የጋርዮሽ መኖሪያዎች ትንሽ ወይም ትልቅ ማለትም ከ100 በታች ወይም በላይ ነዋሪዎች የሚኖሩባቸው ሊሆኑ ይችላሉ:: ይህ ቅጽ የሚሞላው ወረዳው ላይ (አስተዳደር ጽ/ቤት) ሲሆን በመስክ ሥራ ወቅት ግን የማጣሪያ ሥራ ይከናወናል:: በመስክ ሥራ ወቅት በወረዳ ጽ/ቤት በተደረገው ምዝገባ ያልተመዘገቡ የጋርዮሽ መኖሪያዎች መኖራቸው ሲረጋገጥ ወዲያውኑ በቅጹ ውስጥ መመዝገብ ያስፈልጋል::

ክፍል 1:- <u>የአካባቢ መለያ</u>

አምድ 1-3:- <u>ክልል፤ ዞን፤ ወረዳ</u>:- በእነዚህ አምዶች የጋርዮሽ መኖሪያው የሚገኝበትን የክልል፤ የዞንና የወረዳ ስሞች ይፃፋል:: ንዑስ አምዶች 1-6 ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግሉ ምንም አይሞላባቸውም::

ክፍል 2:- <u>የጋርዮሽ መኖሪያ ዝርዝር መረጃ</u>

አምድ 4:- <u>ተራ ቁጥር</u>:- በዚህ ዓምድ (በንዑስ አምዶች 7-8) ለጋርዮሽ መኖሪያዎች ባለ ሁለት አሀዝ ተከታታይ ቁጥር ይሰጣል:: ይህም ማለት ለመጀመሪያው 01፤ ለሁለተኛው 02፤ ለሦስተኛው 03፤ ...ወዘተ በማለት በወረዳው የገጠር ክፍል ለሚገኙት የጋርዮሽ መኖሪያዎች በሙሉ ተራ ቁጥር ይሰጣቸዋል::

አምድ 5-6:- <u>የጋርዮሽ መኖሪያው ስምና አድራሻ</u>:- በዚህ ዓምድ የጋርዮሽ መኖሪያው ሙሉ ስምና አድራሻው/የፓስታ ሣጥን ቁጥር፤ የስልክ ቁጥር፤ ...ወዘተ/ ይመዘገባል::

አምድ 7:- <u>የጋርዮሽ መኖሪያው አገልግሎት</u>:- በዚህ አምድ የጋርዮሽ መኖሪያው የሚሰጠው የአገልግሎት ዓይነት በግልጽ ይፃፋል:: ለምሣሌ አዳሪ ት/ቤት፤ የጤና አገልግሎት ማሰልጠኛ፤ የኃይማኖት ድርጅት፤ ወህኒ ቤት፤ ገዳም፤ ...ወዘተ:: ንዑስ አምድ 9 ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም::

አምድ 8:- <u>የነዋሪዎች ብዛት</u>:- በዚህ አምድ በጋርዮሽ መኖሪያው ውስጥ የሚኖሩትን ነዋሪዎች ብዛት በጾታ በመለየት ይጻፋል:: የወንዶችን ብዛት በንዑስ አምዶች 10-12፤ የሴቶችን ብዛት በንዑስ አምዶች 13-15 የሁለቱን ድምር ደግሞ በንዑስ አምዶች 16-18 ይሞላል::

አምድ 9:- <u>የገጠር ቀበሌው ስምና የመለያ ቁጥር</u>:- በዚህ አምድ የጋርዮሽ መኖሪያው የሚኝበትን የገጠር ቀበሌ ስም እንዲሁም የመለያ ቁጥሩን በንዑስ ዓምዶች 19-21 ይሞላል::

አምድ 10:- <u>የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር</u>:- ይህ አምድ የሚሞላው የቆጠራ ቦታው ማካለል ሲጠናቀቅ ነው:: የጋርዮሽ መኖሪያው በመደበኛ የቆጠራ ቦታ ውስጥ የታቀፈ ወይም ልዩ የቆጠራ ቦታ የወጣው ሊሆን ይችላል:: ስለሆነም ተገቢው የመለያ ቁጥር በንዑስ አምዶች 22-23 ይመዘገባል::

አምድ 11:- <u>አስተያየት</u>:- በዚህ አምድ ቀደም ብለው ለተሞሉ መረጃዎች ተጨማሪ አስተያየት ካለ ይሰፍራል::

በመጨረሻም የካርታ ሠራተኛውና ተቆጣጣሪው ስማቸውን፤ ፊርማቸውንና ቅጹ የተጠናቀቀበትን ቀን በተሰጠው ክፍት ቦታ ማስፈር ይኖርባቸዋል::

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
በገጠር የጋርዮሽ መኖሪያዎች መመዝገቢያ ቅጽ

ቅጽ ገ-3

ክፍል 1: የአካባቢ መለያ

1			2			3		
ክልል	1	2	ዞን	3	4	ወረዳ	5	6

ክፍል 2: የጋርዮሽ መኖሪያ ዝርዝር መረጃ

4		5	6	7	8									9				10		11
ተራ ቁጥር		የጋርዮሽ መኖሪያው			የነዋሪዎች ብዛት									የገጠር ቀበሌው				የቆጠራ ቦታ		አስተያየት
		ስም	አድራሻ	አገልግሎት	ወንድ			ሴት			ድምር									
7	8				9	10	11	12	13	14	15	16	17	18	ስም	19	20	21	22	23	

የካርታ ሠራተኛው ስም_____ ፊርማ _____ቀን _____

የተቆጣጣሪው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____

4.5.4 ቅጽ ገ-4:- <u>የልዩ ቆጠራ ቦታ መመዝገቢያ ቅጽ</u>:- /100ና ከዚያ በላይ ነዋሪዎች ያሉባቸው የጋርዮሽ መኖሪያዎች/

ይህ ቅጽ 100 እና ከዚያ በላይ ነዋሪዎች የሚኖሩበትን የጋርዮሽ መኖሪያ ዝርዝር መረጃና በዚያው ውስጥ የሚገኙትን መደበኛ ቤተሰቦች መመዝገቢያ ነው::

ክፍል 1:- <u>የአካባቢ መለያ</u>:-

ዓምድ 1-3:- <u>ክልል፤ ዞን፤ ወረዳ</u>:- በእነዚህ ዓምዶች የጋርዮሽ መኖሪያው የሚገኝበት ክልል፤ ዞንና ወረዳ ስሞች ይጻፋል:: ንዑስ ዓምዶች 1-6 ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግሉ ምንም አይሞላባቸውም::

ዓምድ 4:- <u>የገጠር ቀበሌ</u>:- በዚህ ዓምድ የጋርዮሽ መኖሪያው የሚገኝበት የገጠር ቀበሌ ስም ይጻፋል:: የገጠር ቀበሌው መለያ ቁጥር ደግሞ በንዑስ ዓምዶች 7-9 ይፃፋል::

ዓምድ 5:- <u>ልዩ የቆጠራ ቦታ</u>:- በዚህ ዓምድ /በንዑስ ዓምዶች 10-11/ የልዩ ቆጠራ ቦታው መለያ ቁጥር ይመዘገባል::

ዓምድ 6:- <u>የጋርዮሽ መኖሪያው ስም</u>:- በዚህ ዓምድ የጋርዮሽ መኖሪያው መጠሪያ ሙሉ ስም ይጻፋል::

ዓምድ 7:- <u>የጋርዮሽ መኖሪያው አገልግሎት</u>:- በዚህ ዓምድ የጋርዮሽ መኖሪያው የሚሰጠው አገልግሎት ይጻፋል::

<u>ዓምድ 8</u>:- <u>የፖስታ ሣጥን ቁጥር</u>:- በዚህ ዓምድ የጋርዮሽ መኖሪያው የፖስታ ሣጥን ቁጥር /ካለው/ ይመዘገባል::

ክፍል 2:- <u>የጋርዮሽ መኖሪያው ነዋሪዎች/የቤተሰብ አባላት ብዛት</u>

ዓምድ 9:- <u>ጠቅላላ የነዋሪዎች ብዛት</u>:- በዚህ ዓምድ የጋርዮሽ መኖሪያው ነዋሪዎች /የመደበኛ ቤተሰብ አባላትን ሳይጨምር/ ብዛት በጾታ ተለይቶ ይመዘገባል:: የወንዶች ብዛት በንዑስ ዓምዶች 12-15፤ የሴቶች ብዛት በንዑስ ዓምዶች 16-19 እና ጠቅላላ ብዛት ደግሞ በንዑስ ዓምዶች 20-23 ይሞላል::

ዓምድ 10:- <u>ጠቅላላ የመደበኛ ቤተሰብ አባላት ብዛት</u>:- በዚህ ዓምድ በጋርዮሽ መኖሪያው ውስጥ የሚገኙ የመደበኛ ቤተሰብ አባላት ብዛት በጾታ ተለይቶ ይጻፋል:: ይህ

መረጃ በጋርዮሽ መኖሪያው የሚገኙ ቤተሰቦች በሙሉ ከተመዘገቡ በኋላ የአባላቱን ብዛት በጾታ ለይቶ በመደመር ይገኛል :: የወንዶች ብዛት በንዑስ ዓምዶች 24-26፤ የሴቶች ብዛት በንዑስ ዓምዶች 27-29፤ ጠቅላላ ብዛት ደግሞ በንዑስ ዓምዶች 30-32 ይመዘገባል::

ክፍል 3:- <u>በጋርዮሽ መኖሪያው ውስጥ የሚገኙ መደበኛ ቤተሰቦች ዝርዝር</u>

በዚህ ክፍል የሚገኙ ዓምዶች (ከዓምድ 11-14) የሚሞሉት በጋርዮሽ መኖሪያው ውስጥ መደበኛ ቤተሰቦች ካሉ ብቻ ነው::

ዓምድ 11:- <u>ተራ ቁጥር</u>:- በዚህ ዓምድ (በንዑስ ዓምዶች 33-34) በጋርዮሽ መኖሪያው ለሚገኙ መደበኛ ቤተሰቦች ከ01 በመጀመር ባለሁለት አሀዝ ተከታታይ ተራ ቁጥር ይሰጣል::

ዓምድ 12:- <u>የቤተሰብ ኃላፊ ስም</u>:- በዚህ ዓምድ የእያንዳንዱን በጋርዮሽ መኖሪያው ውስጥ የሚገኘውን መደበኛ ቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም ይጻፋል::

ዓምድ 13:- <u>የቤተሰብ አባላት ብዛት</u>:- በዚህ ዓምድ በእያንዳንዱ ቤተሰብ ውስጥ የሚገኙ መደበኛ አባላት ብዛት በጾታ በመለየት ይመዘገባል:: የወንዶች ብዛት በንዑስ ዓምዶች 35-36፤ የሴቶች ብዛት በንዑስ ዓምዶች 37-38፤ ጠቅላላ ብዛት ደግሞ በንዑስ ዓምዶች 39-40 ይመዘገባል::

ዓምድ 14:- <u>አስተያየት</u>:- ስለ ጋርዮሽ መኖሪያውና ስለቤተሰቦች ተጨማሪ አስተያየት ካለ በዚህ ዓምድ ይጻፋል::

በመጨረሻም የካርታ ሠራተኛውና ተቆጣጣሪው ስማቸውን፤ ፊርማቸውንና ቅጹ የተጠናቀቀበትን ቀን በተሰጠው ክፍት ቦታ ማስፈር ይኖርባቸዋል::

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

የልዩ ቆጠራ ቦታ መመዝገቢያ ቅፅ

(100ና በላይ ነዋሪዎች ያሉባቸው የጋርዮሽ መኖሪያዎች)

ቅፅ ገ-4

ክፍል 1:- የአካባቢ መለያ

1			2			3			4				5			6	7	8
ክልል			ዞን			ወረዳ			የገጠር ቀበሌ ስም				የቆጠራ ቦታ			የጋርዮሽ መኖሪያው		
	1	2		3	4		5	6		7	8	9		10	11	ስም	አገልግሎት	አድራሻ

ክፍል 2:- ጋርዮሽ መኖርያው ነዋሪዎች/የቤተሰብ አባላት ብዛት

9. ጠቅላላ የነዋሪዎች ብዛት	ወንድ				ሴት				ድምር			
	12	13	14	15	16	17	18	19	20	21	22	23

10. ጠቅላላ የመደበኛ ቤተሰብ አባላት ብዛት	ወንድ			ሴት			ድምር		
	24	25	26	27	28	29	30	31	32

ክፍል 3:- በጋርዮሽ መኖሪያ ውስጥ የሚገኙ መደበኛ ቤተሰቦች ዝርዝር

11		12	13					
ተራ ቁጥር		የቤተሰብ ኃላፊ ስም	የቤተሰብ አባላት ብዛት					
			ወንድ		ሴት		ድምር	
33	34		35	36	37	38	39	40

14. አስተያየት _____

_____

የካርታ ሠራተኛው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____

የተቆጣጣሪው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____

4.5.5 ቅጽ ገ-5፡- <u>የገጠር ቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫ ቅጽ</u>

ይህ ቅጽ ለተከለለው የገጠር ቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫ መጻፊያ ያገለግላል። የቆጠራ ቦታው ድንበር ሲገለፅ በቆጠራ ቦታው ወሰን ውጪና ውስጥ የሚገኙ ቋሚ የሆኑ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ምልክቶችን መጠቀም ያስፈልጋል። በተቻለ መጠን ፈራሽና ጊዜያዊ የሆኑ ምልክቶችን /ለምሣሌ፡- ጊዜያዊ መጠለያዎች፡ ዛፎች፡ ...ወዘተ/ መጠቀም አያስፈልግም። በተጨማሪ የድንበር መግለጫ ሲፃፍ መታወስ ያሚገባው የቆጠራ ቦታ ካርታው ቢያንስ ለመጪዎቹ አሥር ዓመታት የሚያገለግል መሆኑን ነው። ስለ ቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫ ከመጻፉ በፊት ወደቆጠራ ቦታው እንዴት መድረስ እንደሚችል አጠር ያለ መግቢያ በቅጹ ላይ በተሰጠው ባዶ ቦታ መፃፍ ይኖርበታል። የድንበር መግለጫው በማያሻማና በቀላሉ ሊነበብ በሚችል የእጅ ጽሑፍ ሊጻፍ ይገባል። ከዚያም የድንበር መግለጫው ሲጻፍ በቆጠራ ቦታው የሰሜን አቅጣጫ በመጀመር በምሥራቅ፡ በደቡብና በምዕራብ አካሄድ ዞሮ መነሻው ሥፍራ እስኪገኘም ድረስ ያሉትን የድንበር መለያ ነጥቦች ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

ክፍል 1፡- <u>የአካባቢ መለያ</u>

አምድ 1-3፡- <u>ክልል፡ ዞንና ወረዳ</u>፡- በእነዚህ አምዶች የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ክልል፡ ዞንና ወረዳ ስሞች ይጻፋሉ። ንዑስ ዓምዶች 1-6 ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግሉ ምንም አይሞላባቸውም።

አምድ 4፡- <u>የገጠር ቀበሌ</u>፡- በዚህ አምድ የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት የገጠር ቀበሌ ስም ይጻፋል። የገጠር ቀበሌው መለያ ቁጥር ደግሞ በንዑስ ዓምዶች 7-9 ይሞላል።

አምድ 5፡- <u>የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር</u>፡- በዚህ አምድ የቆጠራ ቦታው መለያ ቁጥር ይመዘገባል።

ክፍል 2፡- <u>የቆጠራ ቦታ መግለጫ</u>፡-

አምድ 6፡- <u>መግቢያ</u>፡- በዚህ ሥፍራ ከቀበሌ ጽ/ቤት ተነስቶ ወደ ቆጠራ ቦታው እንዴት መድረስ እንደሚቻል የሚያስረዳ አጠር ያለ መግለጫ ይፃፋል።

አምድ 7፡- <u>የድንበር መግለጫ ዕሁፍ</u>፡- የቆጠራ ቦታው መግለጫ ሲጻፍ ከሰሜናዊ አቅጣጫ በመነሳት ወደ ምሥራቅ፡ ወደ ደቡብና ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመሄድ ይሆናል። የድንበር መግለጫው ጽሁፍ ሲፃፍ የቆጠራ ቦታው ድንበር መነሻ ነጥብ በሚገባ መገለፅ ይኖርበታል። ይህ ቅጽ ከተሞላ በኋላ ከቆጠራ ቦታ ካርታ ጋር ይያያዛል። ተጨማሪ ቅጽ የሚያስፈልግ ከሆነ ጨምሮ በመጠቀም ለእያንዳንዱ ገጽ ቁጥር በመስጠት አንድ ላይ መያያዝ ይኖርበታል።

በመጨረሻም በተሰጠው ክፍት ቦታ የካርታ ሠራተኛውና ተቆጣጣሪው ስማቸውን፡ ፊርማቸውንና ሥራው የተጠናቀቀበትን ቀን በተሰጠው ክፍት ቦታ ማስፈር ይኖርባቸዋል።

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

የገጠር ቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫ ቅፅ

ቅፅ ገ-5

ክፍል 1፡- የአካባቢ መለያ

1			2			3			4			5		
ክልል	1	2	ዞን	3	4	ወረዳ	5	6	የገጠር ቀበሌ	7	8	የቆጠራ ቦታ	9	10

ክፍል 2፡- የቆጠራ ቦታ መግለጫ

6. መግቢያ _____

_____

_____

_____

7. የድንበር መግለጫ ዕሁፍ

_____

_____

_____

4.5.6 ቅፅ ገ-6:- በገጠር የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባብ መመዝገቢያ ቅፅ

ይህ ቅፅ በገጠር ካርታ ሥራ ወቅት ለገጠር ቀበሌዎችና ለቆጠራ ቦታዎች የድንበር ነጥቦች፡ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ገፅታዎች እና የቆጠራ ቦታ ድንበር መለያ ነጥቦች የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባቦችን ለመመዝገብ ያገለግላል። ይህን ቅፅ ለገጠር ቀበሌ የድንበር ነጥቦች ኮኦርዲኔቶች መመዝገቢያ በምንጠቀምበት ወቅት በክፍል 1 ዓምድ 4 የቀበሌው ስም ተጽፎ፡ በዓምድ 5 የቆጠራ ቦታ ዓምድ ደግሞ በሰረዝ "__" ይታለፋል። የጂ.ፒ.ኤስ ንባቡ በቆጠራ ቦታዎች ውስጥና ድንበር ላይ የተወሰደ ከሆነ ደግሞ በክፍል 1 ዓምድ 5 የቆጠራ ቦታው መለያ ቁጥር ተፅፎ በክፍል 2 ባሉት ዓምዶች አስፈላጊው የኮርዲኔቶች ንባብ ዝርዝር መረጃ ይመዘገባል።

ክፍል 1:- የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1-5:- ክልል፡ ዞን፡ ወረዳ፡ የገጠር ቀበሌ፡ የቆጠራ ቦታ

በእነዚህ ዓምዶች የቆጠራ ካርታ ሥራው የሚካሄድበት ክልል፡ ዞን፡ ወረዳ፡ የገጠር ቀበሌ ስሞችና የቆጠራ ቦታው መለያ ቁጥር ይፃፋል። በንዑስ ዓምዶች 1-6 ምንም የማይሞላ ሲሆን በንዑስ ዓምዶች 7-9 የገጠር ቀበሌው ቁጥር፡ በንዑስ ዓምዶች 10-11 ደግሞ የቆጠራ ቦታው መለያ ቁጥር ይፃፋል።

ክፍል 2:- ለድንበር ነጥቦች የጂ.ፒ.ኤስ መረጃዎች ዝርዝር

ዓምድ 6:- የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባብ ተራ ቁጥር

በዚህ ዓምድ የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔት ንባብን ቅደም ተከተል የሚያመለክት ተራ ቁጥር ይፃፋል።

ዓምድ 7:- መግለጫ

በዚህ ዓምድ የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔት ንባብ የተነበባቸው የድንበር ነጥቦች፡ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ገፅታዎች፡ የድንበር መለያ ነጥቦች ...ወዘተ ምን እንደሆነ የሚገልጽ መግለጫ ይፃፋል።

ዓምድ 8:- UTM ኢስቲንግ ንባብ

በዚህ ዓምድ ባለሰባት አሀዝ የዩ.ቲ.ኤም(UTM) ኢስቲንግ ንባብ በ2-2-3 አሀዝ/ዲጂት/ በመከፋፈል ይፃፋል።

ዓምድ 9:- UTM ኖርዚንግ ንባብ

በዚህ ዓምድ ባለሰባት አሀዝ የዩ.ቲ.ኤም(UTM) ኖርዚንግ ንባብ በ2-2-3 አሀዝ/ዲጂት/ በመከፋፈል ይፃፋል።

ክፍል 3:- ለውስጥ ገፅታዎችና መለያ ነጥቦች የጂ.ፒ.ኤስ ዝርዝር መረጃዎች

ዓምድ 10:- የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ ተራ ቁጥር:- በዚህ ዓምድ የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ አወሳሰድ ቅደም ተከተል የሚያመለክት ተከታታይ ቁጥር ይፃፋል::

ዓምድ 11:- መግለጫ:- በዚህ ዓምድ የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ የተወሰደላቸው የውስጥ ገፅታዎችና መለያ ነጥቦች ምን እንደሆኑ የሚያመለክት መግለጫ ይፃፋል::

ዓምድ 12:- UTM ኢስቲንግ:- በዚህ ዓምድ ባለሰባት አሀዝ የዩ.ቲ.ኤም(UTM) ኢስቲንግ ንባብ በ2-2-3 አሀዝ/ዲጂት/ በመከፋፈል ይፃፋል::

ዓምድ 13:- UTM ኖርዚንግ:- በዚህ ዓምድ ባለሰባት አሀዝ የዩ.ቲ.ኤም(UTM) ኖርዚንግ ንባብ በ2-2-3 አሀዝ/ዲጂት/ በመከፋፈል ይፃፋል::

በመጨረሻም የካርታ ሠራተኛውና ተቆጣጣሪው ስማቸውን፤ ፊርማቸውንና ሥራው የተጠናቀቀበትን ቀን በተሰጠው ክፍት ቦታ ማስፈር ይኖርባቸዋል::

ማስታወሻ 1 :- ከቅፅ ገ-1 እስከ ገ-6 በሚሞሉበት ጊዜ ከአንድ በላይ ገፆች ጥቅም ላይ የሚውሉ ከሆነ በየገፆቹ የቀኝ ራስጌ ላይ (ገፅ ___ ከ___ ገፆች) በሚለው ቦታ የገፆች ቁጥር መሞላት ይኖርበታል::

ማስታወሻ 2:- የቀበሌውን ከፍታ በሜትር ማንበብና መመዝገብ ስለሚያስፈልግ በገ-6 ክፍል 3 እንዲመዘገብ ይደረጋል:: ይህም:-

ሀ. የቀበሌው አማካይ ቦታ ላይ የጂ.ፒ.ኤስ ከፍታ ነጥብ (Altitude) በሜትር አምድ 11 ላይ ይፃፍና ይኸው የተነበበት ቦታ ኢስቲንግና ኖርዚንግ በአምድ 12 እና 13 ላይ ይፃፋል::

ለ. ቀበሌው የተለያየ ከፍታ ካለው በቀበሌው ሁለት የተለያዩ ቦታዎች / ከፍተኛና ዝቅተኛ/ የከፍታ ነጥብ (Altitude) በሜትር ተነቦ በአምድ 11 ላይ ይፃፋል:: በአምድ 12 እና 13 ላይ ምንም አይሞላም::

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

በገጠር የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች መመዝገቢያ ቅፅ

ቅፅ ገ-6

ክፍል 1፡- የአካባቢ መለያ

1			2			3			4				5		
ክልል	1	2	ዞን	3	4	ወረዳ	5	6	የገጠር ቀበሌ	7	8	9	የቆጠራ ቦታ	10	11

ክፍል 2፡- የድንበር ነጥቦች የጂ.ፒ. ኤስ ንባብ ዝርዝር መረጃዎች

6	7	8	9
የኮኦርዲኔቶች ንባብ ተራ ቁጥር	መግለጫ	UTM ኢስቲንግ	UTM ኖርዚንግ

ክፍል 2፡- የድንበር ነጥቦች የጂ.ፒ. ኤስ ንባብ ዝርዝር መረጃዎች (የቀጠለ)

6	7	8	9
የኮአርዲኔቶች ንባብ ተራ ቁጥር	መግለጫ	UTM ኢስቲንግ	UTM ኖርዚንግ

የካርታ ሠራተኛው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____

የተቆጣጣሪው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____

ክፍል 3:- ለውስጥ ገፆች የጂ.ፒ. ኤስ ንባብ ዝርዝር መረጃዎች

10	11	12	13
የኮኦርዲኔቶች ንባብ ተራ ቁጥር	መግለጫ	UTM ኢስቲንግ	UTM ኖርዚንግ

ማሳሰቢያ፦

በቅፅ 1 - 6 ክፍል የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ መረጃ ከሚሰበሰብላቸው የተለያዩ በገጠር ቀበሌ ውስጥ ከሚገኙ ገፅታዎች መካከል የሚከተሉት በክፍል 3 ዓምድ 11 ሙሉ ስማቸው እየተጠየቀ መሣፍ ይኖርበታል።

ቤተክርስቲያን

1. አርቶዶክስ
2. ካቶሊክ
3. ፕሮቴስታንት
4. መስጊድ

የትምህርት ተቋም

5. አንደኛ ደረጃ ብቻ
6. ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ብቻ
7. መዋዕለ ህፃናት
8. አንደኛ ደረጃና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ
9. ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና የቴክኒክና ሙያ
10. የቴክኒክና ሙያ ት/ቤት
11. ኮሌጅ
12. ዩኒቨርሲቲ

የጤና ተቋም

13. ሆስፒታል
14. ጤና ጣቢያ
15. ክሊኒክ
16. ጤና ኬላ
17. **የገበያ ቦታ**
18. **ጥንታዊ ሕንፃ**

የማዕድን ቁፋሮ ቦታ

19. ወርቅ
20. ብረት
21. ታንታለም
22. እብነበረድ
23. ሌላ /ይገለጽ/
24. ወፍጮ ቤት
25. ቤንዚን ማደያ
26. ቴሌ
27. ፖስታ ቤት

ፋብሪካ

28. ምግብና መጠጥ
29. ትምባሆ
30. ጨርቃጨርቅና የተሰፉ ልብሶች
31. የቆዳና ጫማ
32. የእንጨት ምርትና ቤት ቁሳቁስ
33. የወረቀትና ማተሚያ
34. የኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች
35. የላስቲክና የፕላስቲክ
36. የብረታ ብረት ያልሆኑ የማዕድን ውጤቶች
37. የብረታ ብረት
38. **መንደር**

ምዕራፍ አምስት

የቆጠራ ካርታ ሥራ በከተማ አካባቢዎች

5.1 *በከተማ አካባቢዎች የቆጠራ ቦታ መመስረቻ መመዘኛ ነጥቦች*

የከተማ የቆጠራ ቦታዎች አከላለል መሠረት የሚያደርገው በከተማ ቀበሌዎች ላይ ይሆናል። ቀበሌዎች ባልተመሠረቱባቸው ከተማዎች ግን የቆጠራ ቦታዎች የሚመሠረቱት በቀጥታ ከተማውን በመሸንሸን ይሆናል። በከተማ የቆጠራ ቦታዎች በሚካለሉበት ወቅት የሚከተሉትን ሶስት ዋና ዋና የመመዘኛ ነጥቦች ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል።

ሀ. አንድ የከተማ ቆጠራ ቦታ ከ150-200 ቤቶችን እንዲይዝ ተደረጉ ይመሰረታል። ሆኖም የቆጠራ ቦታው የቆዳ ስፋት ትልቅ ከሆነ የቤቶቹ ብዛት ወደ ዝቅተኛው ገደብ ማለትም ወደ 150 ቤቶች መጠጋት ይኖርበታል። በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝቡ አሰፋፈር ጥቅጥቅ ያለ ከሆነ የቆጠራ ቦታው የቆዳ ስፋት አነስ እንዲል ይደረግና የቤቶች ብዛት ደግሞ ወደ ከፍተኛው ገደብ ማለትም ወደ 200 ቤቶች እንዲጠጋ ይደረጋል።

ለ. የቆጠራ ቦታዎች አከላለል በቀበሌ ወሰን ላይ የተመረኮዘ በመሆኑ አንድ ቆጠራ ቦታ በአንድ ቀበሌ ውስጥ መካተት አለበት። በሌላ አነጋገር አንድ የቆጠራ ቦታ ከአንድ በላይ የሆኑ ቀበሌዎችን ድንበር አቋርጦ መመሥረት የለበትም። ሆኖም አንድ የቆጠራ ቦታ የአንድ ቀበሌ አካል ወይም ቀበሌው እንዳለ አንድ የቆጠራ ቦታ ሊወጣው ይችላል።

ሐ. የቆጠራ ቦታዎቹ በተሰጠው መመዘኛ መሠረት ሲከለሉ የሚከተሉት ነጥቦች እንደ መመሪያ ሊወሰዱ ይገባል።

መ.ቀበሌዎች ባልተቋቋሙባቸው ከተሞች የቆጠራ ቦታዎች ከላይ በተገለፀው መሠረት ይከለላሉ።

i) በተቻለ መጠን ሁኔታዎች እስከፈቀዱ ድረስ ለቆጠራ ቦታዎች ወሰን መለያ የሚሆኑ በጉልህ የሚለዩ ገፅታዎችን ለምሣሌ እንደ መኪና መንገድ፤ ወንዝ፤ ቤተክርስቲያን፤ ትምህርት ቤት፤ ሱቆች፤ የእግር መንገድ፤ ሆቴሎች፤ ...ወዘተ መጠቀም ያስፈልጋል።

ii) በጉልህ የሚለዩ ገፅታዎች በሌሉበት ቦታ የሣጣብ መስመሮች በመፍጠር መጠቀም የግድ ይሆናል። በዚህ አይነቱ አጋጣሚ በሣጣብ መስመሩ ከውስጥና ውጪ ያሉትን ቤቶች መለየት ያስፈልጋል። የሣጣብ መስመሩን በማያሻማ መንገድ በካርታው ላይ መለየት እንዲቻል በዛ ያሉ ቤቶችን በምልክትነት መውሰድ ጠቃሚ ነው። ከዚያም በቀበሌ ወይም በሌላ አካል የተሰጠውን የቤቶች ቁጥርና የባለቤቶቹን ስም ለወሰን መግለጫ መጠቀም ያስፈልጋል። በቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫ ላይ በቆጠራ ቦታው ድንበር ውስጥና ውጭ ያሉትን ቤቶች በግልፅ መመልከት ተገቢ ነው።

iii) አብዛኛዎቹ የከተማ ቤቶች ቀበሌ የሰጣቸው የቤት ቁጥር አላቸው። የቀበሌ የቤት ቁጥሮች አንዳንድ ጊዜ ተከታታይ ባይሆኑም በአንድ የቆጠራ ቦታ መካተት የሚገባቸውን የቤቶች ብዛት ለመገመትና ለመመደብ ይረዳሉ።

iv) የሚመሠረቱት የቆጠራ ቦታዎች በተቻለ መጠን ተሟሉሮ ለመሥራት በሚያመችና በቀላሉ ለማቆራረጥ በሚያስችል መንገድ መሆን ይኖርበታል። በተጨማሪም የቆጠራ ቦታዎች ወሰን በቀላሉ ሊገለጽ በሚችል መልኩ መካለል ይኖርበታል።

5.2 የከተማ ቆጠራ ቦታዎች መመስረቻ ተከታታይ ቅደም ተከተሎች:-

በከተማ የቆጠራ ካርታ ሥራ ወቅት የሚከተሉትን የቆጠራ ቦታ መመሥረቻ ቅደም ተከተሎች በትክክል መከተል ያስፈልጋል።

ስቴፕ 1: በተመደባችሁበት ከተማ/ከተሞች ለቆጠራ ቦታ አከላለል መሠረት የሚሆን የመነሻ (Base) ካርታ ይሰጣችኋል። የተሰጣችሁ ካርታ የምትሠማሩበት ከተማ ካርታ መሆኑንና ሙሉ በሙሉ ከተማውን እንደሚሸፍን ማረጋገጥ ይኖርባችኋል። ይህን የምታደርጉት ወደ ምትሠማሩበት ከተማ ከመሄዳችሁ በፊት ሲሆን አስፈላጊውን የትብብር ደብዳቤም መያዛችሁን አረጋግጡ።

ስቴፕ 2: በወረዳው ዋና ከተማ እንደደረሳችሁም የወረዳውን አስተዳዳሪ ወይም ተወካዩን በማግኘት ተልዕኮአችሁን አስረዱ። በመቀጠልም ወረዳው ውስጥ የሚገኙትን የከተሞች ዝርዝር በቅጽ ከ-1፤ የከተማ የጋርዮሽ መኖሪያዎችን በቅጽ ከ-3 ጠይቃችሁ መዝግቡ። ወደ ምድብ ከተማችሁ ከመሄዳችሁ በፊት የትብብር ደብዳቤ ከወረዳው ጽ/ቤት መያዝ ይኖርባችኋል።

ስቴፕ 3: ስራችሁን በምትጀምሩበት ከተማ በመድረስ የከተማውን ማዘጋጃ ቤት ወይም የከፍተኛውን ወይም የቀበሌውን አመራር በማግኘትና የትብብር ደብዳቤውን በማስረከብ የመጣችሁበትን ዓላማ በሚገባ አስረዱ። ከዚያም በከተማው የሚገኙትን ወረዳዎች/ከፍተኞች፤ ቀበሌዎችና የጋርዮሽ መኖሪያዎች ዝርዝር በመውሰድ ቀደም ብላችሁ በቅፅ ከ-1 እና ከ-3 ላይ ከመዘገባችሁት ጋር በማስተያየት ትክክለኛነቱን አረጋግጡ። በተጨማሪ ከተማው የተለያዩ ቀበሌዎች ካሉት ለቀበሌዎቹ ከሚመለከተው አካል የትብብር ደብዳቤ አፅፉችሁ መያዝ ይኖርባችኋል።

ስቴፕ 4: የወረዳዎች/ከፍተኞች፤ የቀበሌዎችና የጋርዮሽ መኖሪያዎችን ዝርዝር ምዝገባ ካጠናቀቃችሁ በኋላ ከከተማው አመራር ጋር በመሆንና በእግር በመንዝ የከተማውን ድንበር በአራቱም አቅጣጫዎች (ሰሜን፤ ምሥራቅ፤ ደቡብና ምዕራብ) እንዲያሳይዋችሁ አድርጉ። በዚህም ወቅት በእያንዳንዱ የቀበሌ ድንበር መታጠፊያ ላይ የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ በመውሰድ በቅጽ ከ-6 ክፍል 2 ላይ መመዝገብ ያስፈልጋል። ከተማው ትልቅ ከሆነ የእያንዳንዱ ቀበሌ ድንበር አንባራዊ ስፋራውን ይዞ በመነሻ ካርታው ላይ መስፈር ይኖርበታል። ይህ ተግባር የቆጠራ ቦታዎች ምሥረታ ከመጀመሩ በፊት መከናወን ይኖርበታል።

ነገር ግን ከተማው የመነሻ ካርታ ወይም ሌላ ካርታ ከሌለው የከተማውን ንድፍ (Sketch) የጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያ በመጠቀም በምዕራፍ 5 ክፍል 5.5 በተጠቀሱት ቴክኒካዊ መመሪያዎች መሠረት ታዘጋጃላችሁ።

ስቴፕ 5: አሁን ደግሞ የተመደባችሁበት ቀበሌ ምን ያህል የቆጠራ ቦታዎች እንደሚወጣው ሃሣብ እንድታገኙ ቀበሌውን አጥኑት:: ከዚያም ቅጽ ከ-2ን በመጠቀም ቤቶችን፤ ቤተሰቦችንና ከ100 ነዋሪዎች በታች የሚገኙባቸውን የጋርዮሽ መኖሪያዎችን፤ በቅጽ ከ-4 ደግሞ ልዩ የቆጠራ ቦታ የሚወጣቸውን የጋርዮሽ መኖሪያዎች ከቤት ወደ ቤት በመሄድ መዝግቡ:: ቤቶችን በምትመዘግቡበት ወቅት ምዝገባውን በታሳቢ የቆጠራ ቦታ ውስጥ እየገደባችሁ መሆን አለበት:: የምዝገባው ገደብ የከተማ ቆጠራ ቦታ መመስረቻ መመዘኛ ነጥቦችን ግምት ውስጥ በማስገባት መሆን ይኖርበታል::

በምዝገባው ወቅት ቤቶች ሳይዘለሉና ሳይደጋገሙ እንዲመዘገቡ በተመዘገቡ ቤቶች በር ላይ ትሥሥ (Urban Census Cartography) የሚል ቃል በግልፅ እንዲታይ ተደርጐ በጠመኔ መጻፍ ይኖርበታል:: የቤቶችን የቤተሰቦችንና የጋርዮሽ መኖሪያዎችን ምዝገባ በቀበሌ ውስጥ ካጠናቀቃችሁ በኋላ በተሰጠው መመዘኛ መሠረት የቆጠራ ቦታዎችን ታካልላላችሁ:: በዚህም ጊዜ ጐላ ጐላ ላሉ የተፈጥሮና ሰውሰራሽ ገፅታዎች፤ ለቆጠራ ቦታ ወሰንና ለድንበር መለያ ነጥቦች የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ በመውሰድ በቅፅ ከ-6 ክፍል 3 መመዝገብ ይኖርባችኋል:: ከተማው ከአንድ በላይ ቀበሌዎች ካሉት በስቴፕ 5 በተገለፀው መሠረት ለሁሉም ቀበሌዎች የቆጠራ ቦታ ማካለል ሥራ ይከናወናል::

ማስታወሻ:- በጂ.ፒ.ኤስ (GPS) መሣሪያ በእያንዳንዱ የቀበሌ ድንበር መታጠፊያ ቦታ ላይ የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ በመውሰድ በቅጽ ከ-6 ክፍል 2 ላይ መሙላት ይኖርባችኋል:: የቆጠራ ቦታዎችን በምትከልሉበት ወቅት አሁንም የጂ.ፒ.ኤስ(ጅኅል) መሣሪያን በመጠቀም በቆጠራ ቦታ ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉ የሰው ሠራሽና ተፈጥሮአዊ የሆኑ ዋና ዋና ገፅታዎችን በመውሰድ በቦታው ላይ ሆናችሁ ካነበባችሁ በኋላ በቅጽ ከ-6 ክፍል 3 ላይ መመዝገብ ይኖርባችኋል:: እነዚህም ሆስፒታሎች፤ ድልድዮች፤ ቤተክርስቲያናት፤ ትምህርት ቤቶች፤ ክሊኒኮች፤ መስጊዶች፤ ወንዞች ...ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው:: የመንገድ መገናኛዎች፤ አዲስ መንገዶች፤ የቦኖ ውሃ እና ሌሎች ግንባታዎች፤ በመነሻ ካርታው ላይ ከሌሉ የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ ሊወሰድላቸው ይገባል:: የቀበሌና የቆጠራ ቦታዎች ድንበር በመነሻ ካርታው ላይ የሚሰፍሩት መሬት ላይ በሚኖራቸው አንፃራዊ አቀማመጥ እንጂ የጂ.ፒ.ኤስ ንባቦችን መሠረት በማድረግ አይደለም:: ለዚህም ምክንያቱ በማስተር ፕላን ካርታዎች ላይ የዩ.ቲ.ኤም መስመሮችና ቁጥሮች ስለሌሉ ነው::

ስቴፕ 6: ወደ ካምፕ በመመለስ ሁሉንም የቆጠራ ቦታዎች የያዘ፤ ከክፍተኞች/ወረዳዎች እና ከቀበሌዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች ያካተተ የከተማውን ካርታ አዘጋጁ:: በከተማው ውስጥ የካርታ ሥራውን የሚሠሩ የሠራተኞች ቡድኖች ከአንድ በላይ ከሆኑ ሁሉም ቡድኖች አንድ ላይ በመሆን የዘለሉት ወይም ደጋግመው የሠሩት የከተማው አካል አለመኖሩን በማጣራት የከተማውን ካርታ ማጠናቀቅ ይኖርባቸዋል::

ስቴፕ 7: የሚቀጥለው ተግባር ወደ መስክ ተመልሶ በመሄድ በካምፕ የተሠራውን ካርታ የማጣራት ሥራ ይሆናል። እያንዳንዱ የቆጠራ ቦታ ምን ያህል በትክክል መሠራቱንና ጠቃሚ ምልክቶች በካርታው ውስጥ በሚገባ መካተታቸውን ታጣራላችሁ። ከዚያም ቅጽ ከ-5ን በመጠቀም የቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫ ታዘጋጃላችሁ። ስለ መግለጫው አፃፃፍ የቅጽ ገ-5ን ማብራሪያ ተመልከቱ። ከላይ የተጠቀሱትን ለማከናወን ለቆጠራ ቦታዎቹ የመጨረሻ መለያ ቁጥር ከመሰጠቱ በፊት ጊዜያዊ መለያ ቁጥር ይሰጣቸዋል።

ስቴፕ 8: በከተማ ያሉት ወረዳዎች/ክፍተኞች እና ቀበሌዎች በአብዛኛው የራሳቸው ቁጥር አላቸው። በዚህ ጊዜ ቁጥሮቹን እንደመለያ ቁጥር በቀጥታ መውሰድ ያስፈልጋል። ነገር ግን ከክፍተኞቹ /ወረዳዎቹ ወይም ቀበሌዎቹ የራሳቸው ቁጥር ከሌላቸው ቀደም ብሎ በተገለጸው የመለያ ቁጥር አሠጣጥ ደንብ መሠረት መለያ ቁጥር ይሰጣቸዋል። ለቆጠራ ቦታዎች ደግሞ ጊዜያዊ መለያ ቁጥሮችን በመሰረዝ የመጨረሻ የመለያ ቁጥር መስጠት ያስፈልጋል። በአንድ ቀበሌ ውስጥ ለተመሠረቱት የቆጠራ ቦታዎች የመለያ ቁጥር አሠጣጥ በሁለት አሃዝ ይሆንና ከቀበሌው ሰሜናዊ አቅጣጫ ካለው የቆጠራ ቦታ በመጀመር በጥምዝምዞሽ አካሄድ ተከታታይ ቁጥሮች ይሰጣሉ። ለምሳሌ አንድ ቀበሌ ሶስት የቆጠራ ቦታዎች ቢወጣው ለእነዚህ የቆጠራ ቦታዎች 01፣ 02፣ እና 03 ቁጥሮች ይሰጣሉ። ሌላ ቀበሌ አምስት የቆጠራ ቦታዎች ቢወጣው በተመሳሳይ መንገድ የመለያ ቁጥሮቹ 01፣ 02፣ 03፣ 04 እና 05 ይሆናሉ። ለልዩ የቆጠራ ቦታዎች የሚሰጠው መለያ ቁጥር ግን 91፣ 92፣ 93፣... ወዘተ ይሆናል።

በሌላ በኩል ደግሞ አንድ ልዩ የቆጠራ ቦታ አስተዳደራዊ ግንኙነቱ በአካል ከሚገኝበት ቀበሌ ጋር ካልሆነና ግንኙነቱ ከጎረቤት ቀበሌ ጋር ከሆነ እሱን ለመለየት የሚያገለግለው የቀበሌ መለያ ቁጥር በአስተዳደር የሚገናኘው ቀበሌ ቁጥር መሆን አለበት። ቀበሌዎች ባልተቋቋሙባቸው ከተሞች የሚመሠረቱት የቆጠራ ቦታዎች መለያ ቁጥር አሠጣጥ ከከተማው ሰሜናዊ ጫፍ በመጀመር በጠመዝማዛ አካሄድ ባለ ሁለት አሃዝ ተከታታይ ቁጥር በመጠቀም ይሆናል።

ስቴፕ 9: ያዘጋጃችሁት የከተማ ካርታ የወረዳዎችን/የክፍተኞችን፣ የቀበሌዎችንና የቆጠራ ቦታዎችን ድንበር ከጠቃሚ ምልክቶች ጋር (ቤተክርስቲያን፣ መስጊድ፣ ት/ቤት፣ መንገድ፣ ገበያ፣ ...ወዘተ) አካትቶ የያዘ መሆን አለበት። ይህን ካደረጋችሁ በኋላ ካምፓችሁ በመሆን የሠራችሁትን የከተማ ካርታ ሁሉም ምልክቶችና መረጃዎች ሳይጓደሉ ሶስት ኮፒ ታዘጋጃላችሁ። ከዚያም ከአንዱ ኮፒ ላይ የተጠናቀቁ የቆጠራ ቦታዎችን በምላጭ በመቁረጥ ትለያላችሁ። እያንዳንዱን የቆጠራ ቦታ ለየብቻው ፋይል ላይ ትለጥፋላችሁ። ከዚያም ቅጽ ከ-7ን በመጠቀም የየቆጠራ ቦታውን የአካባቢ መለያ (ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ የከተማ ስም፣ ክፍተኛ/ወረዳ፣ ቀበሌ) በማስገባት በቆጠራ ቦታው ፋይል የፊት ሽፋን ላይ ትለጥፋላችሁ። የቆጠራ ቦታውን ካርታ መግለጫ፣ ሰሜናዊ አቅጣጫ፣ ተጎራባች የቆጠራ ቦታዎች ቁጥርና ሌሎች የጎን መረጃዎችን ማስፈር እንደሚገባ ማስታወስ ያስፈልጋል። በቆጠራ ቦታው ፋይል ውስጥም የቆጠራ ቦታውን የድንበር መግለጫ ቅጽ (ቅጽ ከ-5)፣ የቤቶችና ቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ (ቅጽ ከ-2)፣ የጋርዮሽ መኖሪያ መመዝገቢያ ቅጽ (ቅጽ ከ-4) እና በቆጠራ ቦታው የጂ.ፒ.ኤስ ከአርዲኔቶች መመዝገቢያ ቅፅ (ቅጽ ከ-6) ጨምራችሁ አስቀምጡ።

<u>ስቴፕ 10</u>፡ በቀሪዎቹ ሁለት የከተማው ካርታዎች ላይ ደግሞ ቀይ ማርከር በመጠቀም የመቆጣጠሪያ ቦታዎችን ለይዋቸው።

ይህንን ለማከናወንም የሚከተሉትን ነጥቦች መገንዘብ ያስፈልጋል።

ሀ. እያንዳንዱ የመቆጣጠሪያ ቦታ/ልዩ የቆጠራ ቦታዎችን ጨምሮ/በአማካይ አምስት የቆጠራ ቦታዎችን ይይዛል። እንደየሁኔታው አንዳንድ የመቆጣጠሪያ ቦታዎች ከአምስት በላይ ወይም በታች የቆጠራ ቦታዎችን ሊይዙ ይችላሉ።

ለ. አንድ ቀበሌ ከአንድ በላይ የመቆጣጠሪያ ቦታዎች ማካተት አይገባውም። ነገር ግን የተለየ ሁኔታ ሲያጋጥም ለምሣሌ አንድ ቀበሌ ስምንት ወይም ከዚያ በላይ የቆጠራ ቦታዎች ቢወጡት ቀበሌው በሁለት ወይም ከዚያ በላይ የመቆጣጠሪያ ቦታዎች ሊከፋፈል ይችላል። በአጠቃላይ አንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ በአንድ ወረዳ/ከፍተኛ ውስጥ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ቀበሌዎችን ሊያካትት ይችላል። ቀበሌዎች ባልተመሠረቱባቸውም ከተሞች አንድ የመቆጣጠሪያ ቦታ ወደ አምስት የሚደርሱ የቆጠራ ቦታዎችን ሊያቅፍ ይችላል።

ሐ. በሁለቱም የከተማ ካርታዎች ላይ ለመቆጣጠሪያ ቦታዎቹ መለያ ቁጥር ለመስጠት ከከተማው ሰሜናዊ አቅጣጫ በመጀመርና የጥምዝምዞሽ አካሄድን በመከተል ባለ ሁለት አሃዝ ተከታታይ ቁጥር 01፣ 02፣ ...ወዘተ የመለያ ቁጥር ይስጣቸዋል። ይህንን ካከናወናችሁ በኋላ ሥራውን ለተቆጣጣሪው አሳይታችሁ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል። ቀጥሎም ከአንዱ ኮፒ ላይ እያንዳንዱን የመቆጣጠሪያ ቦታ በምላጭ እየቀፈፋችሁ አውጥታችሁ በአዲስ ፋይል ላይ ለጥፉት። ከዚያም የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ በሚለው ርዕስ (በክፍል 4-4-2) ሥር የተጠቀሱትን ዝርዝር መረጃዎች አሟልታችሁ መዝግቡ።

በመጨረሻም እያንዳንዱ የመቆጣጠሪያ ቦታ ፋይል በስሩ ከሚገኙት የቆጠራ ቦታዎች ፋይል ጋር አንድ ላይ መታሰር ይኖርበታል። በተጨማሪም የመቆጣጠሪያ ቦታው ፋይል በውስጡ የተካተቱ ቀበሌዎች የድንበር ነጥቦችን የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባብ የያዙ ቅፆች (ቅፅ ከ-6) አብረው መቀመጥ ይኖርባቸዋል።

5.3 ልዩ የቆጠራ ቦታዎች በከተማ አካባቢዎች

በከተማ ውስጥ 100 እና ከዚያ በላይ ነዋሪዎች ያሉዋቸው የጋርዮሽ መኖሪያዎች ሲያጋጥሙ እንደ ልዩ የቆጠራ ቦታዎች ተቆጥረው በሚገኙበት ቀበሌ ውስጥ 91፣ 92፣ ...ወዘተ እየተባለ የመለያ ቁጥር ይሰጣቸዋል። አንድ መቶና ከዚያ በላይ ነዋሪዎች ያሉት የጋርዮሽ መኖሪያ የቆዳ ስፋቱ ከፍተኛ ከሆነ የጋርዮሽ መኖሪያው ከልዩ የቆጠራ ቦታ ባሻገርም ራሱን የቻለ የቆጠራ ቦታ ተደርጐ የጂ.ፒ.ኤስ የንድፍ ቴክኒክን በመጠቀም ድንበሩን ግልፅ አድርጐ የሚያሳይ ካርታ ይሠራለታል። ልዩ የቆጠራ ቦታ በሆነው የጋርዮሽ መኖሪያ ውስጥ የሚኖሩ መደበኛ ቤተሰቦች ካሉም በቅጽ ከ-4 ላይ ዝርዝራቸው ይመዘገባል። በከተማው ውስጥ የሚገኙ ከ100 ነዋሪዎች በታች የሚኖሩባቸው የጋርዮሽ መኖሪያዎች ውስጥ የሚገኙ ቤተሰቦች ግን በሚገኙበት ቀበሌ በሚሰራ መደበኛ የቆጠራ ቦታ ውስጥ በማካተት በቅጽ ከ-2 ላይ ይመዘገባሉ።

5.4 የከተማ አካባቢ ካርታዎች ዲዛይንና ይዘት

ለአንድ ከተማ ሶስት ዓይነት ካርታዎች ይዘጋጃሉ። እነዚህም የቆጠራ ቦታ፤ የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎችና የማስተር ፕላን ለሌላቸው ደግሞ የጂ.ፒ.ኤስ ንድፍ ካርታዎች ናቸው።

5.4.1 **የቆጠራ ቦታ ካርታ**፡- የቆጠራ ቦታ ካርታ የሚከተሉትን መረጃዎች በተገቢው ሥፍራቸው ማሳየት አለበት። /ስዕል 4.1 ተመልከት/፤

ሀ. የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ክልል፤ ዞንና ወረዳ ስሞች

ለ. የከተማው ስም፤

ሐ. የወረዳው/ከፍተኛውና የቀበሌው ስሞች/ቁጥሮች፤

መ. የቆጠራ ቦታው መለያ ቁጥር፤

ሠ. በቆጠራ ቦታው የሚገኙ ጠቅላላ የቤቶችና የቤተሰቦች ብዛት፤

ረ. በጋርዮሽ መኖሪያ የሚገኙ ነዋሪዎች ብዛት፤

ሰ. የቆጠራ ቦታው ግምታዊ የቆዳ ስፋት፤

ሸ. የቆጠራ ቦታ ወሰን ተለይተው የሚታወቁ ገፅታዎችን /እንደ መንገድ፤ ቤተክርስቲያን፤ ት/ቤት፤ መስጊድ፤ ...ወዘተ ያሉ ምልክቶች/ ተከትሎ የተከለለ፤

ቀ. የአጎራባች የቆጠራ ቦታዎች መለያ ቁጥርና አቀማመጥ፤

በ. የመሬት ላይ ገፅታዎች /ወንዞች፤ የመኪና መንገዶች፤ የእግር መንገዶች፤ ድልድዮች፤ ህንፃዎች፤ ...ወዘተ/፤

ተ. የሰሜናዊ አቅጣጫ አመልካች፤

ቸ. በካርታው የሰፈሩ የተለያዩ ምልክቶችን የሚያስረዳ መግለጫ (ሌጀንድ)፤

ኀ. የካርታው መሥፈርት (Scale)፤

ነ. የመቆጣጠሪያ ቦታ መለያ ቁጥር፤


ኘ. የካርታ ሠራተኛውና የተቆጣጣሪው ስም፤ ፊርማና ሥራው የተጠናቀቀበት ቀን፤

ሥዕል 5.1

የቆጠራ ቦታ ካርታ

ክልል	አሮሚያ
ዞን	ጅማ
ወረዳ	ጅማ
የከተማ ስም	ጅማ
ከፍተኛ	2

ቀበሌ	02
የቀ/ሊ/መ ስም . .	ሬታቸው ኃይሉ
የቤተሰብ ብዛት	152
የቤቶች ብዛት	176
የቆ.ቦታ መ.ቁ. . . .	2-02-01
ግምታዊ ስፋት	0·0256ስ.ኪ.ሜ.
የመቆ/ቦታ መ/ቁጥር	17



መስፈርት 1:2500

መግለጫ

	የከፍተኛ ድንበር
	የቆጠራ ቦታ ድንበር
	የዘወትር መኪና መንገድ
	ቤቶች
	ወፍጮ ቤት
2-02-01	የቆጠራ ቦታ ቁ.

የካርታ ሠራተኛ ስም ሠለሞን መኮ ፈርማ _____ ቀን 12 / 05 / 85

የተቆጣጣሪ ስም ናኅል ቢሜቃ ፈርማ _____ ቀን 16 / 05 / 85

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
የከተማ ቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫ ቅፅ

ቅፅ ከ-5

ክፍል 1፦ የአካባቢ መለያ

1		2			3			4	5			6				7		
ክልል	1	2	ዞን	3	4	ወረዳ	5	6	ከተማ	7	ክፍተኛ	8	9	ቀበሌ	10	11	12	የቆጠራ ቦታ	13	14
አሮሚያ			ጅማ			ጅማ			ጅማ		2			02				01		

ክፍል 2፦ የቆጠራ ቦታ መግለጫ

8. መግቢያ

የዚህ የቆጠራ ቦታ የሰሜን መነሻ ነጥብ ካቆበኬ ዐረ ሞ/ቤት በስተ ምዕራብ በግምት 250 ሜትር ይሆናል ተመዝግቧል።

9. የድንበር መግለጫ ፅሁፍ

ሰሰሜን ቁህ የቆጠራ ቦታ ካካፍተኛ ካንቺ ኡለቁዋት: ወሰኒና መንገሬ በመነሣት የፓሊኡን ኃይሌን: ቆሮና ማር መሸጫ ሱቅ ወዲ ሙለፕ በጣዛይ ሬማ ሃካካፎተኛ ካንቺ: መሶ ከሙስ- ኳየተቁለነ ካሂፈጠኃት ሰንጉሬል ቡናቤን ወዲ ሙስኛ ካሮርገ በጣስፍ የበረሂ ወፀሮችን ቤት ወደ ሙለፕ ኡሮርገ ፎማ ፓሊስ ጣቢያ ለደርለ የሰሜን: ክብል ፃበቃል

በምሥራቅ የነበኝት ክብል ካቆ መደት ካካፍተኛ ካንቺ ሮጌበር በምዕራብ ቆሙ ይሚ ፓሊስ ጣቢያ: ወዲ ውጭ ኳሮርገ ለመነሣት ሙኛተስመጋዝ የቤት ሎፕር ናጋ የሆነውን የሱኬ ፀህን በሸርገ ቤት ወዲ ሙኳ ኳሮርገ ወዲፍት በመጋዝ የበር ተከማኝ ሱቆ ወዲ ሙኳ የኳሂ/ሰዲ መጋዘኛ ወዲ ሙለኛ በጣሬሪግ: ጉንሽ ኳንቺ ተጋዘ የቤት ሎፕር ዐፅጌ የሆነ ውን የቆበኬ ዐረ ሞ/ቤት ኳቆጣጣ ሰዲርለ: የቆበርፅ

ምዕራብ ካቆበኬ ዐረ ሞ/ቤት በመነሣት ሞ/ቤቱን: ወዲ ሙኳ ኳሂኮ በመሐፍ በሪሽሙ ኳንቺ ተጋዲሙ የቤት ሎፕር ሂዘ የሆነውን ካሂ:ሪት ሎፓ ቤትን. ወዲ ሙኳ የቤት ሎፕ 231 የሆነውን የሰጠኛ ሞ ውን ካሂርገ ፎቁለል

በምዕራብ የዲ ጉብ ካበል ካበቆበት ኡጣገሪት ሎፓ ቤትን ወዲ ሙለፕ ኳጠፍሙ ቡናቤትን: ወዲ ሙኳ በጣሬሪግ ፃነሡና ወፈሮች በመገዝ የኳለመዝ ገጠሰኡሲን ቤት ወዲ ሙለፕ የቤት ሎፕር ገጋገ የሆነውን የኳዛጠሙየሱ ፍን ፎዲ ቤት ወዲ ሙኳ ኳሂርገ የመኳና ወንገሬ ሥዲ ጉንሽ ኳንቺ ተጋዘ ቦቪዲን ኳኡጣሜ ካቲመሪበት ካ ኒተኛ ኳንቺ ዩንበር ዞሪሮ በ ሀሪጠቁ ዋዚህ ፃጠቆ ቦታ ክብል ፃበቃል

ማሳሰቢያ: የድንበር ማገናዘቢያ መለያ ነጥቦች (Reference Points) የሚሆኑት ቋሚና በግልፅ ተለይተው የሚታዩ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ገፅታዎች ሲሆኑ የሌላ ቆጠራ ቦታ ድንበር እንደድንበር ማገናዘቢያ መለያ ነጥቦች (Reference Points) መወሰድ የለባቸውም::

የካርታ ሠራተኛው ስም ሠለቻን ወሻሞ ፊርማ ~~ሠለቻን~~ ቀን 14/05/85

የተቆጣጣሪው ስም ናኡለ ቢሜቆ ፊርማ ~~ለሌቆ~~ ቀን 20/05/85

5.4.2 <u>የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ</u>፡- የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ የሚከተሉትን መረጃዎች በተገቢው ሥፍራቸው ማሳየት አለበት:: /ስዕል 4.2 ተመልከት/፤

ሀ. የመቆጣጠሪያ ቦታው የሚገኝበት ክልል፤ ዞንና ወረዳ ስሞች፤

ለ. የከተማው ስም፤

ሐ. በመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታው ውስጥ ያሉ ቀበሌዎች ሥምና መለያ ቁጥር፤

መ. በመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታው ውስጥ ያሉ ቀበሌዎች ብዛት፤

ሠ. በመቆጣጠሪያ ቦታው ውስጥ የሚገኙ ጠቅላላ የቆጠራ ቦታዎች ብዛት፤

ረ. በመቆጣጠሪያ ቦታው ውስጥ የተካተቱ የቆጠራ ቦታዎች የመለያ ቁጥር፤

ሰ. የመቆጣጠሪያ ቦታው የመለያ ቁጥር፤

ሸ. ዋና ዋና የመሬት ገፅታዎችና ተጐራባች የመቆጣጠሪያ ቦታዎች ወሰን መገናኛ ነጥቦች፤

ቀ. የወረዳዎች/ከፍተኞች፤ ቀበሌዎች፤ የመቆጣጠሪያ ቦታዎችና የቆጠራ ቦታዎች ድንበር፤

በ. የሰሜናዊ አቅጣጫ አመልካች፤

ተ. በካርታ ውስጥ የሰፈሩ የተለያዩ ምልክቶችን የሚያስረዳ መግለጫ፤

ቸ. የካርታው መስፈርት፤


ኀ. የመቆጣጠሪያ ቦታው ካርታ ተሰርቶ የተጠናቀቀበት ቀን፤ የካርታ ሠራተኛውና የተቆጣጣሪው ስምና ፊርማ

የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ

ሥዕል 5.2

ክልል	ኦሮሚያ
ዞን	ጅማ
ወረዳ	ጅማ
የከተማ ስም . . .	ጅማ

የመቆጣጠሪያ ቦታ ቁ. . . .	17
የቀበሌ ብዛት	1
የቆጠራ ቦታ ብዛት . . .	6



መግለጫ

	የ ከፍተኛ ድንበር
	የመቆጣጠሪያ ቦታ ድንበር
	የቀበሌ ድንበር
	የቆጠራ ቦታድንበር
	የዘወትር መኪና መንገድ
,	መስረድ , ቤቶች
X,	የገበያ ቦታ , ወፍጮ ቦት
2-02-02	የቆጠራ ቦታ መ.ቁጥር
17	የ መቆጣጠሪያ ቦታ መ·ቁ

መስፈርት 1:4000

የካርታሠራተኛ ስም ሠለሞን ማሞ ፊርማ _____ ቀን 12/ 10/ 85

የተቆጣጣሪ ስም ናስልቢጫቃ ፊርማ _____ ቀን 14 / 10/ 85

5.4.3 <u>የጂ.ፒ.ኤስ ንድፍ ካርታ/ማስተር ፕላን ለሌላቸው ከተሞች/</u>

በጂ.ፒ.ኤስ ንድፍ ሥራ የተዘጋጀ የከተማ ካርታ የሚከተሉትን መረጃዎች በተገቢው ሥፍራቸው ማሳየት አለበት:: /ስዕል 4.3 ተመልከት/

ሀ. ከተማው የሚገኝበት ክልል፤ ዞንና ወረዳ ስሞች፤

ለ. የከተማው ስም፤

ሐ. ጠቅላላ የወረዳዎች/የክፍተኞች፤ የቀበሌዎች፤ የመቆጣጠሪያና የቆጠራ በታዎች ብዛትና አቀማመጥ፤

መ. የከተማውን ድንበር በትክክል የሚገልጹ ልዩ ልዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ገፅታዎች /እንደ መንገድ፤ ወንዝ፤ ...ወዘተ/፤

ሠ. በከተማው ውስጥ የሚገኙ ጎላ ጎላ ብለው የሚታዩ የመሬት ላይ ገፅታዎች፡- /<u>ምሳሌ</u>፡- ህንፃዎች፤ የመኪና መንገዶች፤ የእግር መንገዶች፤ ት/ቤቶች፤ የጤና ማዕከላት፤ ቤተክርስቲያኖች፤ መስጊዶች፤ የገበያ ሥፍራዎች፤ ታሪካዊ ስፍራዎች ...ወዘተ፤/

ረ. በጂ.ፒ.ኤስ ንባብ የተወሰደላቸው ገፅታዎችን አቀማመጥ የተከተለ የንባብ ተራ ቁጥር፤

ሰ. የወረዳዎች/የክፍተኞች፤ የቀበሌዎች፤ የመቆጣጠሪያና የቆጠራ በታዎች አቀማመጥ፤

ሸ. ምልክቶችን የሚያስረዳ መግለጫ፤


ቀ. የካርታው መሥፈርት፤

በ. የሰሜናዊ አቅጣጫ አመልካች፤

ተ. የካርታ ሠራተኛውና የተቆጣጣሪው ስም፤ ፊርማና ሥራው የተጠናቀቀበት ቀን፤

<u>ማስታወሻ</u>፡- 1. ማስተር ፕላን ላላቸው ከተሞች ከላይ የተዘረዘሩት መረጃዎች በተሟላ መንገድ መኖር አለመኖራቸውን አስተያይተህ የጎደሉትን አሟልተህ አስፍር::

2. የጂ.ፒ.ኤስ ንድፍ ካርታ ለመሥራት በምዕራፍ 5 የተገለፅውን ቴክኒካዊ መመሪያ ተመልከት::


ሥዕል 5.3
የተጀ ከተማ ካርታ (የጀ.ፐ.ኤስ ንድፍ)
ክልል አሮሚያ
ዞን ደቡብ ምዕራብ ሸዋ
ወረዳ ኢሉ
የከተማ ሥም_ተጀ
የቀበሌ ብዛት__ 1
የቆጠራ ቦታ ብዛት
የመቆ/ቦታ ብዛት
0430000ME
0431000ME
0977000MN
0976000MN
0975000MN
መግለጫ
የከተማ ድንበር
የዘወትር መኪና መንገድ
የበጋ መኪና መንገድ
የእግር መንገድ
የዘወተር ወንዝ
ት/ቤት : ቤተክርስቲያን
ክሊኒክ : ጣበያ ቦታ
ሆቴል : እስተዳደር ጽ/ቤት
ፖስታ ቤት : መፍጭ ቤት
ቤቶች
የድንበር ክለርዳኔት
መለፈርት 1:10,000
በተጀ ከተማ የካርታ ሥራተሮች የተዘጋጀ
የተቆጣጣሪ ሥም
ፊርማ
ቀን

5.5 የጂ.ፒ.ኤስ ንድፍ (GPS SKETCH) አሠራር

በሀገራችን በርከት ያሉ ትንንሽ ከተሞች ማስተር ፕላን ወይም ሌላ ከፍተኛ መስፈርት መነሻ ካርታ አልተሰራላቸውም። በዚህ ሁኔታ ጂኦግራፊያዊ አሰሩፈርን የሚያሳይ የመነሻ ካርታ ከሌለ አዲስ የከተማ ንድፍ መሥራት የግድ ይሆናል። የከተማ ንድፎችን በጂ.ፒ.ኤስ መሳሪያ በመታገዝና የካርታ አሠራር ቴክኒኮችን በመጠቀም መሥራት ይቻላል። የጂ.ፒ.ኤስ ንድፎች ለከተሞች ብቻ ሳይሆን በገጠር ቀበሌ ማህበራት ለሚገኙና ከአንድ የቆጠራ በላይ ሊወጣቸው በሚችሉ ትልልቅ መንደሮችና አነስተኛ የመገበያያ ሥፍራዎችም ጭምር መሥራት ይቻላል። የመንደሮቹን የመሥራት ዋናው አላማ የቆጠራ ቦታዎችን ድንበር ግልፅ በሆነ መንገድ ለመለየት እንዲቻል ነው።

የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የጂ.ፒ.ኤስ ንድፎችን ማዘጋጀት አስፈላጊ ይሆናል፦

1. ከተማው ማስተር ፕላን የሌለው ሲሆንና አዲስ ንድፍ መሥራት ሲያስፈልግ፡
2. ከተማው ማስተር ፕላን (1:2000 ወይም 1:5000) ያለው ሆኖ ማስተር ፕላኑ ጠቅላላውን የአሁኑን የከተማውን ክልል ሙሉ በሙሉ የማይሸፍን ሲሆንና ላልሸፈነው ዳርቻ (fringe) አዲስ ንድፍ መሥራት ሲያስፈልግ፤

የጂ.ፒ.ኤስ ንድፍ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

ሀ. በA2 ወይም A3 መጠን ወረቀት / ማለትም በ1:5000 ወይም 1:10000 መስፈርት/ ላይ የተሳሉ 1ኪ.ሜ የUTM ግሪድ መስመሮችና፤

ለ. የከተማውን ዋና ዋና ገፅታዎች ማለትም የከተማውን ድንበር፤ መንገዶችን ዋና ዋና ሕንፃዎች፤ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋማትና የቆጠራ ቦታ ድንበሮችን ያካተተ መሆን ይኖርበታል።

1. ንድፉን ምንም አይነት መነሻ ካርታ ሳይኖር መሥራት ሲያስፈልግ፤

ሀ. ይህን ተግባር ለማከናወን ሲያስፈልግ በመጀመሪያ የካርታ ሠራተኛው የሚከተሉትን ቁሳቁሶች መረከቡን ማረጋገጥ አለበት።

1. የጂ.ፒ.ኤስ መቀበያ መሳሪያ (ከነባትሪ ድንጋዮች)
2. የጂ.ፒ.ኤስ ኮአርዲኔት መመዝገቢያ ቅፅ (ቅፅ ከ-6)
3. በ1ሣ. ሜ ስኬር ግሪድ መስመሮች የተከፋፈለ A3 መጠን ወረቀት

ለ. በመቀጠል የከተማውን ድንበር የሚያውቅ የቀበሌ ተወካይ ጋር እየተዘዋወሩ በማየትና በድንበር ነጥቦች ላይ የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔት በመውሰድ በኮኦርዲኔት መመዝገቢያ ቅፅ (ቅፅ ከ-6) ላይ መመዝገብ፤

የድንበር ነጥቦች የሚሆኑት ድንበሩ የሚያቋርጥባቸው ነጥቦች ለምሳሌ፦ ቤቶች፤ መንገዶች፤ የኃይል መስመሮች፤ አጥሮች፤ ወንዞች፤ የእግር መንገዶች... ወዘተ ሲሆኑ በሜዳማ ሥፍራዎች ላይ ለሚያልፍ ድንበር ደግሞ የድንበር መታፊያ ነጥቦች ናቸው። አንዳንድ ጊዜ የከተማው ድንበር ተፈጥሮአዊ ገፅታዎችን / ወንዞችን፤ ሰንሰለታማ ተራራዎችን ... ወዘተ / ወጣ ገባ ሳይል ሊከተል ይችላል። በዚህ ጊዜ የድንበር ነጥብ የሚሆኑት የወንዙን መታጠፊያ ነጥቦች ናቸው።

ሐ. በመቀጠልም በተዘጋጀው የUTM ግሪድ ወረቀት ላይ የኮኦርዲኔት የድንበር ነጥቦችን በመስፈርቱ መሰረት ቀይሮ በማስፈርና በማገናኘት የድንበር መስመር ማዘጋጀት፤

መ. በከተማው ውስጥ በሚገኙ በእያንዳንዱ የማህበራዊ አገልግሎት መስጫ ተቋም፤ ድርጅት ሕንፃ አጠገብ እና በመንገድ መታጠፊያዎች ላይ የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ በመውሰድ በኮኦርዲኔቶች መመዝገቢያ ቅፅ (ከ-6) ላይ መመዝገብ፤

ተቋማትና የማህበራዊ አገልግሎት መስጫዎች የሚባሉት የአስተዳደር ቢሮዎች፤ ክሊኒክ፤ ት/ቤት፤ በመንግስት/ ህብረተሰብ የተሰሩ የውኃ ጉድጓዶች / ማደያዎች፤ ቤተክርስቲያን፤ መስጊድ፤ የመቃብር ሥፍራ፤ ፖስታ ቤት ፤ ባንክ፤ ዋና ዋና ሱቆች፤ የገበያ ቦታ፤ መንገድ፤ ወዘተ... የመሳሰሉት ናቸው።

ሠ. በቆጠራ ቦታ ወይም በከተማ ድንበር አካባቢ የሚገኙ ህንፃዎች ወይም ቤቶች፦ የቆጠራ ቦታ ድንበር በሚከለልበት ወቅት ተለይተው የሚታወቁ ህንፃዎች/ ቤቶች ከድንበሩ ውስጥና ውጪ ሊገኙ ይችላሉ። የእነዚህ ህንፃዎች ወይም ቤቶች/ በተለይ በድንበር ማእዘናት ላይ የሚገኙትን/ ኮኦርዲኔት ንባብ በጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያ በመውሰድ እና የእያንዳንዱን ሕንፃ/ ቤት ባለቤት ስም እንዲሁም ሌሎች ገላጭ መረጃዎችን በመነሻ ካርታው ላይ ማስፈር የቆጠራ ቦታ የድንበር መግለጫዎችን በግልፅ ለመግፍ ይጠቅማል።

ይህ አሰራር ዘዴ ጥቅም ላይ የሚውለው ምንም አይነት የከተማ ፕላን ካርታ በማይገኝባቸው አባቢዎች በተሰመረ የግሪድ ወረቀት ላይ የከተማ ንድፎችን መሥራት ሲያስፈልግ ነው።

በመጀመሪያ የካርታ ሥራ ቡድኑ እንደከተማው ስፋትና ጥበት 1:10000 ወይም 1:5000 መስፈርት በመምረጥ ባለ 1 ሳ.ሜ ስኬር የተሰመረ ወረቀት ላይ የUTM ግሪድ መሥመሮችን በመለየት ቁጥሮቻቸውን መፃፍ ይኖርበታል።

ይህን ለማድረግ መስፈርቱ 1:10,000 ከሆነ በግሪዶች መስመሮች መካከል ያለው ርቀት 10 ሳ.ሜ ሲሆን 1:5000 ከሆነ ደግሞ በግሪዶቹ መካከል ያለው ርቀት የ20 ሳ.ሜ ነው። ስለዚህ ለመጀመሪያው በ10 ስኬሮች ልዩነት የግሪድ ቁጥር መፃፍ፤ ለሁተኛው ደግሞ በ20 ስኬየር ልዩነት የግሪድ ቁጥር መፃፍ ያስፈልጋል። በዚህ መሰረት የከተማው ውሰን እስኪካተት ድረስ የግሪድ ቁጥሮችን በመስፈርቱ መሰረት መፃፍ ያስፈልጋል። በተጨማሪ ሁሉንም የካርታ ዝርዝር መረጃዎችን ማካተት ይኖርበታል። በተለያዩ ከፍተኛ መስፈርቶች በግሪድ መስመሮች መካከል ያለውን ርቀት በሳ.ሜ ለማመልከት በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቧል።

ሠንጠረዥ 5.1 ከፍተኛ መስፈቶችና በግሪድ መስመሮች መካከል ያለው ርቀት በሣ.ሜትር (ባለ 1ሣ.ሜ ስኬሮች ብዛት)

መስፈርት	በግሪዶች መካከል ያለ ርቀት በሣ.ሜ	ወደ ጎን/ላይ የሚቆጠሩ ባለ 1ሣ.ሜ ስኬሮች ብዛት
1:10,000	10	10
1:5000	20	20
1:2500	40	40
1:2000	50	50

ይህ ተግባር እንደሚከተለው ሊከናወን ይችላል:-

i. በከተማው የድንበር ነጥቦች ላይ የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔት ንባቦችን መውሰድና በኮኦርዲኔት መመዝገቢያ ቅፅ (ቅፅ ከ-6) ላይ መመዝገብ፤

ii. ባለ 1ኪ.ሜ የግሪድ መሥመሮችን በመስፈርቱ መሠረት መቀየር በA2 (42.0 ሳ.ሜX59.4 ሳ.ሜ) ወይም A3 (29.7ሳሜ X 42.0 ሳሜ) መጠን ባለ 1 ሳ.ሜ ስኬየር የተሰመረ ወረቀት ላይ በመለየት የኮኦርዲኔት ነጥቦችን በሙሉ በሚያካትት መልኩ ማዘጋጀት፤

iii. ለድንበር ነጥቦች የተነበቡ ኮኦርዲኔቶችን በተዘጋጀው የUTM ግሪድ ወረቀት ላይ ማስፈር፤ ትክክለኛነታቸውን ማረጋገጥና የድንበር ነጥቦችን በቅደም ተከተል በማገናኘት ድንበሩን ማግኘት፤

iv. በከተማው ውስጥ የሚገኙ የገፅታዎችንና የቆጠራ ቦታ ድንበር መለያ የኮኦርዲኔት ንባቦችን ማስፈርና የቆጠራ ቦታ ድንበሮችን መከለል፤

v. በትሬሲንግ ወረቀት ላይ ኮፒ ማድረግ

ለምሳሌ ያህል የተጂ ከተማ የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔት ንባቦች በእዝል III በቅፅ ከ-6 ቀርበዋል:-

ሀ. <u>የተጂ ከተማን ንድፍ ለመሥራት በ1:10000 መስፈርት ላይ የUTM ግሪድ መስመሮችን ለመለየት ቅደመ ዝግጅት ሥራ።</u>

i. የተመዘገቡትን የኮአርዲኔት ንባቦች የሚያካትት የA2 (42.0 ሳሜ x 59.4ሳሜ) ወይም የA3 (29.7ሳሜ x 42.0ሳሜ) መጠን በ1 ሳ.ሜ ስኬር የተስመረ ወረቀት ላይ የUTM ግሪድ መስመሮችን መለየት። በእያንዳንዱ የግሪድ መስመር መካከል 10 ሣ.ሜ ወይም 10 ባለ 1ሳሜ ስኬሮች ርቀት ይኖራል።

ii. ባለ 1ኪ.ሜ መስመሮችን መለየት። እነዚህም ለEasting 29,30,31 እና ። ለNorthing ደግሞ 75,76 እና 77 ናቸው።

iii. ለEasting መስመሮች አንድ ባለ 1ኪ.ሜ ስኩየር መስመር በመጨመር የመጨረሻውን ስኬየር መስመር ማሟላት ሲሆን ይህም በ29 30 እና 31 መስመሮች ላይ 32ን መጨመር ይሆናል። ይህም የሚሆነው ክ31 በኃላ ያሉትን ባለሶስት አሀዝ ንባቦች ማካተት እንዲቻል ነው።

iv. ለNorthing መስመሮች ደግሞ ባለ 1ኪ.ሜ ስኬር መስመር በመጨመር የመጨረሻውን ስኬር ማሟላት ሲሆን ይህም በ75 ,76 እና 77 መስመሮች ላይ 78ን መጨመር ይሆናል። ይህ የሚሆነው ከ77 በኃላ ያሉትን ባለሶስት አሀዝ ንባቦች ማካተት እንዲቻል ነው።

ለ. <u>የተጂ ከተማ ንድፍ በ1:10000 መስፈርት ለማዘጋጀት የUTM ግሪዶችን የመለየት፤ ቁጥር የመስጠትና ኮአርዲኔቶችን የማስፈር ሥራ።</u>

i. የEasting (ከታች ወደ ላይ የሚሰመሩ) መስመሮች የሚሆኑት የ29,30 ,31 እና 32 ከምእራብ ወደ ምስራቅ የሚዛፉ ቁጥሮች ሲሆኑ በመካከላቸውም የ10 ሣ.ሜ ወይም 10 ባለ 1ሳ.ሜ ስኬሮች ርቀት ይኖራል ።

ii. የNorthing (ከግራ ወደ ቀኝ የሚሰመሩ) መስመሮች የሚሆኑት የ 75 ,76, 77 እና 78 ከደቡብ ወደ ሰሜን የሚዛፉ ቁጥሮች በመካከላቸውም የ10 ሣ.ሜ ወይም 10 ባለ 1 ሳ.ሜ ስኬር ርቀት ይኖራል።

iii. እነዚህ የUTM ግሪድ መስመሮች በትክክል ሲሰመሩ 9 ባለ 1ኪ.ሜ ስኬሮችን ይሰጣሉ::

iv. የUTM መስመሮች ቁጥር በመስመሩ ትይዩ ጠርዝ ላይ መፃፍ ይኖርበታል:: ለምሳሌ:- ለኢስቲንግ 0429000ME ለኖርዚኒግ ደግሞ 0975000MN በሚል ጠርዝ ላይ ይፃፋሉ:: በተጨማሪም 1ኪ.ሜ ስኬር ውስጥ ያሉ ባለ 100 ሜትር ስኬር ቁጥሮች በ1ሳ.ሜ ልዩነት (ከ1 እስከ 9) በመስመሮች ጠርዝ ላይ መፃፍ::

v. በእነዚህ ስኬር ውስጥ የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔት የድንበር ነጥብ ንባቦችን (ከቅፅ ከ-6 ክፍል 2) በመውሰድ ማስፈርና የድንበር ነጥቦች የኮኦርዲኔት ንባቦችን ከቅፅ ከ-6 ክፍል 3 በመውሰድ በማስፈርና የድንበር ነጥቦች የኮኦርዲኔት ንቦቦችን በማገናኘት የተጂ ከተማን ድንበር ማግኘት፤

vi. በመቀጠልም የሌሎች ገፅታዎችን (መንገዶች፤ ት/ቤት፤ ቤተክርስቲያን፤ የመቃብር ሥፍራዎች፤ ሱቆች፤ ሆቴሎች) ኮኦርዲኔቶች ንባቦችን ከቅፅ ከ-6 ክፍል3 በመውሰድ በተዘጋጀው የግሪድ ስኬር ንድፍ ላይ ማስፈር፤

vii. የተሰጠውን ንድፍ በትሬሲንግ ወረቀት ላይ ኮፒ ማድረግ፤

የተጂ ከተማ ንድፍ የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔት ንባብና ከላይ የተዘረዘሩትን ቴክኒካዊ ቅደም ተከተሎች መሠረት በማድረግ ተሰርቶ በእዝል ቀረቧል:: አሁን የቆጠራ ቦታዎችን ለመመሥረት የሚያስችል የተጂ ከተማ መነሻ ካርታ ተዘጋጅቷል ማለት ነው:: በዚህ ካርታ ላይ ተመርኩዞ፤ የጂ.ፒ ኤስ መሣሪያውን በመጠቀም፤ የቆጠራ ቦታዎችን ድንበር መለያ ነጥቦች ላይ ንባብ በመውሰድ የቆጠራ ቦታ ካርታዎችን ማዘጋጀት ይቻላል::

2. <u>በማስተር ፕላን ላልተሸፈኑ የከተማ ዳርቻዎች የጂ.ፒ.ኤስ ንድፍ መስራት</u>

ከፍተኛ መስፈርት ያላቸው የከተማ ማስተር ፕላኖች ብዙውን ጊዜ የሚሸፍኑት የአየር ፎቶግራፍ በተነሣበት ጊዜ የነበረውን ግንባታ የተካሄደበት የከተማ አካባቢ ብቻ ነው:: በሕዝብ ቁጥር መጨመር ሳቢያ አብዛኛዎቹ ከተሞች ቀደም ብሎ ከተሠራላቸው የማስተር ፕላን ካርታ ሽፋን ውጪ እየተስፋፉ ይገኛሉ:: ይህ ሁኔታ ሲያጋጥም በማስተር ፕላኑ ላልተሸፈኑ ዳርቻዎች ቀደም ብሎ በተገለፀው የጂ.ፒ.ኤስ ንድፍ አሠራር ዘዴ መሠረት ንድፍ መሥራት ያስፈልጋል:: የሚሰራው ንድፍ በማስተር ፕላኑ መስፈርት መሰረት ይሆናል::

- እነዚህ የከተማ ዳርቻዎች በተለይ በትላልቅ ከተሞች ውስጥ ከፍተኛ የሕዝብ አሰፋፈር፣ ያልታቀዱ የቤት አሰራሮች የሚታዩባቸውና በግልፅ የተቀየሱ የመንገድ አውታሮች የሌላቸው በመሆኑ የቆጠራ ቦታዎችን ድንበር ለመከለል እና ካርታ ለማዘጋጀት አዳጋች ነው::

- ሌላው ከከተሞች መስፋፋት ጋር ተያይዞ የሚከተለው ችግር በአዲስ መልክ የተገነቡት ቤቶች ከከተማው ድንበር ውጭ ሰፈረው ስለሚገኙ ከህጋዊ የከተማው አስተዳደር ድንበር ውስጥ የሚጠቃለሉትን ግንባታዎች ከከተማው ውጭ በገጠር ቀበሌ ማህበር ክልል ካሉት በጥንቃቄ መለየት አስፈላጊ ይሆናል:: የከተማና የገጠር የቆጠራ ቦታዎች መለየት ስለሚኖርባቸውና ሁለቱ የማይደባለቁና እንዲሁም የከተማውን ድንበር የማያቋርጡ መሆኑን መገንዘብ ተገቢ ነው::

- በተጨማሪ በከተማ ካርታ ውስጥ ያልተካተቱ ዳርቻዎች የንድፍ ሥራ ሲሰራ የጂ.ፒ.ኤስ መሳሪያው የተወሰነ ስህተት ሊኖረው እንደሚችል ማስታወስ ያስፈልጋል :: የጂ.ፒ.ኤስ ተነበው የሚጨመሩትን ገፅታዎች መነሻ ካርታው ላይ ካለው አቀማመጣቸው ጋር ስናመሳክር አለመጣጣም ሊፈጠር ይችላል:: <u>ለምሳሌ</u>:- በመነሻ ካርታው ጫፍ ላይ የሚገኝ መንገድ በጂ.ፒ.ኤስ ተነቦ ከሚገኘው ተመሳሳይ መንገድ ጋር ከላይ በተጠቀሰው የG.P.S. ERROR ምክንያት ላይጣጣም ይችላል ይህን በማገናዘብ ንደፉንና ማስተር ፕላኑን ማገጣጠም ያስፈልጋል:: በሁለቱም ሁኔታዎች በንድፉ የተጨመሩት ገፅታዎች በማስተር ፕላኑ ከነበሩት ገፅታዎች ጋር በትክክል መጣጣማቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

- በሌላ በኩል ማስተር ፕላኑ ከተሰራ በኃላ የተገነቡ ሰው ሰራሽ ገፅታዎች <u>ለምሳሌ</u>:- መንገድ ፊት ተሰርቶ ከነበረው አቀማመጡ ተቀይሮ ከሆነ ያለመጣጠሙ በጂ.ፒ.ኤስ መሳሪያ ስህተት አለመሆኑን በመገንዘብ ለውጡን በንድፉ ማካተት ያስፈልጋል::

- በሁለቱም ሁኔታዎች በንድፉ የተጨመሩት ገፅታዎች በማስተር ፕላኑ ከነበሩት ገፅታዎች ጋር በትክክል መጣጣማቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

- ለአንድ ከተማ ዳርቻዎች የሚሰሩ የጂ.ፒ.ኤስ ንድፎች ከከተማው ማስተር ፕላን ጋር የሚገጣጠሙት ቋሚና ታዋቂ ገፅታዎችን በማነፃፀር ነው::

ጠቃሚ ነጥቦች:-

1. በጂ.ፒ.ኤስ ንባብ በሚወሰዱበት ወቅት በመሳሪያው ስክሪን ላይ ከUTM ኮኦርዲኔት ቁጥሮች ጋር የዞን ቁጥር የሆነ (ምሳሌ 37p) የሚል ንባብ ይገኛል ይህን ቁጥር መመዝገብ አስፈላጊ አይደለም::

2. የUTM ኮኦርዲኔት ቁጥሮች ከጂ.ፒ.ኤስ መሳሪያው ስክሪን ላይ ተነበው ግልፅ በሆነ መንገድ መመዝገብ ይኖርባቸዋል::በምዝገባ ወቅትም ሰባቱም አሀዞች (ዜሮን ጨምሮ) መፃፍ አለባቸው:: በንባብ አወሳሰድና አመዘጋገብ ወቅት የሚከሰት ስህተት ገፅታዎችን (features) በካርታ ላይ በተሳሳተ ሥፍራ ላይ እንዲሰፍሩ ሊያደርግ ይችላል::

3. በቆጠራ ቦታ ውስጥ የሚገኝን የአንድ ትልቅ መንደር የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔት ንባብ በመንደሩ መሀከለኛ ሥፍራ ላይ በመሆን መውሰድ ተገቢ ነው:: መንደሩ ሁለትና ከዚያ በላይ የቆጠራ ቦታዎች የሚወጣው ከሆነ ግን የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ የሚወሰደው በእያንዳንዱ ቆጠራ ቦታ ውስጥ ይሆናል::

4. በመስክ ሥራ ወቅት ማንኛውም ለካርቶግራፊ ሠራ የሚጠቅም መረጃ በቅፆች በስተጀርባ በአስተያየት መልክ ቢፃፍ ጠቃሚ ነው:: ለምሳሌ:- ቤተሰቦች የሌላቸው መንደሮች ቢያጋጥሙ ቤተሰቦች የሌሉበትን መንደር "ቤተሰቦች እስከ ካርታ ሥራው ውቅት ድረስ ያልተመለሱ" የሚል መረጃ ሊፃፍ ይችላል:: ይህ መረጃ ለቆጠራ እቅድ አውጪ አካላት ምንም እንኳን በካርታው ሥራ ወቅት የመንደሩ ነዋሪዎች ባይገኙም ወደፊት በቆጠራው ወቅት በመንደራቸው ተገኝተው እንደሚቆጠሩ ያመለክታል:: እነዚህን የመሳሰሉ የተለያዩ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ መረጃዎቹን መፃፍ ያስፈልጋል::

5. የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔት ንባቦች በመነሻ ካርታ ላይ በሚሰፍርበት ጊዜ በእያንዳንዱ ኪ.ሜ ስኩየር በሚገኙ ሜትሮች ትክክለኛውን የመስፈርት ማበጣ ቁጥር (Scale factor) መጠቀማችንን ማረጋገጥ ይኖርብናል:: ለምሳሌ:- 0.002 ለ1:50000 መስፈርት:: 0.004 ለ1:25000 መስፈርት ... ወዘተ መጠቀማችንን ማረጋገጥ ይኖርብናል::

6. የአንድ ቀበሌ ድንበር ወንዝን የሚከተል ሆኖ የተገኘ እንደሆነና የመነሻ ካርታዎች ተዘጋጅተው የተሰጡን ከሆነ የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ የምንወስደው ድንበሩ ወንዙን የሚገኝበትትና የሚለቅበት ነጥቦች ላይ ብቻ ይሆናል:: አዲስ ንድፍ የሚሰራ ከሆነና ወንዙ የቀበሌው ድንበር ከሆነ በሁሉም የወንዙ መታጠፊያዎች ላይ የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባብ ተወስዶ በንድፉ ላይ የወንዙን ቅርፅ ጠብቆ ይሰፍራል::

5.6 ለከተማ አካባቢዎች የካርታ ሥራ ቅጾች ዓነትና ይዘት

5.6.1 ቅጽ ከ-1: የከተሞች፤ የወረዳዎች/የከፍተኞችና የቀበሌዎች መመዝገቢያ ቅጽ:

ይህ ቅጽ ከተሞችኝ፤ ወረዳዎችን/ከፍተኞችንና ቀበሌዎችን ለመመዝገብ ያገለግላል::

ክፍል 1: የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1-3 ክልል፤ ዞንና ወረዳ:- በእነዚህ አምዶች ከተሞቹ፤ ከፍተኞቹ/ወረዳዎቹና ቀበሌዎቹ የሚገኙባቸው ክልል፤ ዞንና ወረዳ ስም ይጻፋል:: ንዑስ አምዶች 1-6 ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግሉ ምንም አይሞላባቸውም::

ክፍል 2: የከተሞች፤ ከፍተኞችና የቀበሌዎች ዝርዝር:-

ዓምድ 4: ተራ ቁጥር:- በዚህ ዓምድ በወረዳው ለሚገኙ ከተሞች በንዑስ አምዶች 7-8 ባለ ሁለት አሀዝ ተከታታይ ተራ ቁጥር ይሰጣል::

ዓምድ 5-6:- እነዚህን ዓምዶች በትክክል ለመሙላት በምዕራፍ 2 ላይ የተሰጠውን የከተማ ትርጉምና በዚሁ ገፅ ከዓምድ 6 በታች የተዘረዘረውን የከተማ ደረጃ ዓይነት በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል::

ዓምድ 5: የከተማ ስም:- በዚህ ዓምድ በወረዳው ውስጥ የሚገኙ ከተሞች ስም ይጻፋል:: ከአንድ በላይ ስም ያለው ከተማ ሲያጋጥም ዋነኛው ስም በቅድሚያ ይጻፍና ሁለተኛው ስም በቅንፍ ውስጥ ይፃፋል:: ንዑስ አምድ 9 ለቢሮ ሥራ ስለሚያገለግል ምንም አይሞላበትም::

ዓምድ 6: የከተማ ደረጃ:- በዚህ ዓምድ /በንዑስ ዓምዶች 10-11/ ቀጥሎ ከተዘረዘሩት የከተሞች ደረጃ መካከል የከተማውን ትክክለኛ ደረጃ የሚያሳየውን በመምረጥ ለደረጃው የተሰጠው መለያ ቁጥር (ኮድ) ይሞላል::

መለያ ቁጥር (ኮድ)	ደረጃ
01	ማዘጋጃ ቤት ያለው የወረዳ ዋና ከተማ
02	ማዘጋጃ ቤት ያለው የዞን ዋና ከተማ
03	ማዘጋጃ ቤት ያለው የክልል ዋና ከተማ
04	ማዘጋጃ ቤት የሌለው የወረዳ ዋና ከተማ
05	ማዘጋጃ ቤት የሌለው የዞን ዋና ከተማ
06	ማዘጋጃ ቤት ያለው የወረዳና የዞን ዋና ከተማ
07	ማዘጋጃ ቤት ያለው የዞንና የክልል ዋና ከተማ
08	ማዘጋጃ ቤት ያለው የክልል፤ የዞንና የወረዳ ዋና ከተማ
09	ማዘጋጃ ቤት የሌለው የዞንና የወረዳ ዋና ከተማ
10	ማዘጋጃ ቤት ያለው የክልልና የወረዳ ዋና ከተማ
11	ማዘጋጃ ቤት ያለው ግን ከላይ ከተገለጹት ውጭ የሆነ ከተማ
12	ማዘጋጃ ቤት የሌለው ቀበሌ ግን ያለው ከላይ ከተገለጹት ውጭ የሆነ ከተማ
13	ማዘጋጃ ቤት የሌለውና ቀበሌም የሌለው ከተማ

ምሣሌ:

- ሞጆ የሎሚ ወረዳ ዋና ከተማና ማዘጋጃ ቤት ያለው በመሆኑ በዓምድ 6 ማዘጋጃ ቤት ያለው የወረዳ ዋና ከተማ ለሚለው የተሰጠው ኮድ "01" ይሞላል::
- አሰላ የጢዮ ወረዳና የአርሲ ዞን ዋና ከተማ እንዲሁም ማዘጋጃ ቤት ያለው በመሆኑ በዓምድ 6 ማዘጋጃ ቤት ያለው የወረዳና የዞን ዋና ከተማ ለሚለው የተሰጠው ኮድ "06" ይሞላል::
- አሶሳ የአሶሳ ወረዳ፤ የአሶሳ ዞንና የቤንሻንጉል ጉምዝ ክልል ዋና ከተማና ማዘጋጃ ቤት ያለው በመሆኑ በዓምድ 6 ማዘጋጃ ቤት ያለው የክልል፤ የዞንና የወረዳ ዋና ከተማ ለሚለው የተሰጠው ኮድ "08" ይሞላል::

ዓምድ 7: **ተራ ቁጥር**:- በዚህ አምድ በከተማው ውስጥ ለሚገኙት ከፍተኞች/ወረዳዎች ባለሁለት አሀዝ የመለያ ቁጥር በንዑስ አምዶች 12-13 ይሰጣል::

ዓምድ 8: **የከፍተኛ ቁጥር**:- በዚህ ዓምድ በንዑስ አምዶች 14-15 የከፍተኛው ቁጥር /ስም ካለው ስሙ/ ይሞላል::

ዓምድ 9: **ተራ ቁጥር**:- በዚህ ዓምድ በንዑስ አምዶች 16-17 በከተማው ለሚገኙ ቀበሌዎች ባለሁለት አሀዝ ተከታታይ ተራ ቁጥር ይሰጣል::

ዓምድ 10: **የቀበሌ ቁጥር/ስም**:- በዚህ ዓምድ የቀበሌው ቁጥር/ስም ካለውም ስሙ/ በተሰጠው ባዶ ቦታ ይሞላል:: የቀበሌው ቁጥር እንዳለ የቀበሌው መለያ ቁጥር ተደርጎ በንዑስ አምዶች 18-20 ይሞላል::

ዓምድ 11: **የቀበሌው ሊቀመንበር/ተወካይ ስም**:- በዚህ ዓምድ በምዝገባ ወቅት የቀበሌ ሊቀመንበር/ተወካይ የሆኑት ሰው ሙሉ ስም ይሞላል::

ዓምድ 12: **አስተያየት**:- በዚህ ዓምድ ከአምድ 5-11 በተመለከተ ተጨማሪ አስተያየት እንደ አስፈላጊነቱ ይሰጣል::

በመጨረሻም የካርታ ሠራተኛውና ተቆጣጣሪው ስማቸውን፤ ፊርማቸውንና ቅጹ የተጠናቀቀበትን ቀን በተሰጠው ክፍት ቦታ ማስፈር ይኖርባቸዋል::

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
የከተሞች፡ ወረዳዎች/ከፍተኞችና ቀበሌዎች
መመዝገቢያ ቅጽ

ቅጽ ከ-1

ክፍል 1: የአካባቢ መለያ

1			2			3		
ክልል	1	2	ዞን	3	4	ወረዳ	5	6

ክፍል 2: የከተሞች፡ ወረዳዎች/ከፍተኞችና ቀበሌዎች ዝርዝር

4	5	6	7	8	9	10	11	12
ተራ ቁጥር	የከተማ ስም	የከተማ ደረጃ	ተራ ቁጥር	ክፍተኛ	ተራ ቁጥር	የቀበሌ ቁጥር/ስም	የቀበሌው ሊቀመንበር/ተወካይ	አስተያየት
7 8	9	10 11	12 13	14 15	16 17	18 19 20		

101

የካርታ ሠራተኛው ስም _____ ፊርማ ቀን

የተቆጣጣሪው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____

የከተማ ቀበሌዎች ብዛት	
የገጽ ድምር	ጠቅላላ ድምር

5.6.2 ቅጽ ከ-2: <u>የቤቶችና የቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅጽ</u>

ይህ ቅፅ የቆጠራ ቦታዎችን ለመመሥረት እንዲያስችል ቤቶችን ለመመዝገብ የሚያገለግል ሲሆን በተጨማሪም በዚህ ቅፅ በቤቶቹ ውስጥ የሚኖሩ ቤተሰቦችም ይመዘገባሉ። በከተማ ቀበሌ የሚካሄደው (የቤቶችና የቤተሰቦች) ምዝገባ ቤቶችና ቤተሰቦች ሳይዘለሉና ሳይደገሙ ከቤት ቤት በመሄድ ይከናወናል። የቆጠራ ቦታ የመከለል ሥራ ከመከናወኑ በፊት በከተማ ቀበሌ ውስጥ የሚገኙት ቤቶች በሙሉ ታሳቢ የቆጠራ ቦታዎችን ምሥረታ ግምት ውስጥ በማስገባት መመዝገብ ይኖርባቸዋል። ከመቶ በታች ነዋሪዎች በሚገኙባቸው የከተማ የጋርዮሽ መኖሪያዎች ውስጥ የሚገኙ ራሳቸውን የቻሉ ቤተሰቦችና የጋርዮሽ መኖሪያው ስም በቅፅ ከ-2 ላይ መመዝገብ እንደሚኖርባቸው መዘንጋት አይገባም።

ክፍል 1: <u>የአካባቢ መለያ</u>:-

ዓምድ 1-4: <u>ክልል፤ ዞን፤ ወረዳና ከተማ</u>:- በእነዚህ ዓምዶች ምዝገባው የሚካሄድበት የክልል፤ የዞን፤ የወረዳውና የከተማው ስም ይጻፋል። ንዑስ አምዶች 1-7 ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግሉ ምንም አይሞላባቸውም።

ዓምድ 5-6: <u>ከፍተኛና ቀበሌ</u>:- በእነዚህ አምዶች ምዝገባው የሚካሄድበት ከፍተኛና ቀበሌ ቁጥር/ስም ይሞላል። በንዑስ አምዶች 8-9 የከፍተኛው ቁጥር ሲመዘገብ በንዑስ አምዶች 10-12 ደግሞ የቀበሌው ቁጥር እንደ ቀበሌው መለያ ቁጥር ይመዘገባል። በስም ብቻ የሚታወቁ ከተሞች የቀበሌ መለያ ቁጥር በካርታ ሠራተኛው ተሰጥቶ ይመዘገባል።

ዓምድ 7: <u>የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር</u>:- በዚህ ዓምድ በንዑስ አምዶች 13-14 በቀበሌው ውስጥ የተመሠረተው የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር ይሞላል። መለያ ቁጥሩ የሚሞላው የቆጠራ ቦታው ከተከለለና መለያ ቁጥር ተሰጥቶ ከተጠናቀቀ በኋላ እንደሆነ መታወቅ አለበት።

ክፍል 2: <u>የቤቶችና የቤተሰቦች ዝርዝር መረጃ</u>

ዓምድ 8: <u>ተራ ቁጥር</u>:- በዚህ ዓምድ በንዑስ አምዶች 15-17 በቆጠራ ቦታው ውስጥ ለሚገኙት ቤቶች በሙሉ ባለ ሶስት አሀዝ ተከታታይ ተራ ቁጥር ይሰጣል። የተራ ቁጥሩ አሰጣጥ የሚጀምረው በየቆጠራ ቦታው ውስጥ ይሆንና በከተማ ቀበሌው ውስጥ የሚገኙት ቤቶች በሙሉ ሊመዘገቡና ተራ ቁጥር ሊሰጣቸው ይገባል። ይህም ለመጀመሪያው ቤት 001፤ ለሁለተኛው 002፤ ...ወዘተ በማለት በታሳቢው የቆጠራ ቦታ ውስጥ ላሉት ቤቶች (ለመኖሪያም ሆነ ለሌላ ለማንኛውም አገልግሎት የሚውሉ) በሙሉ ተራ ቁጥር ይሰጣል።

ዓምድ 9: <u>የቤት ቁጥር</u>:- በዚህ ዓምድ በቀበሌው ወይም በሌላ አካል ለቤቱ የተሰጠው ቁጥር ይመዘገባል:: ከአንድ በላይ የሆኑ ቤቶች በአንድ አጥር ግቢ ውስጥ ይኖሩና ለሁሉም የሚሆን አንድ ቁጥር በግቢው በር ላይ ሊሰጥ ይችላል:: በተጨማሪም አንዳንዱ ቤት ንዑስ ቁጥርም ሊኖረው ይችላል:: እያንዳንዱ ቤት በሚመዘገብበት ወቅት የሚሰጠው ቁጥር ዋናው በር ላይ ያለው የቀበሌ ቁጥር ይሆንና የየቤቱ ንዑስ ቁጥር በእዝባር (/) እየተለየ ይጨመርበታል:: ለምሳሌም ዋናው በር ላይ የተሰጠው ቁጥር 0087 ቢሆንና እግቢው ውስጥ ያሉ አራት ቤቶች 1፡ 2፡ 3፡ 4 ንዑስ ቁጥሮች ቢኖራቸው በዚህ ዓምድ ለመጀመሪያው ቤት የሚሰጠው የቤት ቁጥር 0087/1 ለ2ኛው 0087/2፡ ...ወዘተ ይሆናል ማለት ነው:: የቀበሌ ቁጥር የሌላቸው ቤቶች ቢያጋጥሙ ይህንን ዓምድ ክፍት በመተው ሁኔታውን በአስተያየት አምድ መግለጽ ይገባል::

ዓምድ 10: <u>የቤቱ አገልግሎት</u>:- በዚህ ዓምድ/በንዑስ ዓምድ 18/ የተመዘገበው ቤት በምዝገባ ወቅት የሚሰጠው አገልግሎት ምን እንደሆነ ከሚከተሉት አማራጮች ትክክለኛውን በመምረጥ ይሞላል::

<u>መለያ</u>	<u>አገልግሎት</u>
1	መደበኛ መኖሪያ
2	ከፊል መኖሪያ
3	በመሠራት ላይ ያለ ቤትና ባዶ ቤት
4	ድርጅት

1 = <u>መደበኛ መኖሪያ</u>:- ለመደበኛ የቤተሰብ አባላት መኖሪያ ብቻ የሚያገለግል፡

2 = <u>ከፊል መኖሪያ (መደበኛ መኖሪያና ድርጅት)</u>:- በከፊል ለመደበኛ ቤተሰብ አባላት መኖሪያና በከፊል ለድርጅት አገልግሎት የሚውል፡ የጋርዮሽ መኖሪያ፡

3 = <u>በመሠራት ላይ ያለ ቤትና ባዶ ቤት</u>:- በአገልግሎት ላይ ያልዋለ ወይም ያልተያዘ ቤት/ባዶ ቤት፡ በመሠራት ላይ ያለ ቤት፡ ...ወዘተ፡

4 = <u>ድርጅት</u>:- ለማምረቻ፡ ለአገልግሎትና ንግድ ሥራ (ጫማ፡ ዳቦ፡ ጨርቃጨርቅ፡ ትራንስፖርት፡ ጤና፡ ትምህርት፡ የሕግ፡ የምግብና መጠጥ፡ ሽቀጣሽቀጥ ...ወዘተ):: (ስለ ድርጅት ትርጉም በቂ ግንዛቤ እንዲኖርዎ ለቅጽ ገ-2 የተሰጠውን ማብራሪያ ይመልከቱ::)

<u>ማስታወሻ</u>፡- አንዳንድ ቤተሰቦች የተሰማሩባቸው ጥቃቅን የሥራ መስኮች ለምሳሌ ልብስ ስፌት፤ ቆዳ ማልፋትና መፋቅ፤ ሸክላ ሥራ የቅጥቀጣና የብየዳ ሥራና አነስተኛ ንግዶች የሚከናወኑት ከቤት ውጭ በበርንዳ፤ በዛፍ ጥላ ሥር በወንዝ ዳርና በአጠቃላይም የቤትን ትርጉም በማያሟላ ሥፍራ ሊሆን ይችላል። የዚህ ዓይነት ሁኔታ በሚያጋጥምበት ወቅት (ምንም እንኳን ሥራው ቤቱ ውስጥ ባይከናወንም) የቤቱ አገልግሎት እንደ መኖሪያና ድርጅት ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል።

ዓምድ 11-12: <u>ለመደበኛ መኖሪያ፤ ለከፊል መደበኛ መኖሪያ እና ለጋርዮሽ መኖሪያ የሚያገለግሉ ቤቶችን ብቻ የሚመለከት</u>

ዓምዶች 11-12 የሚያገለግሉት መደበኛ ቤተሰቦችንና ከ100 ነዋሪዎች በታች የሚገኙባቸውን የጋርዮሽ መኖሪያዎች ለመመዝገብ ነው።

ዓምድ 11: <u>ተራ ቁጥር</u>፡- በዚህ ዓምድ /በንዑስ አምዶች 19-21/ ለቤተሰቦችና ለጋርዮሽ መኖሪያዎች የሚሰጠው ተራ ቁጥር ተከታታይነት ሊኖረው ይገባል። በአንድ ቤት ውስጥ ከአንድ በላይ ቤተሰቦች የሚኖሩ ከሆነ በዚህ ዓምድ ለእያንዳንዳቸው የተለያየ ተራ ቁጥር መሰጠት አለበት። የቤቱ ተራ ቁጥር (ዓምድ 8) ግን ተደጋግሞ ይፃፋል።

ዓምድ 12: <u>የቤተሰብ ኃላፊ/የጋርዮሽ መኖሪያ ስም</u>፡- በዚህ ዓምድ የቤተሰቡ ኃላፊ ሙሉ ስም ወይም ከ100 በታች የሚሆኑ ነዋሪዎች የሚኖሩበት የጋርዮሽ መኖሪያ ስም ይመዘገባል። በእዚህ ዓይነቱ የጋርዮሽ መኖሪያ ውስጥ ራሳቸውን የቻሉ ቤተሰቦች የሚኖሩ ከሆነ የየቤተሰቡ ኃላፊ ስም በዚህ ዓምድ ውስጥ መመዝገብ ይኖርበታል።

ዓምድ 13: <u>የቤተሰቡ አባላት /የጋርዮሽ ነዋሪዎች ብዛት</u>፡- በዚህ ዓምድ በየቤተሰቡ ያሉትን አባላት ብዛት ኃላፊውን ጨምሮ በጾታ በመለየት ይመዘገባል። በተጨማሪም የጋርዮሽ ነዋሪዎችም ብዛት በፆታ ተለይቶ ይመዘገባል። የወንዶችን ብዛት በንዑስ አምዶች 22-23፤ የሴቶችን ብዛት በንዑስ አምዶች 24-25 የሁለቱን ድምር ደግሞ በንዑስ አምዶች 26-27 ይሞላል። የጋርዮሽ መኖሪያው ባለቤቶች ወይም አስተዳዳሪዎች የራሳቸውን ቤተሰብ ይዘው በጋርዮሽ መኖሪያው ውስጥ የሚኖሩ ከሆነ በምዝገባው ወቅት እንደጋርዮሽ ነዋሪ ሳይሆን ራሳቸውን ችለው እንደ ቤተሰብ ይመዘገባሉ።

ዓምድ 14: <u>በዓምድ 10 ኮድ 2 ወይም ኮድ 4 ለተሞላላቸው የድርጅቱ ዓይነት ምንድነው</u>?

በዓምድ 10 ኮድ 2 ወይም ኮድ 4 ለተሞላላቸው የድርጅቱ ዓይነት ተጠይቆ ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት ስምና የኮድ ቁጥሩ በዚህ ዓምድ ይሞላል::

ኮንስትራክሽን	1
የከበሩ ማዕድናትን ማውጣት(Minning)	2
ቁፋሮ/አሸዋ፤ ድንጋይና የመሳሰሉትን Quarring	3
የጎጆ/ዕደ-ጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	4
የአነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	5
የወፍጮ አገልግሎት	6
የትላልቅና መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ	7
የጅምላ ንግድ	8
የችርቻሮ ንግድ	9
የአገልግሎት ሰጪ ንግድ	10
ሌሎች	11

<u>ማስታወሻ</u>:- የድርጅቱ ዓይነት በሚጠየቅበት ጊዜ በአንድ ቤት ውስጥ ከአንድ በላይ የሆነ የድርጅት ዓይነት ካጋጠመ ከፍተኛ ገቢ የሚገኝበት የድርጅት ዓይነት ይወሰዳል::

የድርጅቶች ዓይነት ትረጉም ከዚህ በታች የተገለፀ በመሆኑ በዚሁ መሠረት ኮዶቹ በሚሞሉበት ጊዜ ትርጉሞቹን በሚገባ መረዳት ያስፈልጋል::

1. <u>ኮንስትራክሽን</u>:- የኮንስትራክሽን ሥራ በአብዛኛው ቋሚ ንብረትን ማለትም ከአንድ ዓመት በላይ የአገልግሎት ዘመን የሚሰጡ ንብረቶችን ለመገንባት፤ ለማደስና ለመጠገን የሚካሄድ የሥራ እንቅስቃሴን ያጠቃልላል:: ለምሳሌም የኮንስትራክሽን ሥራ ሕንጻዎችን አውራ መንገዶችን፤ የውስጥ ለውስጥ መንገዶችንና ድልድዮችን፤ የውሃ መውረጃ ቱቦዎችን፤ የውሃና የኤሌክትሪክ መስመሮችን፤ የአውሮፕላን ማረፊያዎችን፤ የመኪና ማቆሚያዎችን፤ ግድቦችን፤ የውሃ ጉድጓዶችን፤ የመገናኛ መስመሮችን ማለትም የቴሌፎንና የቴሌግራም መስመሮችን፤ የወደብ ሥራዎችንና የመሳሰሉትን የመገንባት፤ የማሻሻል ወይም የመለወጥ፤ የማደስና የመጠገን የሥራ ሂደቶችን ሁሉ ያጠቃልላል::

2. <u>የከበሩ ማዕድናትን (Mining) ማውጣት</u>:- ወርቅ፤ ብር፤ ነሐስ፤ ፕላቲኒየምና የመሳሰሉትን የከበሩ ማዕድናት ከከርሰ ምድር ውስጥ ማውጣትን የሚያጠቃልል ነው::

3. <u>የቁፋሮ (Quarring)</u>:- ሥራ ለግንባታ ወይም ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ ድንጋይ፤ አሸዋ፤ እምነበረድና ኖራ የመሳሰሉትን ከመሬት ውስጥ ወይም ላይ ማውጣትን ሥራን ያጠቃልላል::

4. <u>የጎጆ/ዕደ-ጥበብ ማምረቻ ኢንዱስትሪ</u>፡- የሚባለው በአንድ ስፍራ የተለየ አድራሻ ያለው፤ አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ ሆኖ አብዛኛው ምርቱን በእጅ ወይም በእግር (በሰው ኃይል) የሚንቀሳቀስ መሣሪያ በመጠቀም አንድ ወይም የተለያዩ ምርቶችን ለገበያ የሚያመርት የሥራ መስክ/ድርጅት ነው።

5. <u>አነስተኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ</u>፡- የሚባለው በአማካኝ ዘጠኝና ከዚያ በታች በሥራው ተካፋይ የሆኑ ሠራተኞች ያሉትና በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ያለው፤ አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ ሆኖ በኢነርጂ ወይም በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ መሣሪያ በመጠቀም አንድ ወይም የተለያዩ ምርቶችን በማምረት ለገበያ የሚያቀርብ ወይም የአገልግሎት ዋጋ በማስከፈል የማምረት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅትን የሚያካትት ነው።

6. <u>የወፍጮ አገልግሎት</u>፡- ከደንበኞች ጥሬ ዕቃን በመቀበልና የአገልግሎት ክፍያን በማስከፈል የማምረት አገልግሎት የሚሰጥ ድርጅት በዚህ ሥር ይመደባል። ድርጅቱ የማምረት አገልግሎት የሚሰጠው በሞተር ኃይል፤ በነዳጅ፤ በውሃና በንፋስ የሚንቀሳቀስ መሣሪያ በመጠቀም መሆን ይኖርበታል።

7. <u>የትላልቅ ወይም መካከለኛ ማምረቻ ኢንዱስትሪ</u>፡- የሚባለው በአማካይ አሥርና በላይ ሠራተኞችን የሚያሰራ፤ በአንድ ሥፍራ የተለየ አድራሻ ያለው፤ አብዛኛውን ጊዜ በአንድ ሥራ አስኪያጅ ወይም ባለቤት የሚመራ ሆኖ በኢነርጂ ወይም በሞተር ኃይል የሚንቀሳቀስ መሣሪያ በመጠቀም አንድ ወይም የተለያዩ ምርቶችን የሚያመርት ፋብሪካን ሁሉ የሚያካትት ነው።

8. <u>የጅምላ ንግድ</u>፡- የጅምላ ንግድ ማለት አዳዲስ ወይም አሮጌ ዕቃዎችን/ቀደም ሲል የነበራቸውን አሠራር ወይም ቅርጻቸውንና ባህሪያቸውን ሳይለውጥ /ለኢንዱስትሪዎች፤ ለንግድ ተቋማት፤ ለድርጅቶች፤ ለቸርቻሪዎች፤ ለፕሮፌሽናል ተጠቃሚዎች፤ ለሌሎች የጅምላ ነጋዴዎች ... ወዘተ የመሸጥ ተግባር ማለት ነው። በዚህ ሥር ለሚሸጡት ሸቀጥ በቀጥታ ባለቤት የሆነ የጅምላ ነጋዴዎችና ወኪሎች በሙሉ ይጠቃለላሉ። ምሣሌ፡- አስመጪዎች፤ ላኪዎች የኢንዱስትሪም ሆነ የእርሻ ምርት በጅምላ አከፋፋዮች፤ በጅምላ የሚሸጡ የህብረት ሥራ ማህበራት ነዳጅ በማከማቸት በጅምላ የሚሸጡ ዲፖዎች ...ወዘተ በጅምላ ንግድ ድርጅትነት ሥራ የሚጠቃለሉ ናቸው።

9. <u>የችርቻሮ ንግድ</u>፡- የችርቻሮ ንግድ ማለት አዳዲስ ወይም አሮጌ ዕቃዎችን /ቀደም ሲል የነበራቸው አሠራር ወይም ቅርጻቸውንና ባህሪያቸውን ሳይለውጥ /ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለግል ወይም ለቤተሰብ ፍጆታ ወይም ጥቅም መልሶ የመሸጥ ተግባር ማለት ነው። በችርቻሮ የንግድ ዘርፍ ለሚሸጡት/ለሚቸረቸሩት/ ሸቀጥ በቀጥታ ባለቤት የሆኑ የችርቻሮ ንግድ መደብሮች በሙሉ ይጠቃለላሉ። ለምሳሌ፡- ሱቆች፤ ኪዎስኮች፤ የገበያ መደብር፤ በችርቻሮ ንግድ የተሰማሩ የህብረት ሥራ ማህበራት ሱቆች፤ የጽህፈት መሣሪያዎች፤ የመጽሐፍት ንግድ፤

የቢሮ ዕቃዎች ንግድ፤ የተዘጋጁ ልበሶች ንግድ፤ ያገለገሉ ዕቃዎች ችርቻሮ መደብር፤ የግልና የቤት ዕቃዎች ጥገናና እድሳት መደብር/ ምሳሌ፡- የጫማ፤ የኤሌክትሪክ ዕቃዎች፤ ሰዓትና ጌጣጌጥ፤ ወዘተ መድኃኒት ቤቶች ... ወዘተ

10. <u>የአገልግሎት ሰጪ ንግድ</u>፡- የአገልግሎት ሰጪ ንግድ ማለት ለግል፤ ለቤተሰብ ወይም ለድርጅቶች በክፍያ ላይ ተመስርቶ የሚሰጥ የልዩ ልዩ አገልግሎቶች የንግድ ተግባር ማለት ነው። በዚህ የንግድ ዘርፍ የሚካተቱ የአገልግሎት ሰጪ ንግድ ድርጅቶች ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

ለምሳሌም፡-

- ሆቴሎች፤ መኝታ ቤቶችና ሌሎች የአጭር ጊዜ ማረፊያ ቤቶችና የመሳሰሉት፤
- ሬስቶራንት፤ ካፊቴሪያ፤ ቡና ቤትና የመመገቢያና የመጠጥ ቤቶች፤
- የማሽን፤ የመሣሪያ፤ የግልና የቤት ዕቃዎች፤ ማከራየት አገልግሎት፤
- የማስታወቂያ አገልግሎት ... ወዘተ በዚህ ሥር ይጠቃለላሉ።

11. <u>ሌሎች</u>፡- ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት የድርጅት ዓይነቶች የተለየ ካጋጠመ በዚህ ስር ይካተታል።

<u>ማስታወሻ 1</u>፡- በእያንዳንዱ የቅጹ ገጽ በአምድ 13 የተሞላውን መረጃ ቁልቁል በመደመር በተሰጠው ክፍት ቦታ ድምሩን አስቀምጥ። በመቀጠልም የየገጹን ድምር የሚያጠቃልል አጠቃላይ ድምርም በመጨረሻው የቅጹ ገጽ ላይ በተሰጠው ቦታ መሞላት ይኖርበታል።

<u>ማስታወሻ 2</u>፡- የማምረቻ ድርጅቱ በሥራው ያሰማራው የሰው ኃይል ቁጥር የሚወሰደው የካርታ ሥራው በሚሠራበት ወቅት ሲሆን ይህም በድርጅቱ ሥራ ላይ የተሰማሩትን ባለንብረቶች፤ ሽርኮች፤ የቤተሰብ አባል ሠራተኞች፤ ተለማማጅ የሚከፈላቸው፤ ተለማማጅ የማይከፈላቸው፤ ቋሚ ተቀጣሪ ሠራተኞችንና ጊዜያዊ ሠራተኞችን በሙሉ ያጠቃልላል።

በመጨረሻም ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ የካርታ ሠራተኛውና ተቆጣጣሪው ስማቸውን፤ ፊርማቸውንና ሥራው የተጠናቀቀበትን ቀን በተሰጠው ክፍት ቦታ ማስፈር ይኖርባቸዋል።

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
የቤቶችና ቤተሰቦች መመዝገቢያ ቅፅ

ቅፅ ከ-2

ክፍል 1:- የአካባቢ መለያ

1	2	3	4	5	6	7
ክልል	ዞን	ወረዳ	ከተማ	ከፍተኛ	ቀበሌ	የቆጠራ ቡድን
1 2	3 4	5 6	7	8 9	10 11 12	13 14

ክፍል 2:- የቤቶችና ቤተሰቦች ዝርዝር መረጃ

8			9	10		11			12	13						14	
ተራ ቁጥር			የቤት ቁጥር	የቤቱ አገልግሎት		ተራ ቁጥር			የቤተሰቡ ኃላፊ/ የጋርዮሽ መኖሪያው ስም	የቤተሰብ አባላት/የጋርዮሽ ነዋሪዎች ብዛት						በዓምድ 10 ኮድ 2 ወይም ኮድ 4 ለተሞላላቸው የድርጅቱ አይነት ምንድን ነው?	
										ወ		ሴ		ድምር			
15	16	17			18	19	20	21		22	23	24	25	26	27		ኮድ

5.6.3 ቅጽ ከ-3: በከተማ የጋርዮሽ መኖሪያዎች መመዝገቢያ ቅጽ

ይህ ቅጽ በከተማ የሚገኙ የጋርዮሽ መኖሪያዎችን በሙሉ ለመመዝገብ ያገለግላል። በዚህ ቅጽ የሚመዘገቡ የጋርዮሽ መኖሪያዎች ከ100 በታች ወይም በላይ ነዋሪዎች የሚኖሩባችው ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ቅፅ የሚሞላው በከተማው አስተዳደር ጽ/ቤት ይሆንና በመስክ ሥራ ወቅት ግን የማጣራት ሥራ ይከናወናል። በመስክ ሥራ ወቅት በከተማው አስተዳደር ጽ/ቤት በተደረገው ምዝገባ ያልተካተቱ የጋርዮሽ መኖሪያዎች መኖራቸው ሲረጋገጥ ወዲያውኑ በቅጹ ላይ መመዝገብ ይኖርባቸዋል።

ክፍል 1: የአካባቢ መለያ

ዓምድ 1-4: ክልል፤ ዞን፤ ወረዳና ከተማ፡- በእነዚህ አምዶች የጋርዮሽ መኖሪያው የሚገኝበት ክልል፤ ዞን፤ ወረዳና የከተማ ስሞች ይጻፋሉ። ንዑስ ዓምዶች 1-7 ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግሉ ምንም አይሞላባቸውም።

ክፍል 2: የጋርዮሽ መኖሪያ ዝርዝር መረጃ

ዓምድ 5: ተራ ቁጥር፡- በዚህ ዓምድ (በንዑስ አምዶች 8-9) ለጋርዮሽ መኖሪያዎች ባለሁለት አሀዝ ተከታታይ ተራ ቁጥር ይሰጣል።

ዓምድ 6: የቤት ቁጥር፡- በዚህ ዓምድ በቀበሌው ወይም በሌላ አካል ለጋርዮሽ መኖሪያው የተሰጠው የቤት ቁጥር ይመዘገባል። በከተማው አስተዳደር ጽ/ቤት ምዝገባው ሲከናወን የቤት ቁጥሩ ላይታወቅ ይችላል። በዚህ ጊዜ በመስክ እየተጠየቀ ይሞላል።

ዓምድ 7: የጋርዮሽ መኖሪያው ስም፡- በዚህ ዓምድ የጋርዮሽ መኖሪው ስም ይጻፋል። የጋርዮሽ መኖሪያው በባለቤቱ/አስተዳዳሪው ስም የሚታወቅ ከሆነ የባለቤቱ/የአስተዳዳሪው ስም ይጻፋል።

ዓምድ 8: አድራሻ፡- በዚህ አምድ የጋርዮሽ መኖሪያውን አድራሻ ማለትም የሚገኝበትን ክፍተኛ/ወረዳ፤ ቀበሌ ስም/ቁጥርና የፖስታ ሣጥን ቁጥር /ካለው/ ይመዘገባል።

ዓምድ 9: የጋርዮሽ መኖሪያው አገልግሎት፡- በዚህ ዓምድ የጋርዮሽ መኖሪያው የሚሰጠው አገልግሎት ይመዘገባል። ለምሣሌ የጋርዮሽ መኖሪያው የሚሰጠው አገልግሎት፤ አዳሪ ት/ቤት፤ የጤና አገልግሎት፤ የኃይማኖት ድርጅት፤ ወህኒቤት፤ ገዳም፤ ...ወዘተ ሊሆን ይችላል።

ዓምድ 10: የነዋሪዎች ብዛት፡- በዚህ ዓምድ በጋርዮሽ መኖሪያው ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎችን ብዛት በጾታ በመለየት ይመዘገባል። የወንዶችን ብዛት በንዑስ አምዶች 10-12፤ የሴቶችን ብዛት በንዑስ አምዶች 13-15 እና የሁለቱን ድምር ደግሞ በንዑስ አምዶች 16-19 መመዝገብ ያስፈልጋል።

ዓምድ 11: <u>የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር</u>:- በዚህ አምድ በንዑስ አምዶች 20-21 እያንዳንዱ የጋርዮሽ መኖሪያ የሚገኝበትን የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር ይመዘገባል:: ይህ አምድ የሚሞላው የቆጠራ ቦታዎች ምሥረታ ከተጠናቀቀ በኋላ ነው:: የጋርዮሽ መኖሪያው ልዩ የቆጠራ ቦታ ከወጣው የልዩ ቆጠራ ቦታው መለያ ቁጥር /91፤ 92፤ 93 ...ወዘተ/ እየተባለ መመዝገብ ይኖርበታል::

ዓምድ 12: <u>አስተያየት</u>:- በዚህ ዓምድ ስለጋርዮሽ መኖሪያዎች ተጨማሪ መግለጫዎች እንደ አስፈላጊነታቸው ይጻፋሉ::

በመጨረሻም ምዝገባው ከተጠናቀቀ በኋላ የካርታ ሠራተኛውና ተቆጣጣሪው ስማቸውን፤ ፊርማቸውንና ምዝገባው የተጠናቀቀበትን ቀን በተሰጠው ቦታ ማስፈር አለባቸው::

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
በከተማ የጋርዮሽ መኖሪያዎች መመዝገቢያ ቅጽ

ቅጽ ከ-3

ክፍል 1: የአካባቢ መለያ

1			2			3			4	
ክልል	1	2	ዞን	3	4	ወረዳ	5	6	ከተማ	7

ክፍል 2: የጋርዮሽ መኖሪያ ዝርዝር መረጃ

5		6	7	8			9	10										11		12
ተራ ቁጥር		የቤት ቁጥር	የጋርዮሽ መኖሪያው ስም	የጋርዮሽ መኖሪያው አድራሻ			የጋርዮሽ መኖሪያው አገልግሎት	የነዋሪዎች ብዛት										የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር		አስተያየት
								ወንድ			ሴት			ድምር						
8	9			ከፍተኛ	ቀበሌ	ፖ.ሣ. ቁ		10	11	12	13	14	15	16	17	18	19		20	21	

የካርታ ሠራተኛው ስም_____ ፊርማ _____ቀን _____

የተቆጣጣሪው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____

5.6.4 ቅጽ ከ-4: <u>የልዩ ቆጠራ ቦታ መመዝገቢያ ቅጽ (100 እና ከዚያ በላይ ነዋሪዎች ያሉባቸው የጋርዮሽ መኖሪያዎች)</u>

ይህ ቅጽ 100 እና ከዚያ በላይ ነዋሪዎች የሚገኙበትን የጋርዮሽ መኖሪያ ዝርዝር መረጃና በዚያ ውስጥ የሚኖሩ ራሳቸውን የቻሉ ቤተሰቦችን ለመመዝገብ የሚያገለግል ነው::

ክፍል 1:- <u>የአካባቢ መለያ</u>

ዓምድ 1-3: <u>ክልል፤ ዞን፤ ወረዳ</u>:- በእነዚህ አምዶች የጋርዮሽ መኖሪያው የሚገኝበት ክልል፤ ዞንና ወረዳ ስሞች ይጻፋል:: ንዑስ ዓምዶች 1-6 ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግሉ ምንም አይሞላባቸውም::

ዓምድ 4-6: <u>ከተማ፤ ከፍተኛና ቀበሌ</u>:- በእነዚህ አምዶች (ንዑስ ዓምዶች ከ7-12) የጋርዮሽ መኖሪያው የሚገኝበት ከተማ፤ ከፍተኛና ቀበሌ ስም/ቁጥር ይጻፋል::

ዓምድ 7: <u>የቆጠራ ቦታ</u>:- በዚህ ዓምድ (በንዑስ ዓምዶች 13-14) የልዩ ቆጠራ ቦታው የመለያ ቁጥር ይመዘገባል::

ዓምድ 8: <u>የጋርያሽ መኖሪያው ስም</u>:- በዚህ ዓምድ የጋርዮሽ መኖሪያው መጠሪያ ስም ይመዘገባል::

ዓምድ 9: <u>የጋርዮሽ መኖሪያው አገልግሎት</u>:- በዚህ ዓምድ የጋርዮሽ መኖሪያው የሚሰጠው አገልግሎት ይመዘገባል::

ዓምድ 10: <u>የፖስታ ሣጥን ቁጥር</u>:- በዚህ ዓምድ የጋርዮሽ መኖሪያው የፖስታ ሣጥን ቁጥር /ካለው/ ይመዘገባል::

ክፍል 2:- <u>የጋርዮሽ መኖሪያው ነዋሪዎች/የቤተሰብ አባላት ብዛት</u>

ዓምድ 11: <u>ጠቅላላ የነዋሪዎች ብዛት</u>:- በዚህ ዓምድ በጋርዮሽ መኖሪያው የሚኖሩትን ነዋሪዎች ብዛት በጾታ በመለየት የወንዶችን ብዛት በንዑስ ዓምዶች 15-18፤ የሴቶችን ብዛት በንዑስ ዓምዶች 19-22 እና ጠቅላላ ብዛት ደግሞ በንዑስ ዓምዶች 23-26 ይሞላል:: በዚህ ውስጥ በጋርዮሽ መኖሪያው የሚኖሩ ራሳቸውን የቻሉ ቤተሰብ አባላት አይጨመሩም::

ዓምድ 12: <u>ጠቅላላ የመደበኛ የቤተሰብ አባላት ብዛት</u>:- በዚህ ዓምድ በጋርዮሽ መኖሪያው የሚኖሩ ራሳቸውን በቻሉ ቤተሰቦች ውስጥ ያሉትን አባላት ብዛት በጾታ በመለየት የወንዶችን ብዛት በንዑስ ዓምዶች 27-29፤ የሴቶችን ብዛት በንዑስ ዓምዶች 30-32 እና ጠቅላላ ብዛት ደግሞ በንዑስ ዓምዶች 33-35 ይሞላል:: ይህ መረጃ በጋርዮሽ መኖሪያው የሚገኙ ቤተሰቦች በሙሉ ከተመዘገቡ በኋላ የአባላቱን ብዛት በያታ ለይቶ በመደመር ይገኛል::

ክፍል 3:- <u>በጋርዮሽ መኖሪያው ውስጥ የሚገኙ መደበኛ ቤተሰቦች ዝርዝር</u>

ዓምድ 13: <u>ተራ ቁጥር</u>:- በዚህ ዓምድ በንዑስ ዓምዶች 36-37 በጋርዮሽ መኖሪያው ውስጥ ለሚኖሩ መደበኛ ቤተሰቦች ከ01 በመጀመር ባለሁለት አሃዝ ተከታታይ ተራ ቁጥር ይሰጣል::

ዓምድ 14: <u>የቤተሰብ ኃላፊ ስም</u>:- በዚህ ዓምድ በጋርዮሽ መኖሪያው ውስጥ የሚገኘው የእያንዳንዱ መደበኛ ቤተሰብ ኃላፊ ሙሉ ስም ይመዘገባል::

ዓምድ 15: <u>የቤተሰብ አባላት ብዛት</u>:- በዚህ ዓምድ የየቤተሰቡን አባላት ብዛት በጾታ በመለየት የወንዶችን ብዛት በንዑስ ዓምዶች 38-39፤ የሴቶችን ብዛት በንዑስ ዓምዶች 40-41 እና ጠቅላላ ብዛት ደግሞ በንዑስ ዓምዶች 42-43 ይሞላል::

የዓምድ 16: <u>አስተያየት</u>:- በተሰጠው ክፍት ቦታ ስለጋርዮሽ መኖሪያው እና ስለ ቤተሰቦች ተጨማሪ መረጃ እንደ አስፈላጊነቱ ይፃፋል::

በመጨረሻም ምዝገባው ከተጠናቀቀ በኋላ የካርታ ሠራተኛውና ተቆጣጣሪው ስማቸውን፤ ፊርማቸውንና ምዝገባው የተጠናቀቀበት ቀን በተሰጠው ቦታ ማስፈር ይኖርባቸዋል::

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
የልዩ ቆጠራ ቦታ መመዝገቢያ ቅፅ
(100ና ከዚያ በላይ ነዋሪዎች የያዘ የጋርዮሽ መኖሪያዎች)

ቅፅ ከ-4

ክፍል 1:- የአካባቢ መለያ -

1			2		3		4	5		6			7			8	9	10
ክልል			ዞን		ወረዳ		ከተማ	ከፍተኛ		ቀበሌ			የቆጠራ ቦታ			የጋርዮሽ መኖሪያው		
	1	2		3		4			5		6	7		8	9	10	11	12	13	14	ስም	አገልግሎት	ፖ.ሣ.ቁ

ክፍል 2:- ጋርዮሽ መኖርያው ነዋሪዎች/የቤተሰብ አባላት ብዛት

	ወንድ				ሴት				ድምር			
11. ጠቅላላ የነዋሪዎች ብዛት	15	16	17	18	19	20	21	22	23	24	25	26

	ወንድ			ሴት			ድምር		
12. ጠቅላላ የመደበኛ ቤተሰብ አባላት ብዛት	27	28	29	30	31	32	33	34	35

ክፍል 3:- በጋርዮሽ መኖሪያ ውስጥ የሚገኙ መደበኛ ቤተሰቦች ዝርዝር

13		14	15						16
ተራ ቁጥር		የቤተሰብ ኃላፊ ስም	የቤተሰብ አባላት ብዛት						አስተያየት
			ወንድ		ሴት		ድምር		
36	37		38	39	40	41	42	43	

የካርታ ሠራተኛው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____

የተቆጣጣሪው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____

5.6.5 ቅጽ ከ-5: <u>የከተማ ቆጠራ ቦታ መግለጫ ቅጽ</u>

ይህ ቅጽ ለተከለለው የከተማ ቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫ መጻፊያ ያገለግላል። የቆጠራ ቦታውን ድንበር ሲገለፅ በቆጠራ ቦታው ውስጥና ውጪ የሚገኙ ቋሚ የሆኑ ሰው ሰራሽና ተፈጥሮአዊ ምልክቶችን መጠቀም ያስፈልጋል። በተቻለ መጠን ፈራሽና ጊዜያዊ የሆኑ ምልክቶችን መጠቀም ክልክል ነው። መግለጫው በማያሻማና በቀላሉ ሊነበብ በሚችል የእጅ ጽሑፍ ሊጻፍ ይገባል። በተጨማሪ የድንበር መግለጫ ዕሁፍ ሲፃፍ መታወስ የሚገባው የቆጠራ ቦታ ካርታው ቢያንስ ለመጭውቹ አሥር ዓመታት የሚያገለግል መሆኑን ነው። ስለቆጠራ ቦታው ድንበር መግለጫ ከመጻፉ በፊት በቅጹ ላይ መግቢያ በሚለው ባዶ ቦታ ወደ ቆጠራ ቦታው እንዴት መድረስ እንደሚቻል አጠር ያለ መግቢያ መጻፍ ይኖርበታል። ከዚያም የድንበር መግለጫው ሲፃፍ ከቆጠራ ቦታው ሰሜናዊ አቅጣጫ በመጀመር በምሥራቅ፤ በደቡብና በምዕራብ በቅደም ተከተል ዞሮ መነሻው ሥፍራ እስኪገጥም ድረስ ያሉትን የያዘ መሆን ይኖርበታል።

ክፍል 1: <u>የአካባቢ መለያ</u>

ዓምድ 1-4: <u>ክልል፤ ዞን ፤ ወረዳና ከተማ</u>:- በእነዚህ አምዶች የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ክልል፤ ዞን ፤ ወረዳና ከተማ ስም ይሞላል። ንዑስ ዓምዶች 1-7 ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግሉ ምንም አይሞላባቸውም።

ዓምድ 5-7: <u>ከፍተኛ፤ ቀበሌና የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር</u>:- በእነዚህ አምዶች የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ከፍተኛና ቀበሌ እንዲሁም የቆጠራ ቦታው መለያ ቁጥር ይመዘገባል። በንዑስ ዓምዶች 8-9 የከፍተኛው፤ በንዑስ ዓምዶች 10-12 የቀበሌውና በንዑስ አምዶች 13-14 ደግሞ የቆጠራ ቦታው መለያ ቁጥሮች ይመዘገባሉ።

ክፍል 2: <u>የቆጠራ ቦታ መግለጫ</u>:-

ዓምድ 8: <u>መግቢያ</u>:- በዚህ ሥፍራ ወደ ቆጠራው ቦታው እንዴት መድረስ እንደሚቻል የሚያስረዳ አጠር ያለ መግለጫ ይጻፋል።

ዓምድ 9: <u>የድንበር መግለጫ ዕሑፍ</u>:- የቆጠራ ቦታው ድንበር መግለጫ ሲጻፍ ከሰሜናዊ አቅጣጫ በመነሳት ወደ ምሥራቅ፤ ደቡብና ምዕራብ አቅጣጫ በመሄድ ይሆናል። የድንበር መግለጫው ሲፃፍ የቆጠራ ቦታውን ድንበር መነሻ ነጥብ በሚገባ መግለፅ ይኖርበታል።

ይህ ቅጽ ከላይ በተብራራው መንገድ ከተሞላ በኋላ ከቆጠራ ቦታው ካርታ ጋር መያያዝ አለበት። መግለጫውን ለመጻፍ ተጨማሪ ቅጽ የሚያስፈልግ ከሆነ ጨምሮ በመጠቀም በእያንዳንዱ ቅጽ ላይ የገጽ ቁጥር በመጻፍ አንድ ላይ ማያያዝ ይገባል።

በመጨረሻም ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ የካርታ ሠራተኛውና ተቆጣጣሪው ስማቸውን፤ ፊርማቸውንና ሥራው የተጠናቀቀበትን ቀን በተሰጠው ክፍት ቦታ ማስፈር ይኖርባቸዋል።

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

የከተማ ቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫ ቅፅ

ቅፅ ከ-5

ክፍል 1፡- የአካባቢ መለያ

1			2			3			4		5			6				7		
ክልል	1	2	ዞን	3	4	ወረዳ	5	6	ከተማ	7	ክፍተኛ	8	9	ቀበሌ	10	11	12	የቆጠራ ቦታ	13	14

ክፍል 2፡- የቆጠራ ቦታ መግለጫ

8. መግቢያ

9. የድንበር መግለጫ ዕሁፍ

ማሳሰቢያ፡ የድንበር ማገናዘቢያ መለያ ነጥቦች (Reference Points) የሚሆኑት ቋሚና በግልፅ ተለይተው የሚታዩ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ገፅታዎች ሲሆኑ የሌላ ቆጠራ ቦታ ድንበር እንደድንበር ማገናዘቢያ መለያ ነጥቦች (Reference Points) መወሰድ የለባቸውም::

የካርታ ሠራተኛው ስም_____ ፊርማ _____ ቀን _____

የተቆጣጣሪው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____

5.6.6 ቅጽ ከ-6: <u>በከተማ የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባብ መመዝገቢያ ቅፅ</u>

ይህ ቅፅ በከተሞች/በከተማ ቀበሌዎች የሚገኙ የድንበር ነጥቦችን፤ የውስጥ ገፅታዎችንና የቆጠራ ቦታ ወሰን መለያ ነጥቦችን የጂ.ፒ.ኤስ ንባቦች ለመመዝገብ ያገለግላል።

<u>ማስታወሻ</u>:- ማስተር ፕላን ለሌላቸው ከተሞች በዚህ ቅፅ የተመዘገቡ የጂ.ፒ.ኤስ ንባቦችን በመጠቀም የንድፍ ሥራ እንደሚሠራ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ክፍል 1: <u>የአካባቢ መለያ</u>

ዓምድ 1-4: <u>ክልል፤ ዞን፤ ወረዳና ከተማ</u>:- በእነዚህ አምዶች የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ የተነበበለት ከተማ የሚገኝበት ክልል፤ ዞን፤ ወረዳ እና ከተማ ስሞች ይመዘገባሉ። ንዑስ ዓምዶች 1-7 ለቢሮ ሥራ ብቻ ስለሚያገለግሉ ምንም አይሞላባቸውም።

ዓምድ 5: <u>የከተማው ደረጃ</u>:- በዚህ ዓምድ (በንዑስ አምዶች 8-9) የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ የተነበበለት ከተማ ደረጃ በቅጽ ከ-1 አምድ 6 የተሰጠውን በመውሰድ ይመዘገባል።

ዓምድ 6:- <u>የከተማ ቀበሌ</u>:- በዚህ ዓምድ የቀበሌው ስም/ቁጥር ይፃፋል። (በንዑስ አምዶች 10-12 ለቀበሌው የተሰጠው ኮድ ይሞላል።)

ዓምድ 7:- <u>ቆጠራ ቦታ</u>: በዚህ ዓምድ (በንዑስ አምዶች 13-14) የቆጠራ ቦታው መለያ ቁጥር ይፃፋል።

<u>ማስታወሻ</u>:- የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ የተነበበው ለከተማ ድንበር ከሆነ በዓምድ 4 የከተማው ስም ይፃፍና ዓምድ 6 እና 7 በሠረዝ /"____"/ ይታለፋሉ። በተመሣሣይ ንባቡ የተወሰደው ለቀበሌው ድንበር ከሆነ በዓምድ 6 የቀበሌው ስም/ቁጥር ይፃፍና ዓምድ 7 በሠረዝ /"__"/ ይታለፋል።

ክፍል 2: <u>ለድንበር ነጥቦች የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ ዝርዝር መረጃዎች</u>

ዓምድ 8: <u>የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባብ ተራ ቁጥር</u>:- በዚህ አምድ የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባብ አወሳሰድን ቅደም ተከተል የሚያመለክት ተከታታይ ተራ ቁጥር ይፃፋል።

ዓምድ 9: <u>መግለጫ</u>:- በዚህ አምድ የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባብ የተወሰደላቸው ነጥቦች ምን እንደሆኑ የሚያመለክት መግለጫ ይፃፋል።

ዓምድ 10: UTM ኢስቲንግ በዚህ አምድ የኢስቲንግ ዩቲኤም(UTM) ኮኦርዲኔቶች በ2-2-3 አሀዝ ተከፋፍለው ይፃፋሉ::

ዓምድ 11: UTM ኖርዚንግ:- በዚህ አምድ የኖርዚንግ ዩቲኤም(ትፍክ) ኮኦርዲኔቶች በ2-2-3 አሀዝ ተከፋፍለው ይፃፋሉ::

ክፍል 3:- ለውስጥ ገፅታዎችና መለያ ነጥቦች የጂፒኤስ ንባብ ዝርዝር መረጃዎች

ዓምድ 12: የጂፒኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባብ ተራ ቁጥር:- በዚህ ዓምድ የጂፒኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባብ አወሳሰድን ቅደም ተከተል የሚያመለክት ተከታታይ ተራ ቁጥር ይፃፋል::

ዓምድ 13: መግለጫ:- በዚህ ዓምድ የጂፒኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባብ የተወሰደላቸው የውስጥ ገፅታዎችና መለያ ነጥቦች ምን እንደሆኑ የሚያመለክት መግለጫ ይፃፋል::

ዓምድ 14: UTM ኢስቲንግ:- በዚህ ዓምድ የኢስቲንግ ዩቲኤም(UTM) ኮኦርዲኔቶች በ2-2-3 አሀዝ ተከፋፍው ይፃፋሉ::

ዓምድ 15: UTM ኖርዚንግ:- በዚህ ዓምድ የኖርዚንግ ዩቲኤም(UTM) ኮኦርዲኔቶች በ2-2-3 አሀዝ ተከፋፍለው ይፃፋሉ::

በመጨረሻም ሥራው ከተጠናቀቀ በኋላ የካርታ ሠራተኛውና ተቆጣጣሪው ስማቸውን፤ ፊርማቸውንና ሥራው የተጠናቀቀበትን ቀን በተሰጠው ክፍት ቦታ ማስፈር ይኖርባቸዋል::

ማስታወሻ:- የቀበሌው ከፍታ በሜትር ማንበብና መመዝገብ ስለሚያስፈልግ በክ-6 ክፍል 3 እንዲመዘገብ ይደረጋል:: ይህም:-

ሀ. የቀበሌው አማካይ ቦታ ላይ የጂ.ፒ.ኤስ ከፊታ ነጥብ (Altitude) አምድ 13 ላይ ይፃፍና ይኸው ይተነበበት ቦታ ኤስቲንግና ኖርዚንግ በአምድ 14 እና 15 ላይ ይፃፋል::

ለ. ቀበሌው የተለያየ ከፍታ ካለው በቀለሌው ሁለት የተለያዩ ቦታዎች / ከፍተኛና ዝቅተኛ / የከፍታ ነጥብ (Altitude) በሜትር ተነቦ በአምድ 13 ላይ ይፃፋል:: በአምድ 14 እና 15 ላይ ምንም አይሞላም::

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

በከተማ የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች ንባብ መመዝገቢያ ቅፅ

ቅፅ ከ-6

ክፍል 1:- የአካባቢ መለያ

1			2			3			4		5			6				7		
ክልል	1	2	ዞን	3	4	ወረዳ	5	6	ከተማ	7	ከተማ ደረጃ	8	9	ቀበሌ	10	11	12	የቆጠራ ቦታ	13	14

ክፍል 2:- ለድንበር ነጥቦች የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ ዝርዝር መረጃዎች

8	9	10	11
የኮኦርዲኔቶች ንባብ ተራ ቁጥር	መግለጫ	UTM ኢስቲንግ	UTM ኖርዚንግ

የካርታ ሠራተኛው ስም_____ ፊርማ _____ ቀን _____

የተቆጣጣሪው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____

ክፍል 2፡- ለድንበር ነጥቦች የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ ዝርዝር መረጃዎች (የቀጠለ)

8	9	10	11
የካኦርዲኔቶች ንባብ ተራ ቁጥር	መግለጫ	UTM ኢስቲንግ	UTM ኖርዚንግ

ክፍል 3:- ለውስጥ ገፅታዎች የጂ.ፒ. ኤስ ንባብ ዝርዝር መረጃዎች

12	13	14	15
የካርዲኔቶች ንባብ ተራ ቁጥር	መግለጫ	UTM ኢስቲንግ	UTM ኖርዚንግ

የካርታ ሠራተኛው ስም_____ ፊርማ _____ ቀን _____

የተቆጣጣሪው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____

ማሳሰቢያ፦ በቅፅ ከ-6 ክፍል 3 የጂ.ፒ.ኤስ ንባብ መረጃ ከሚሰበሰብላቸው የተለያዩ የውስጥ ገፅታዎች መካከል የሚከተሉት ገፅታዎች በክፍል 3 ዓምድ 13 ሙሉ ስማቸው እየተጠየቀ መሣፍ ይኖርበታል።

ቤተክርስቲያን

1.. አርቶዶክስ
2. ካቶሊክ
3. ፕሮቴስታንት
4. መስጊድ

የትምህርት ተቋም

5. አንደኛ ደረጃ ብቻ
6. ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ብቻ
7. መዋዕለ ህፃናት
8. አንደኛ ደረጃና ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ
9. ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃና የቴክኒክና ሙያ
10. የቴክኒክና ሙያ ት/ቤት
11. ኮሌጅ
12. ዩኒቨርሲቲ

የጤና ተቋም

13. ሆስፒታል
14. ጤና ጣቢያ
15. ክሊኒክ
16. ጤና ኬላ
17. የገበያ ቦታ
18. ጥንታዊ ሕንፃ

የማዕድን ቁፋሮ ቦታ

19. ወርቅ
20. ብረት
21. ታንታለም
22. እብነበረድ
23. ሌላ /ይገለጽ/
24. ወፍጮ ቤት
25. ቤንዚን ማደያ
26. ቴሌ
27. ፖስታ ቤት

ፋብሪካ

28. ምግብና መጠጥ
29. ትምባሆ
30. ጨርቃጨርቅና የተሰፋ ልብሶች
31. የቆዳና ጫማ
32. የእንጨት ምርትና ቤት ቁሳቁስ
33. የወረቀትና ማተሚያ
34. የኬሚካልና የኬሚካል ውጤቶች
35. የላስቲክና የፕላስቲክ
36. የብረታብረት ያለሆኑ የማዕድን ውጤቶች
37. የብረታ ብረት

5.6.7 ቅጽ ከ-7: <u>የከተማ ቆጠራ ቦታ መለያዎች ዝርዝር ማስፈሪያ ቅጽ</u>

ይህ ቅፅ የከተማ ቆጠራ ቦታ መለያዎችን ዝርዝር ለማስፈር ያገለግላል። ቅጹ ከተሞላ በኋላ በቆጠራ ቦታ ፋይል የፊት ገጽ ላይ መለጠፍ አለበት።

ዓምድ 1-4: <u>ክልል፤ ዞን፤ ወረዳና ከተማ</u>፡- በእነዚህ ዓምዶች የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ክልል፤ ዞን፤ ወረዳና ከተማ ስሞች ይሞላሉ።

ዓምድ 5-6: <u>ከፍተኛና ቀበሌ</u>፡- በእነዚህ ዓምዶች የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ከፍተኛና ቀበሌ ስም/ቁጥር ይሞላል።

ዓምድ 7: <u>የቀበሌዉ ኃላፊ ስም</u>፡- የቆጠራ ቦታው የሚገኝበት ቀበሌ ሊቀመንበር/ተወካይ ሙሉ ስም በዚህ ዓምድ ይመዘገባል።

ዓምድ 8: <u>የቆጠራ ቦታ የመለያ ቁጥር</u>፡- በዚህ ዓምድ ቀደም ብሎ ለቆጠራ ቦታው የተሰጠው መለያ ቁጥር ይሞላል።

ዓምድ 9: <u>ግምታዊ የቆዳ ስፋት</u>፡- የቆጠራ ቦታው የቆዳ ስፋት ግምት በስኬር ኪሎ ሜትር በዚህ ዓምድ ይሞላል። የቆዳ ስፋት መገመቻ ዘዴ በምዕራፍ 2 ላይ እንደቀረበው ነው።

ዓምድ 10: <u>ጠቅላላ የቤቶች ብዛት</u>፡- በቆጠራ ቦታው ውስጥ የሚገኙት ጠቅላላ የቤቶች ብዛት በዚህ ዓምድ ይመዘገባል።

ዓምድ 11: <u>ጠቅላላ የቤተሰቦች እና አባላት ብዛት</u>፡- በቆጠራ ቦታው ውስጥ የሚገኙት ጠቅላላ የቤተሰቦች ብዛት በዚህ ዓምድ ይመዘገባል። በተጨማሪም የሚከተሉት መረጃዎች በዚህ ዓምድ ሥር ይመዘገባሉ ።

ሀ. በመደበኛ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ጠቅላላ የቤተሰቦችና አባላት ብዛት፤

ለ. በጋርዮሽ መኖሪያ ውስጥ የሚገኙ ጠቅላላ መደበኛ ቤተሰቦችና አባላት ብዛት፤

ዓምድ 12: <u>በጋርዮሽ መኖሪያ የሚገኙ ነዋሪዎች ብዛት</u>፡- በዚህ ዓምድ በቆጠራ ቦታ ውስጥ የጋርዮሽ መኖሪያ ካለ በዚያ የሚገኙትን ነዋሪዎች (የመደበኛ ቤተሰቦች አባላትን ሳይጨምር) ብዛት ይመዘገባል ።

<u>ማስታወሻ</u>፡- ስለ ቆጠራ ቦታው ተጨማሪ አስተያየት ካለ በተሰጠው ክፍት ቦታ ማስፈር ይገባል።

በመጨረሻም የካርታ ሠራተኛውና የተቆጣጣሪው ስማቸውን፤ ፊርማቸውንና ቅጹ የተጠናቀቀበትን ቀን በተሰጠው ቦታ ማስፈር ይኖርባቸዋል።

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

ቅጽ ከ-7

የከተማ ቆጠራ ቦታ መለያዎች ዝርዝር ማስፈሪያ ቅጽ

1. ክልል _____ 6. ቀበሌ _____
2. ዞን _____ 7. የቀበሌው ሊ/መንበር ስም _____
3. ወረዳ _____ 8. የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር_ /የልዩ ቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር___
4. የከተማው ስም _____ 9. ግምታዊ ስፋት _____ ኪ.ሜ ስኩዌር
5. ከፍተኛ _____ 10. ጠቅላላ የቤቶች ብዛት _____
11. ጠቅላላ የቤተሰቦች ብዛት _____
    ሀ. በመደበኛ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ጠቅላላ ቤተሰቦች ብዛት_____ የአባላት ብዛት_____
    ለ. በጋርዮሽ መኖሪያ ውስጥ የሚገኙ ጠቅላላ መደበኛ ቤተሰቦች ብዛት_____ የአባላት ብዛት___
12. በጋርዮሽ መኖሪያ ውስጥ የሚገኙ ጠቅላላ ነዋሪዎች ብዛት_____
13. በጋርዮሽ መኖሪያ ውስጥ የሚኖሩ መደበኛ ቤተሰቦች ውስጥ ያሉ አባላት ጠቅላላ ብዛት_
    አስተያየት:- _____

_____

የካርታ ሠራተኛው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____
የተቆጣጣሪው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____

ማስታወሻ: 1. ይህንን ቅጽ በቆጠራ ቦታ ካርታው ፋይል ፊት ለፊት ሽፋን ላይ ያጣብቁት

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

የከተማ ቆጠራ ቦታ መለያዎች ዝርዝር ማስፈሪያ ቅጽ ቅጽ ከ-7

1. ክልል _____ 6.ቀበሌ _____
2. ዞን _____ 7. የቀበሌው ሊ/መንበር ስም _____
3. ወረዳ _____ 8. የቆጠራ ቦታ መለያ ቁጥር_/የልዩ ቆጠራ ቦታ መለያ/ ቁጥር_____
4. የከተማው ስም _____ 9. ግምታዊ ስፋት _____ ኪ.ሜ ስኩዌር
5. ከፍተኛ _____ 10. ጠቅላላ የቤቶች ብዛት _____
11. ጠቅላላ የቤተሰቦች ብዛት _____
    ሀ. በመደበኛ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ጠቅላላ ቤተሰቦች ብዛት_____ የአባላት ብዛት_____
    ለ. በጋርዮሽ መኖሪያ ውስጥ የሚገኙ ጠቅላላ መደበኛ ቤተሰቦች ብዛት_____ የአባላት ብዛት___
12. በጋርዮሽ መኖሪያ ውስጥ የሚገኙ ጠቅላላ ነዋሪዎች ብዛት_____
13. በጋርዮሽ መኖሪያ ውስጥ የሚኖሩ መደበኛ ቤተሰቦች ውስጥ ያሉ አባላት ጠቅላላ ብዛት_
    አስተያየት:- _____

_____

የካርታ ሠራተኛው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____
የተቆጣጣሪው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____


1. ይህንን ቅጽ በቆጠራ ቦታ ካርታው ፋይል ፊት ለፊት ሽፋን ላይ ያጣብቁት

የካርታ ሠራተኛው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____
የተቆጣጣሪው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን _____

ማስታወሻ: 1. ይህንን ቅጽ በቆጠራ ቦታ ካርታው ፋይል ፊት ለፊት ሽፋን ላይ ያጣብቁት

ዕዝል

ዐዝፅ I - የጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያ ዋና ዋና ገፆች



ዕዝል II


በጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያ ውስጥ የባትሪ ድንጋዮች ትክክለኛ አቀማመጥ ማብራሪያ፡-

በጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያ ውስጥ የባትሪ ድንጋዮችን ለመክተት የሚከተሉትን ማብራሪያዎች ጠንቅቆ መገንዘብ ያስፈልጋል።


1. **በመሣሪያው የባትሪ ድንጋይ መክተቻ ቀዳዳዎች አናት ላይ ያሉትን የፖዘቲቭ (+) እና የኔጋቲቭ (-) ምልክቶች መለየት፣ (ሥዕል 3.1 ገጽ 28 ይመልከቱ)**

2. **በመቀጠልም ከመሣሪያው ጋር በሚታደል የአጠቃቀም መመሪያ** (operating instructions manual) **መሠረት በመመሪያው የባትሪ መክተቻ አናት ያሉትን የፖዘቲቭ(+) እና የኔጋቲቭ (-) ምልክቶችን በባትሪ ድንጋዮቹ ላይ ካሉት ተመሳሳይ ምልክቶች ጋር በማገናዘብ እና በማመሳሰል መክተት፣ (የሚከተሉትን ምሥሎች ይመልከቱ)።**

በመሣሪያው ውስጥ ትክክለኛ የባትሪ ድንጋዮች አቀማመጥ



በመሣሪያው ውስጥ ትክክለኛ ያልሆነ የባትሪ ድንጋዮች አቀማመጥ



<u>ማስጠንቀቂያ</u>፡ ትክክለኛ ያልሆነ የባትሪ ድንጋዮች አቀማመጥ በተጠቃሚው ሰው ላይ አደጋ እና በመሣሪያው ላይ ውድመት ያስከትላል። በተጨማሪም የባትሪ ድንጋይ ኃይል ብክነት ያስከትላል።

3. **አገልግሎት የሰጡ ባትሪ ድንጋዮች በሚቀየሩበት ጊዜ ሁሉም በአንድ ጊዜ መቀየር ይኖርባቸዋል። አዲስና አገልግሎት የሰጡ ባትሪ ድንጋዮች ተቀላቅለው ጥቅም ላይ መዋል አይኖርባቸውም። በተጨማሪም አልካላይን እና ሊቲየም /ኒካድ/ ባትሪ ድንጋዮችን አቀላቅሎ መጠቀም አይቻልም።**

4. አዲስ ባትሪድንጋዮች በመሥሪያው ውስጥ እንደተከተቱ ወዲያውኑ መሣሪያውን በመክፈት የባትሪ መጠን አመልካቹ (Battery Level Indicator) ሙሉ (Full) መሆኑን ማረጋገጥ ያስፈልጋል። ባትሪ ድንጋዮች ተከተው መሥሪያው አልከፈትም ቢል ወይም የባትሪ መጠን አመልካቹ "በከፊል ኃይል የተሞሉ (Partially Charged Condition) ባትሪ ድንጋዮች ተከተዋል" የሚል መለዕክት ከሣየ እንደገና የባትሪ አቀማመጡን መፈተሽ ያስፈለጋል። የባትሪ ድንጋዮቹ አቀማመጥ ተፈትሾ ትክክለኛ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ አሁንም የባትሪ መጠን አመልካቹ ተመሣሣይ መልዕክት የሚያሣይ ከሆነ በመሣሪያው የተከተቱት ባትሪድንጋዮች ምናልባት ለረጅም ጊዜ በመቀመጣቸው ምክንያት ኃይላቸው ተዳክሞ ሊሆን ስለሚችል እነዚህን ባትሪድንጋዮች በሙሉ በማውጣት በአዲስ ባትሪድንጋዮች መተካት ያስፈልጋል።

ቅጽ ከ-6

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
የ1997 የሕዝብና ቤት ቆጠራ

የጂ.ፒ.ኤስ ኮኦርዲኔቶች መመዝገቢያ

ዕዝል III

ክፍል 1: የአካባቢ መለያ

1	2	3	4	5	6
ክልል	ዞን	ወረዳ	የገጠር ቀበሌ	ከተማ	የቆጠራ ቦታ
ኦሮሚያ	ደቡብ ምዕራብ ሸዋ	ኢሉ	-	ተጂ	

ክፍል 2: ለድንበር ነጥቦች የኮኦርዲኔቶች ዝርዝር


7	8	9	10
የኮኦርዲኔት መስመር ነጥብ ቁጥር	መግለጫ	UTM ኢስቲንግ	UTM ኖርዚንግ
1	የመነሻ ነጥብ ከዋና ከመኪና መንገድ ከተጂ ከተማ ሰሜናዊ ምሥራቅ	04-31-489	09-77-282
2	አጥር የድንበር መታጠፊያ	04-31-406	09-77-341
3	ግሣ ላይ ያለ ባሕር ዛፍ የድንበር መታጠፊያ	04-30-998	09-77-410
4	የአጥር ማዕዘን የድንበር መታጠፊያ	04-30-837	09-77-280
5	የአጥር ማዕዘን ት/ቤት አጠገብ መታጠፊያ	04-30-650	09-77-049
6	የግሳ ማዕዘን የድንበር መታጠፊያ	04-29-693	09-75-708
7	ከተጂ ከተማ ደቡባዊ ምዕራብ መኪና መንገድ ድንበር መገናኛ	04-29-748	09-75-652
8	ወንዝና የቀበሌ ድንበር መገናኛ	04-29-959	09-75-357
9	ተጂ ወንዝ ላይ የድንበር መታጠፊያ	04-30-080	09-75-510
10	ተጂ ወንዝ ላይ የድንበር መታጠፊያ	04-30-320	09-75-650
11	ተጂ ወንዝ ላይ የቢጋ መኪና መንገድ ማቋረጫ	04-30-360	09-75-770
12	ተጂ ወንዝ ላይ የድንበር መታጠፊያ	04-30-470	09-76-030
13	ተጂ ወንዝ ላይ የድንበር መታጠፊያ	04-30-750	09-76-350
14	ተጂ ወንዝ ላይ የድንበር መታጠፊያ	04-30-850	09-76-320
15	ተጂ ወንዝ ላይ የድንበር መታጠፊያ	04-31-000	09-76-350
16	ተጂ ወንዝ ላይ የእግር መንገድ ማቋረጫ	04-31-075	09-76-471
17	ተጂ ወንዝ ላይ የድንበር መታጠፊያ	04-31-250	09-76-800
18	ተጂ ወንዝ ላይ የድንበር መታጠፊያ	04-31-610	09-76-770
19	ተጂ ወንዝ ላይ የድንበር መታጠፊያ	04-31-620	09-76-980
20	ተጂ ወንዝ የሚለቅበት የድንበር መታጠፊያ	04-31-642	09-77-258

ክፍል 3: ለውስጥ ገፅታዎች የኮኦርዲኔቶች ዝርዝር

7	8	9	10
የኮኦርዴኔት መስመር ንጥብ ቁጥር	መግለጫ	UTM ኢስቲንግ	UTM ኖርዚንግ
1	ቤተክርስቲያን	04-31-150	09-77-153
2	ትምህርት ቤት	04-30-850	09-76-870
3	ፖስታ ቤት	04-30-980	09-76-680
4	የእህል ወፍጮ ቤት	04-30-890	09-76-630
5	የገበያ ቦታ	04-30-820	09-76-390
6	ከዋናው መኪና መንገድ ወደ አስተዳደር የሚታጠፍበት መንገድ	04-30-250	09-76-120
7	የአስተዳደር ጽ/ቤት	04-30-390	09-75-960
8	ከዋናው መኪና መንገድ ወደ ቢላ ዳለቲ ቀበሌ የሚታጠፍበት መንገድ	04-30-150	09-76-030
9	ሆቴል	04-30-080	09-75-890
10	ክሊኒክ	04-29-940	09-75-740
11	ዋናው መንገድ ከተጂ ከተማ ሰሜናዊ ምሥራቅ	04-31-489	09-77-282
12	ዋናው መንገድ ከተጂ ከተማ ደቡባዊ ምዕራብ	04-29-693	09-75-652

የረዳት ካርታ ሠራተኛ ሥም አለማየሁ ገብረመድህን ፊርማ [signature] ቀን 14-2-95

የተቆጣጣሪ ሥም ደሎ ደጎ ተክለማርያም ፊርማ [signature] ቀን 16-2-95













0430000ME
0431000ME
0977000MN
0976000MN
0975000MN
ሥዕል 5.3
የተጀ ከተማ ካርታ (የ ጀ.፫ኤስ ንድፍ)
ክልል አሮሚያ
ዞን ደቡብ ምዕራብ ሸዋ
ወረዳ ኢሉ
የከተማ ሥም_ተጀ
የቀበሌ ብዛት__ 1
የቆጠራ ቦታ ብዛት
የመቆ/ቦታ ብዛት
መግለጫ
የከተማ ድንበር
የዘወትር መኪና መንገድ
የበጋ መኪና መንገድ
የእግር መንገድ
የዘወትር ወንዝ
ት/ቤት : ቤተክርስቲያን
ከሊኒክ : ጋበደ ቦታ
ሆቴል : አስተዳደር ጽ/ቤት
ፖስታ ቤት : ወፍጮ ቤት
ቤቶች
የድንበር ከአርዳኔት
መስፈርት 1:10,000
በተጀ ከተማ የካርታ ዝግጅት ተሞክሮ የተዘጋጀ
የተቆጣጣሪ ሥም_____ ፊርማ_____ ቀን_____
ቀን_____

ዕዝል IV የካርታ ምልክቶችና መግለጫዎች

ሀ- ድንበሮች

	1	የዓለም አቀፍ ድንበር
	2	የክልል ድንበር
	3	የዞን ድንበር
	4	የ ወረዳ ድንበር
	5	የመቆጣጠሪያ ቦታ ድንበር(ቀደም ሲል የፋሽስት ጦር ሰፈር)
	6	የገጠር ቀበሌ ወይም የከተማ ቀበሌ ድንበር
	7	የቆጠራ ቦታ ድንበር

ለ- ሰው ሰራሽ ገፅታዎች





	1	ትልቅ ሰፈራ(መንደር)
	2	ሳር ቤት፣ ቆርቆሮ ቤት
	3	ቤተክርስቲያን፣ መስጊድ፣ የመቃብር ቦታ ያለው ቤ.ክ
	4	ትምህርት ቤት ት/ቤት ያለው ቤተክርስቲያን
	5	ሆስፒታል፣ ክሊኒክ፣ ጤና ጣቢያ
	6	የገበያ ቦታ
	7	የዘወትር መኪና መንገድ
	8	የበጋ መኪና መንገድ
	9	የእግር መንገድ
	10	የባቡር ሐዲድ
	11	ጥንታዊ ሕንፃ፣ የፈራረሰ ሕንፃ
	12	ጦር ሜዳ
	13	የማዕድን ቁፋሮ ቦታ
	14	የመቃብር ቦታ፣ የክርስቲያን ፣ የእስላም
	15	ድልድይ
	16	ወፍጮ ቤት
	17	የእንጨት መሰንጠቂያ
A	18	የእስተዳደር ጽ/ቤት
H	19	ሆቴል
HA	20	ቋሚ የእውራ ጎዳና ካምፕ
PO	21	ፖስታ ቤት
PS	22	ፖሊስ ጣቢያ
■	23	የክልል ዋና ከተማ
◉	24	የዞን ዋና ከተማ
●	25	የወረዳ ዋና ከተማ
○	26	ሌላ ከተማ

ማስታወሻ: ሁለት ወይም ከዚያ በላይ ወሰኖች አንድ ላይ በአንድነት ሲያጋጥሙ በካርታ ለማመልከት በጉረሻ ትልቅ የሆነውን መውሰድ ይገባል ለምሳሌ የክልልና የወረዳ ድንበሮች በአንድነት ቢያጋጥሙ ሊለፍር የሚገባው የክልሉ ድንበር መሆን አለበት

ለ- ሰው ሰራሽ ገፅታዎች

PP	27	የፖሊስ ንዑስ ጣቢያ
Tel	28	የቴሌኮሙኒኬሽን ጽ/ቤት
FS	29	ቤንዚን ማደያ
	30	የአውሮፕላን ማረፊያ
	31	ፋብሪካ

ሐ- ተፈጥሮአዊ ገፅታዎች

	1	የመደርቅ ወንዝ
	2	ኦረቅ ወንዝ
	3	እየሠረገ የሚሄድ ወንዝ
	4	የውሃ ጉድጓድ፣ ምንጭ፣ የውሃ ማጠራቀሚያ፣ ኩሬ
	5	ግድብ
	6	ረግረጋማ ቦታ
	7	ለውሃ ማጥለቅለቅ የተጋለጠ አካባቢ
	8	ቋፋቴ
	9	ሐይቅ
	10	ተራራ
	11	ረባዳ ወይም የሰጠመ ቦታ
∧∧∧	12	እሳተ ገሞራ የፈነዳበት ቦታ
V	13	ሸለቆ

መ- ዕፀዋትና ተክሎች

1	DF	Dense Forst (ጥቅጥቅ ደን)	ሐ	O	Orange (የብርቱካን ተክል)
2	OW	Open Woodland (ክርክር ደለ ደን)	መ	S	Sisal (የቃጫ ተክል)
3	E	Equalyptus (ባሕር ዛፍ)	ሠ	SU	Sugarcane (የሸንኮራ አገዳ ተክል)
4	G	GrassLand (በሳርየተሸፈነመሬ	ረ	T	Tea (የሻይ ተክል)
5	SC	Scrub (ቁጥቋጦ)	ሰ	VY	Vineyard (የወይን ተክል)
6	PLANTAION (ሠፊእርሻ)		ሸ	CH	Chat (የጫት ተክል)
U	C	Coffee (የቡና ተክል)	ቀ	ET	Enset (የእንሰት ተክል)
ለ	CN	Cotton (የጥጥ ተክል)	በ	OS	Oilseed (የቅባት እህሎች)

ማስታወሻ: ከላይ ከተዘረዘሩት የካርታ ምልክቶችና መግለጫዎች ውጪ ገፅታዎች ቢያጋጥሙ ከተዘረዘሩት ምልክቶች ውስጥ ተስማሚውን ምልክት በመጠቀም የገፅታውን ስም መፃፍ ያስፈልጋል

ዕዝል V

1. የእንቅስቃሴ መከታተያ ዝርዝር ለቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊዎች

1.1 በዋናው መሥሪያ ቤት

የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊ በቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ስር ለሚካሄደው የካርታ ሥራ አስፈላጊ የሆኑትን ካርታዎች፣ የካምፕ መገልገያ ቁሳቁሶች፣ መመሪያዎች፣ የጽሕፈት መሣሪያዎች፣ የተለያዩ ቅጾች፣ እንዲሁም ለክልሉ መስተዳድር ጽ/ቤቶች የተጻፉትን የትብብር ደብዳቤዎችና ሌሎች አስፈላጊ ቁሳቁሶችን ይረከባል።

1.2 በቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ሀ. የቅርንጫፍ ጽ/ቤት ኃላፊው ከዋናው መ/ቤት የተረከበውን የትብብር ደብዳቤ ለአካባቢው መስተዳድር ጽ/ቤቶች ያደርሳል። አስፈላጊውን አስተዳደራዊ ቅድመ ዝግጅቶችን ያከናውናል።

ለ. ከዋናው መ/ቤት የተረከባቸውን የካርታ ሥራ ቁሳቁሶች ለተቆጣጣሪዎች ያስረክባል።

2. የእንቅስቃሴ መከታተያ ዝርዝር ለተቆጣጣሪዎች

2.1 በቅርንጫፍ ጽ/ቤት

ሀ. ተቆጣጣሪዎች አስፈላጊ የሆኑ ካርታዎችን እንደ ባለ 1:50.000 መስፈርት ካርታዎች፣ የከተማ ማስተር ፕላን እና ሌሎች ካርታዎችን ከቅርንጫፍ ጽ/ቤት ይረከባሉ።

ለ. ተቆጣጣሪዎች ለካርታ ሥራው የሚከተሉትን አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ይረከባሉ።

እነርሱም፡-

1. የጂ.ፒ.ኤስ መሣሪያ ከነባትሪ ድንጋይ
2. የእርሳስ መቅረጫ
3. እርሳስ
4. ማስመሪያ
5. እስክሪፕቶ
6. የሌሮይ ብዕር፣ ጫፍና መያዣቸው
7. ሌሮይ ቀለም
8. ላጲስ/ለእርሳስና ለቀለም/
9. ሴሎቴፕ
10. ማስኪንግ ቴፕ
11. ማርከር
12. ማስታወሻ ደብተር
13. የትሬሰንግ ወረቀት ጥቅል
14. የግራፍ ወረቀት
15. ክላሰር
16. ቦርሳ
17. ማስደገፊያ ሰሌዳ
18. እስፒል
19. ቡልዶግ ክሊፕስ
20. ስቴፕለር
21. የስቴፕለር ሽቦ
22. የብረት ሣጥን
23. ሴት ሰኩዬር
24. A2 እና A3 መጠን ወረቀት

ሐ. የካምፕ መገልገያ ቁሳቁሶች /ድንኳን፣ ሽራ አልጋ፣ የመኝታ ከረጢት፣ ... ወዘተ/ ያስፈልጋል።

መ. ለካርታ ሥራ የሚያስፈልጉ ለገጠር ክቅፅ ገ-1 እስከ ገ-6፣ ለከተማ ደግሞ ከቅፅ ከ-1 እስከ ከ-7 እንዲሁም የተሞሉ ቅጾች መረካከቢያ ቅጾችን ይረከባሉ።

ሠ. በአካባቢ ያሉትን ዞኖች፣ ወረዳዎች ከተሞች ዝርዝር ይረከባል።

ረ. ለተመደቡበት አካባቢ የሚሆኑ የትብብር ደብዳቤዎችን ይይዛሉ።

2.2 በዞን ጽ/ቤት

1. የትብብር ደብዳቤዎችን ለሚመለከተው ኃላፊ ያስረክባሉ።
2. ክቅ/ጽ/ቤት የተረከቡትን የወረዳና የከተማ ዝርዝር ትክክለኛነት ያረጋግጣሉ።
3. ለወረዳዎች የትብብር ደብዳቤ ከዞን ጽ/ቤት እንዲፃፍላቸው ያደርጋሉ።

2.3 በወረዳ ጽ/ቤት

1. ለወረዳው የተፃፈውን የትብብር ደብዳቤ ለሚመለከተው ኃላፊ ያስረክባሉ።
2. በወረዳው የሚገኙትን የገጠር ቀበሌ ማህበራት፣ ከተማዎችና የጋርዮሽ መኖሪያዎችን ዝርዝር ከወረዳው ኃላፊዎች በመጠየቅ በተገቢው ቅፅ ላይ ይመዘገባሉ።
3. ስለ ገጠር ቀበሌ ማህበራትና ከተሞች አቀማመጥና አሰፋፈር በመጠየቅ መረጃ ያሰባስባሉ።
4. በወረዳው የመነሻ ካርታ ላይ የወረዳውን ድንበር በመለየት በእርሳስ ይከልላሉ።
5. ለየቀበሌዎች የትብብር ደብዳቤ እፅፈው በመያዝ ለሥራ ዝግጁ ይሆናሉ።
6. በወረዳው ውስጥ በየገጠር ቀበሌዎች እና በየከተማው ስለሚያደርጉት የካርታ ሥራ እንቅስቃሴ ዕቅድ ያዘጋጃሉ። በዕቅዱ መሠረት የካርታ ሠራተኞችን ያሠማራሉ።

2.4 በመስክ ላይ

ሀ. ገጠር

1. የካርታ ሠራተኞች የከለሉትን የወረዳና ቀበሌ ማህበራት ድንበር ትክክለኛነት ያረጋግጣሉ።
2. የቤተሰብ ምዝገባ በመመሪያው መሠረት በተሟላ መልኩ መከናወኑን ያረጋግጣል።
3. በመስክ የተሞሉት ቅጾች በሙሉ በመመሪያው መሠረት መሞላታቸውን ያረጋግጣል።
4. የቆጠራ ቦታ መመስረቻ ቅደም ተከተሎች በትክክል በተግባር ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል።
5. የካርታ ሥራው በወጣለት የጊዜ ሠሌዳ መሠረት በመካሄድ ላይ መሆኑን ይከታተላል።
6. የካርታ ሠራተኞች አስፈላጊ የሥራ ቁሳቁሶች በበቂ መጠን እንዳላቸው ያረጋግጣል።
7. የተሠሩት የቆጠራ ቦታዎች ድንበሮች በሚፈለገው የጥራት ደረጃ መሠራታቸውን ያረጋግጣል።
8. በቆጠራ ካርታ ውስጥ የተካተቱት መንደሮችና ሌሎች ጠቃሚ የምልክት ነጥቦች አንባራዊ ስፍራቸውን እና ስማቸውን ይዘው መስፈራቸውን ያረጋግጣል።
9. ለቆጠራ ቦታዎች በተገቢው መንገድ መለያ ቁጥር መስጠቱን ያረጋግጣል።

10. የቆጠራ ቦታዎች ድንበር መግለጫዎች በቀላሉ ለመረዳት በሚቻል መንገድ መዘጋጀቱን ያረጋግጣል።
11. የቆጠራ ቦታዎች መግለጫና ምልክቶች (Level) በሚገባ መስፈራቸውን ያረጋግጣል።
12. በቆጠራ ቦታዎች መካከል መደራረብ (overlap) ወይም ክፍተት (No-mans-land) አለመኖሩን ያረጋግጣል።
13. የካርታ ሥራውን የሚመለከት የድንበር ግጭት ሲኖር ለካርታው ስራ ሲባል ከሚመለከታቸው የወረዳ ተወካዮች ጋር በመሆን ችግሩን ለመፍታት ጥረት ያደርጋል።
14. ወረዳው በመቆጣጠሪያ ቦታዎች በመመሪያው መሠረት መከፋፈሉን ያረጋግጣል።
15. የተጠናቀቁ የቆጠራ ካርታዎችና ሌሎች ቅፆችን በመረከብ በጥንቃቄ ያስቀምጣል።
16. ስለ ሥራው አፈፃፀም ወርሃዊ ሪፖርት በማዘጋጀት ለቅ/ጽ/ቤቱ ኃላፊ ያስተላልፋል። ሪፖርቱ የሚቀርበው ለዚሁ በተዘጋጀው ቅፅ (ቅፅ አሪ) ላይ ነው።

ለ. <u>ከተማ</u>

1. የክፍተኞች/ወረዳዎች፣ ቀበሌ ማህበራትና የጋርዮሽ መኖሪያዎች ዝርዝር ትክክል መሆኑን ያረጋግጣል።
2. የካርታ ሠራተኞች የከለሉትን የከተማና የቀበሌ ማህበራት ድንበር ትክክለኛነት ያረጋግጣል።
3. የቤቶችና የቤተሰቦች ምዝገባ በመመሪያው መሠረት መከናወኑን ያረጋግጣል።
4. በከተማው ውስጡ የሚገኙ ቀበሌዎች የቆጠራ ቦታ መመሥረቻ ቅደም ተከተሎችን መሠረት አድርገው መከፋፈላቸውን ያረጋግጣል።
5. ከተማው/ወረዳው በመቆጣጠሪያ ቦታዎች በመመሪያው መሠረት መከፋፈሉን ያረጋግጣል።
6. የእያንዳንዱን ቆጠራ ቦታ ካርታ አርጂናል ኮፒ በመመሪያው መሠረት በንጽህናና በትክክል መሠራቱን ያረጋግጣል።
7. የተጠናቀቁ ካርታዎችንና ቅፆችን በመረከብ በጥንቃቄ ያስቀምጣል።
8. ስለሥራው አፈፃፀም ወርሃዊ ሪፖርት በማዘጋጀት ለቅ/ጽ/ቤቱ ኃላፊ ያስተላልፋል። ሪፖርቱ የሚቀርበው ለዚሁ በተዘጋጀው ቅፅ (ቅፅ አሪ) ላይ ነው።

ሐ. <u>በወረዳው ውስጥ የካርታ ሥራ ሙሉ በሙሉ ሲጠናቀቅ</u>

1. የካርታ ሠራተኞቹ በወረዳው የሰሯቸውን የቆጠራ ቦታ ካርታዎች በማገጣጠም የወረዳውን ካርታ በትክክል መፍጠር መቻላቸውን ያረጋግጣል።
2. የካርታ ሠራተኞቹ ቡድን ያዘጋጁትን የወረዳ ካርታ በመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታ መከፋፈላቸውን ያረጋግጣል።
3. አዋሳኝ ወረዳዎች መሃከል የድንበር መደራረብ (overlap) ወይም ክፍተት (No-mans-land) መኖርና አለመኖሩን ከሚመለከተው ተቆጣጣሪ ጋር በመነጋገር አጣርቶ ችግር ሲኖር ያስተካክላል።

3. የካርታ ሥራ ክንውን መከታተያ ዝርዝር ለካርታ ሠራተኞች

3.1 ከመስክ ሥምሪት በፊት

ሀ. የካርታ ሠራተኞች አስፈላጊ የሆኑ ካርታዎችን እንደ ባለ 1፡50,000 መስፈርት ካርታዎች፣ የከተማ፣ ማስተር ፕላን እና ሌሎች ካርታዎችን ከተቆጣጣሪው ይረከባሉ።

ለ. የካርታ ሠራተኞች የሚከተሉትን ለካርታ ሥራው አስፈላጊ የሆኑትን ቁሳቁሶች ይረከባሉ።

እነርሱም፦

1. የጂፒኤስ መሣሪያ ከነባትሪ ድንጋይ
2. የእርሳስ መቅረጫ
3. እርሳስ
4. ማስመሪያ
5. እስክሪፕቶ
6. ሌሮይ ብዕር፣ ጫፍና መያዣቸው
7. ሌሮይ ቀለም
8. ላጲስ (ለእርሳስና ለቀለም)
9. ሴሎ ቴፕ
10. ማስኪንግ ቴፕ
11. ቀይ ማርከር
12. ማስታወሻ ደብተር
13. የትራሲንግ ወረቀት ጥቅል
14. የግራፍ ወረቀት
15. ክላሰር
16. ቦርሳ
17. እስፒል
18. ማስደገፊያ ሠሌዳ
19. ቡልዶግ ክሊፕስ
20. ስቴፕለር
21. የስቴፕለር ሽቦ
22. የብረት ሳጥን
23. ሴት ስኬር
24. A2 እና A3 መጠን ወረቀት

ሐ. ለካርታ ሥራ የሚያስፈልጉ የተለያዩ ቅፆች ለገጠር (ከቅጽ ገ-1 እስከ ገ-6) እና ለከተማ (ከቅጽ ከ-1 እስከ ከ-7) ይረከባሉ።

3.2 በወረዳ ጽ/ቤት፦

1. በወረዳው የሚገኙትን የገጠር ቀበሌ ማህበራት፣ ከተሞችና የጋርዮሽ መኖሪያዎችን ዝርዝር ከወረዳው ኃላፊ በመጠየቅ በተገቢው ቅጾች ላይ ይመዘግባሉ።
2. በመነሻ ካርታው ላይ ከተቆጣጣሪው ጋር በመሆን የወረዳውን ድንበር በእርሳስ ይከልላሉ።
3. ለገጠር ቀበሌ ማህበራት እና ለከተማ ቀበሌዎች የሚሰጥ የትብብር ደብዳቤ አፅፎ በመያዝ ለመስክ ሥራ ዝግጁ ይሆናሉ።

3.2.1 በመስክ ላይ፦

1. የትብብር ደብዳቤውን ለገጠር/ለከተማ ቀበሌ ማህበር አመራር ያደርሳሉ።
2. ከአመራሩ ጋር ስለሥራ እቅድና ስለማረፊያ ቦታ ጉዳይ በመነጋገር ያመቻቻሉ።
3. የከተማዎችንና የጋርዮሽ መኖሪያዎችን ዝርዝር ያረጋግጣሉ።

4. የቀበሌ ማህበራትን ድንበር በእግር በመዞርና በድንበር ነጥቦች ላይ የጂፒኤስ ንባብ በመውሰድ ይመዘግባሉ።
5. በገጠር ቀበሌ ማህበራት የድንበር ነጥብ ንባቦችን በመነሻ ካርታ ላይ በማስፈር ድንበሮችን ያካልላሉ።
6. በወረዳው ድንበር ላይ የሚገኙ ቀበሌዎችን በሚያካልሉበት ወቅት የወረዳውን ድንበር ትክክለኛነት ይረጋግጣሉ።
7. በገጠርና በከተማ ቀበሌ ማህበራት የቤተሰቦችና የቤቶች ምዝገባ ከቤት ቤት በመሄድ ሳይደግሙና ሳይዘለሉ ያካሂዳሉ።
8. በተሰጠው የመመዘኛ ነጥቦች መሠረት የቆጠራ ቦታዎችን ይከፋፍላሉ።
9. በቆጠራ ቦታዎች ውስጥ አስፈላጊና ዋና ዋና ሰውሰራሽና ተፈጥሮአዊ ገፅታዎችን ያካትታሉ።
10. የቆጠራ ቦታ በሚመሠረትበት ወቅት ቦታዎች መዘለል (No-mans-Land) እና መደጋገም (Overlap) ያለመኖሩን ያረጋግጣሉ።
11. ማደግ የሚገባቸውን የቆጠራ ቦታዎች በማሳደጊያ ዘዴ በመጠቀም ያሳድጋሉ።
12. ያደገውን የቆጠራ ቦታ ካርታ ይዘው መስክ በመሄድ ድንበሩን አረጋግጠው ተጨማሪ ዝርዝር መረጃዎችን ያካትታሉ።
13. በመመሪያው በተገለፀው መሠረት የተሟላ የቆጠራ ቦታ ድንበር መግለጫ ያዘጋጃሉ።
14. የትሬሲንግ ወረቀት በመጠቀም የተሟላ ምልክትና መግለጫ የያዙ የቆጠራ ቦታ ካርታዎች በቀለም ያዘጋጃሉ።

3.3 በወረዳው ውስጥ የካርታ ሥራ ሲጠናቀቅ

1. በወረዳው ውስጥ የተሰሩ የገጠር ቆጠራ ቦታዎችን በሙሉ በማገጣጠምና ሌሎች ዝርዝሮችን በማካተት የወረዳ ካርታ ያዘጋጃሉ። ነገር ግን በዚህ ካርታ ውስጥ ከተሞች በከፍተኛ መስፈርት የሚወከሉ በመሆናቸው አንዛራዊ ሥፍራቸው እንጂ ዝርዝር መረጃዎቻቸውን ማስፈር አይቻልም።
2. የወረዳው አዋሳኝ የሆኑትን ወረዳዎች/ዞኖች/ክልሎች ምልክት በማድረግ ስማቸውን በተገቢው ሥፍራ ይፅፋሉ።
3. ከወረዳው ሰሜናዊ አቅጣጫ ከግራ ወደ ቀኝ በመጀመርና የጥምዝምዞሽ አካሄድን በመከተል በወረዳ ውስጥ ለሚገኙ የገጠር ቀበሌ ማህበራት በሙሉ ባለ ሦስት አሀዝ ተከታታይ የመለያ ቁጥር ይሰጣሉ። በተመሳሳይ መንገድ በየገጠር ቀበሌ ማህበሩ ውስጥ ለተመሠረቱ የቆጠራ ቦታዎች ባለ ሁለት አሀዝ ተከታታይ የመለያ ቁጥር ይሰጣሉ።

4. የወረዳውን ካርታ በመመሪያው መሠረት በመቆጣጠሪያ ቦታ በመከፋፈል ከላይ በተራ ቁጥር 3 በተገለፀው መሠረት ባለ ሁለት አሀዝ ተከታታይ የመለያ ቁጥር ለመቆጣጠሪያ ቦታዎች ይሰጣሉ።

5. የተሰጠውን መለያ ቁጥር መሠረት በማድረግ ካርታዎችን፣ ቅያችንና ሌሎች ሰነዶችን አስተካክለው ለተቆጣጣሪው ያስረክባሉ።

<u>ማስታወሻ</u>፦

1. አንድ ወጥ የሆነ ምልክትና መግለጫ አጠቃቀም እንዲኖር በዕዝል IV የተሰጠውን ዝርዝር መጠቀም ያስፈልጋል።
2. በሚዘጋጁት ካርታዎች ላይ በተቻለ መጠን የካርታውን ተነባቢነት ሊያሻሽሉ የሚችሉ ዝርዝሮችን መጨመር ጠቃሚ ነው።
3. በወረዳ ውስጥ በከፍተኛ መሰፈርት ካርታ ለተሠራላቸው ከተሞች /ማለትም በማስተር ፕላን ወይም ንድፍ ላይ/ ለቀበሌዎች፣ ለመቆጣጠሪያና ለቆጠራ ቦታዎች በክፍል 3.3 ከተራ ቁጥር 1-5 የተሰጡት መመሪያዎች ተግባራዊ እንደሚሆኑ መገንዘብ ያስፈልጋል።

ብሔራዊ የሕዝብና ቤቶች ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

ወርሃዊ የቆጠራ ካርታ ሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ቅጽ

ቅፅ አወሪ-1

ክልል _____ ዞን _____ ወረዳ _____

1. ገጠር

1.1 አጠቃላይ የገጠር ቀበሌዎች ብዛት _____

ሀ/ በመሠራት ላይ ያሉ _____

ለ/ የተጠናቀቁ _____

ሐ/ ያልተጀመሩ _____

1.2 የተጠናቀቁ የቆጠራ ቦታዎች ብዛት _____

2. ከተማ

2.1 አጠቃላይ የቀበሌዎች ብዛት _____

ሀ/ በመሠራት ላይ ያሉ _____

ለ/ የተጠናቀቁ _____

ሐ/ያልተጀመሩ _____

2.2 የተጠናቀቁ የቆጠራ ቦታዎች ብዛት _____

3. ወረዳውን ለማጠናቀቅ የሚያስፈልጉ ተጨማሪ ቀናት _____

_____

4. ያጋጠሙ ችግሮች _____

_____

_____

_____

_____

7. የተወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች _____

_____

_____

_____

_____

_____

የተቆጣጣሪው ስም _____ ፊርማ _____ ቀን ___/___/___

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት

የቆጠራ ካርታ ሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ቅፅ

(የወረዳ ማጠቃለያ)

ቅፅ አወራ-2

ክልል _____ ዞን _____ ወረዳ _____

1. በወረዳው የሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች ብዛት _____
2. በወረዳው የሚገኙ የከተማ ቀበሌዎች ብዛት
3. የተጠናቀቁ የቆጠራ ቦታዎች ብዛት ገጠር _____
   ከተማ_____
4. የተጠናቀቁ ቀበሌዎች ብዛት ገጠር _____
   ከተማ_____
5. የመስክ ሥራ የተጀመረበት ቀን _____
   የመስክ ሥራ የተጠናቀቀበት ቀን _____
6. ወረዳውን ለማጠናቀቅ የወሰደው ቀን ብዛት _____
7. የተመደቡ ቡድኖች ብዛት _____

የተቆጣጣሪ ስም _____ ፊርማ _____ ቀን_____

የሕዝቦና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
ዕለታዊ የካርታ ሥራ ክንውን መከታተያ ቅፅ

ቅፅ አወሪ - 3

ክልል _____ ዞን _____ ወረዳ _____

ተ.ቁ.	ቀን	አርዕስት	የካርታ ሠራተኞች ስም					
		የተግባራት ዝርዝር						
		ቀበሌ						
		የተግባራት ዝርዝር						
		ቀበሌ						
		የተግባራት ዝርዝር						
		ቀበሌ						
		የተግባራት ዝርዝር						
		ቀበሌ						
		የተግባራት ዝርዝር						
		ቀበሌ						
		የተግባራት ዝርዝር						
		ቀበሌ						
		የተግባራት ዝርዝር						
		ቀበሌ						
		የተግባራት ዝርዝር						
		ቀበሌ						
		የተግባራት ዝርዝር						
		ቀበሌ						
		የተግባራት ዝርዝር						
		ቀበሌ						
		የተግባራት ዝርዝር						
		ቀበሌ						
		የተግባራት ዝርዝር						
		ቀበሌ						

የተቆጣጣሪ ስም _____ ፊርማ _____ ቀን ____/____/_____

የሕዝበና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
የካርታ ሠራተኞች የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ቅፅ
(የወረዳ ማጠቃለያ)

ቅፅ አወሪ - 4

ክልል _____ ዞን _____ ወረዳ_____

1. የካርታ ሠራተኞቹ ስም _____ኮድ _____
   _____ኮድ _____
2. የተቆጣጣሪ ስም _____ኮድ _____
3. በወረዳው ሥራ የተጀመረበት ቀን _____
4. በወረዳው ሥራ የተጠናቀቀበት ቀን _____
5. የተጠናቀቁ የቆጠራ ቦታዎች ዝርዝር_____

ተ.ቁ.	የከተማ ስም ወይም የገጠር ቀበሌ ስም	የቀበሌ መለያ ቁጥር	የቆ. ቦታ መለያ ቁጥር

ዕዝል VI

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
የቅጾችና ካርታዎች መረካከቢያ ቅጽ

ቅጽ- ካቅመ - ገ

ክልል _____ ዞን _____ ወረዳ _____

የካርታ አይነት				ቅጾች			
የመቆ. ቦታ ኮድ	የገጠር ቀበሌ ስም	ተ.ቁ	የቆ.ቦታ/የልዩ ቆ. ቦታ ኮድ	ገ-2	ገ-4	ገ-5	ገ-6

የሕዝብና ቤት ቆጠራ ኮሚሽን ጽ/ቤት
የቅጾችና ካርታዎች መረካከቢያ ቅጽ

ቅጽ- ካቅመ - ከ

ክልል _____ ዞን _____ ወረዳ _____

የካርታ አይነት						ቅጾች			
የመቆ. ቦታ ኮድ	የከተማው ስም	ተ.ቁ	የከፍተኛ ኮድ	የቀበሌ ኮድ	የቆ.ቦታ ኮድ	ከ-2	ከ-4	ከ-5	ከ-6